# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የማንባብ ባህላቸው ከማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለው ተዛምዶ፤ (በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በከምባታ-ጠምባሮ ዞን ስድስት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ናሙናነት)

በ

ሙሉ ሠለሞን

ሰኔ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የማንባብ ባህላቸው ከማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለው ተዛምዶ፤ (በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በከምባታ-ጠምባሮ ዞን ስድስት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ናሙናነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለ በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር (TeAm)
ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ
ሙሉ ሠለሞን

CLEARED FROM ILS LIBRARY

ሰኔ 2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የማንባብ ባህላቸው ከማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለው ተዛምዶ፤ (በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በከምባታ-ጠምባሮ ዞን ስድስት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ናሙናነት


በ

ሙሉ ሠለሞን


ሰኔ 2005 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

የአማካሪ ስም

ደረጀ ገብሬ

ፊርማ

የፈታኝ ስም

ገሠሠ፡ ታደሰ (ዶ/ር)

ፊርማ

ዘሪሁን እንዳለማው


ILS LIBRARY
ADDIS ABAB

## መታሰቢያነቱ

ተስፋህና ምኞትህ የኔን እዚህ ቦታ መድረስ የነበረውና አሁን ግን በህይወት የሌለኸው ውድ አባቴ ሠለሞን ሀይለኢየሱስ ይኸው ደርሼልሃለሁ፤ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ለአባቴ ለአቶ ሰለሞን ኃይለኢየሱስ ይሁንልኝ፡፡

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሞ ለዚህ ጊዜ ያደረሰኝን አምላክ ከናቱ ከድንግል ማሪያም ጋር ምስጋና ይድረሰው፡፡ ከጥናቱ ርዕስ መረጣ ጀምሮ ጥናቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሙያዊ ድጋፍና ምክር በመለገስ ጥናታዊ ጽሑፉ አሁን የያዘውን ቅርጽ እንዲያገኝ ላደረጉኝ መምህሬና አማካሪዬ ለአቶ ደረጀ ገብሬ (ረዳት ፕሮፌሰር) ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

ይህንን የትምህርት ዕድል ለሰጠኝ የደቡብ ትምህርት ቢሮ፣ እንዲሁም ለጥናቱ የሚሆን ገንዘብ ለፈቀደልኝ በአአዩ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ለጥናቱ መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ ለዱራሜ፣ ለሺንሺቾ፣ ለሀደሮ፣ ለአንጋጫ፣ ለዳንቦያ እና ለዶዮገና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ርዕሰ መምህራንና መምህራን ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

የጽሑፉን ረቂቅ በማንበብና በማረም፣ አስፈላጊውን እገዛ በማድረግ ለተከታተሉኝ ለመምህሬ ለአቶ ጌታቸው እንዳላማው (ረዳት ፕሮፌሰር) እንዲሁም ለአቶ ተክለኃይማኖት ገ/ፃዲቅ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ ከፍተኛ ሞራልና ድጋፍ በመስጠት ከጎኔ ላለው እጮኛዬ ለመ/ር መንግስቱ አውላቸው፣ ማበረታቻ እና ድጋፍሽ ላልተለየኝ እናቴ ለወ/ሮ ወይንሸት ዘለቀ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ ከኔ ጋር ለነበራችሁ እህቶቼ እና ወንድሜ፣ ጥሩ ለተመኛችሁልኝ ዘመዶቼና ጓደኞቼ በሙሉ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

ይዘት ገጽ


ምስጋና ........................................................................................................I

ማውጫ ..........................................................................................................II

የሰንጠረዥ ማውጫ..........................................................................................IV

አጠቃሎ ........................................................................................................V

ምእራፍ አንድ

መግቢያ ........................................................................................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ................................................................................................ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ችግር..................................................................................... 3

1.3 የጥናቱ ዓላማ ............................................................................................. 5

1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት....................................................................................... 5

1.5 የጥናቱ ወሰን (Scope) ................................................................................... 6

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳናት .............................................................................................. 8

2.1 ንባብና የንባብ ባህል ....................................................................................... 8

2.1.1 የንባብ ምንነት.............................................................................................. 8

2.1.2 የንባብ ዓላማ................................................................................................ 9

2.1.3 ማንበብ ለምን ይጠቅማል? ............................................................................... 11

2.1.4 የንባብ ባህል ምንድነው?.................................................................................. 15

2.1.5 የንባብ ባህል መገለጫዎች ................................................................................ 16

2.1.6 በንባብ ባህል ላይ ያሉ ተፅዕኖዎች ..................................................................... 18

2.1.7 የንባብ ባህል ለማጎልበት የሚያግዙ ነጥቦች ......................................................... 19

2.1.8 የአንባብያን አይነቶችና ባህሪያት ......................................................................... 24

2.1.8.1 ብቁ የሆኑ አንባብያን .................................................................................. 24

2.1.8.2 ብቁ ያልሆኑ አንባብያን.................................................................................. 25

2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት .................................................................................. 26

ምዕራፍ ሶስት

3.1 የጥናቱ ዘዴ ........ 29

3.1.1 የጥናቱ አካባቢ ናሙና አመራረጥ ........ 29

3.1.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ........ 29

3.1.3 የተጠኚ መምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 30

3.1.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 30

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 31

3.2.1 የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ........ 31

3.2.1.1 የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ........ 32

3.2.1.2 የክፍል ውስጥ ምልከታ ........ 33

3.2.1.3 ቃለ መጠይቅ ........ 33

3.2.1.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 34

ምእራፍ አራት

የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ........ 35

4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና ........ 35

1.1.1 የተጠኚ መምህራን ዳራዊ መግለጫ ........ 36

1.1.2 የመምህራን የንባብ ባህል በተመለከተ ከቀረበው መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 37

ምእራፍ አምስት

ማጠቃለያና አስተያየት ........ 62

5.1 ማጠቃለያ ........ 62

5.1.አስተያየት ........ 64

ዋቢ ጽሑፎች ........ 67

አባሪዎች

# የሰንጠረዥ ማውጫ


ገፅ

ሠንጠረዥ 1፡- የተጠኚ መምህራን ዳራ ....................................................................36
ሰንጠረዥ 2፡ የመምህሩ የንባብ ባህል ባህሪያት .......................................................37
ሠንጠረዥ 3፡ የመምህሩን የንባብ ባህል የሚገልጹ ባህሪያት .........................................38
ሰንጠረዥ 4፡- መምህራን በብዛት የሚያነቧቸው ጽሑፎች .............................................40
ሠንጠረዥ 5፡ መምህራን የንባብ ልምዳቸውን ለሌሎች የማጋራት ሁኔታ .........................41
ሰንጠረዥ 6፡ የንባብ ባህል ሊዳብር የሚችለው እንዴት ነው? ........................................42
ሠንጠረዥ 7፡ መምህራን ንባብን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ዘዴ አስመልክቶ የተገኘ መረጃ .....................................................................................................44
ሠንጠረዥ 8፡ ንባብን ለመማር የሚጠቀሙት ጽሑፍ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ ......................................................................................................45
ሰንጠረዥ 9፡ መምህራኑ ምንባቡን እንዴት እንደሚተገብሩ የሚያሳይ የተገኘ መረጃ ......47
ሠንጠረዥ 10፡ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ .......................................48
ሠንጠረዥ 11፡ በአካባቢያቸው ንባብን የሚያበረታታ/ የሚያደናቅፍ ምን ሁኔታ እንዳለ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ...........................................................49
ሠንጠረዥ 12፡ መምህራኑ የሚያከናውኗቸው ማስተማሪያ ዘዴያቸውን የተመለከ መረጃዎች ...............................................................................................51
ሠንጠረዥ 13፡ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ...............................52
ሠንጠረዥ 14፡ከመማሪያ መጻሕፍት ውጪ ለሚቀርቡ ጽሑፎች ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ .......................................................................................................54
ሠንጠረዥ 15፡መምህራን ተማሪዎቹን እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው የሚያሳይ ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ......................................................................55
ሠንጠረዥ 16 መምህራኑ የምንባቡን መልእክት እንዲረዱ የተጠቀሙበት ዘዴ ከምልከታ የተገኘ መረጃ......................................................................................................56
ሰንጠረዥ 17፡ የንባብ አይነቶችን በተመለከተ ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ........................................................................................................57
ሠንጠረዥ 18፡ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ........................................58
ሠንጠረዥ 19፡ ንባብን ደቂቃ በመወሰን የማንበብ ተግባር በክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ .......................................................................................................59
ሠንጠረዥ 20፡ ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር በማገናኘት የማንበብ ተግባር ከምልከታ የተገኘ መረጃ.........................................................................................59

# አጠቃሎ (Abstract)

ይህ ጥናት በከምባታ ጠምባሮ ዞን ባሉ ስድስት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የማንበብ ባህል ከንባብ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለውን ግንኙነት መመርመር አብይ አላማው አድርጎ የተከናወነ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደባቸው፤ዱራሜ፣ ሺንሺቾ፣ አንጋጫ፣ ሀደሮ፣ ዳምቦያ እና ዶዮገና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ በእነዚህ ትምህርት ቤቶችም አራት ሴት እና አስራ አራት ወንድ መምህራን በድምሩ አስራ ስምንት መምህራን በጠቅላይ ንሞና ዘዴ /Comprehensive Sampling/ ተወስደው እንዲጠኑ ተደርጓል፡፡ ለጥናቱ መረጃዎችን ለማግኘትም የጽሑፍ መጠይቅ፣የክፍል ውስጥ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ በግልጋሎት ላይ ውለዋል፡፡ በነዚህ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎች በሶስት ጎንዮሽ /data triangulation / በመጠቀም በተቀናጀ ሁኔታ ተተንትነዋል፡፡ ከትንተናው የተገኘው ውጤትም የመምህራኑ የንባብ ባህል ዝቅተኛ እንደሆነ አመልክቷል፡፡ በመምህራኑ የንባብ ባህልና ንባብን ለማስተማር በሚከተሉት ዘዴ መካከል ያለው ግንኙነት ዝቅተኛ እንደሆነ ታይቷል፡፡ የመምህራኑ የንባብ ባህል ዝቅተኛ መሆን በክፍል ውስጥ ንባብን ለማስተማር በሚከተሉት ዘዴ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ፈጥሯል፡፡ ለዚህ የንባብ ባህል ዝቅተኛ መሆንም በአካባቢው የሚነበቡ መጻሕፍትን የማግኘት እድሉ ጠባብ መሆን፤ በአካባቢው ንባብን የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች ተጽዕኖ፣ የመምህራኑ ውስጣዊ የስሜት ሁኔታ፣ ፍላጎት እና ሌሎች በምክንያትነት ተጠቅሰዋል፡፡ በመጨረሻም በጥናቱ የተገኙ ውጤቶች በመመርኮዝ የመምህራኑን የንባብ ባህል ለማዳበር፣ በንባብ ባህልና በማስተማሪያ ዘዴያቸው መካከል ያለውን አዎንታዊ ተፅዕኖ ተጠቁሞዋል፡፡ ከተሰጡት አስተያየት መካከል መምህራን የንባብ ልምዳቸውን ተጠቅመው ንባብን ለማስተማር ዘዴያቸው ለተማሪዎች በሚያመች መልኩ ከመማሪያ መጻሕፍት ውጪ ተጨማሪ ጽሑፎችን ቢጠቀሙ፤ ምቹ የማንበቢያ ቦታና የህዝብ ቤተ መጻህፍት መኖር፣ መምህራኑ የንባብ ባህላቸውን እንዲያጎለብቱ ለማድረግ መንግስታዊ የሆኑና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እገዛ ቢያደርጉ የሚል አስተያየት ተሰንዝሯል፡፡

# ምእራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ስለንባብ ባህል ጥናት ማድረግ ጠቀሜታ እንዳለው የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ምህረቱ (1999፤42) ብርሀኑ (1999)ን ጠቅሰው "የንባብ ባህል ምርምር የተጀመረው በ19 ኛውና በ20ኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓና በአሜሪካ በብዙሃኑ አንባቢ ሕዝብ ዙሪያ እና ከዚህም ጋር ተያይዞ የንባብ ምርምር በኢትዮጵያና በሌሎች በትምህርት ባልገፉ ህብረተሰቦች መካከል የቅርብ ጊዜ ክስተት" እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

የንባብ ባህልን ማዳበር በብዙ አቅጣጫ የአንድን አገር ዕድገት ያፋጥናል፡፡ ሰዎች የማንበብ ችሎታ ከሌላቸው ስለጤና ማህበራዊ ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ አጀንዳዎች ጠቃሚ መረጃ ሊያገኙ አይችሉም፡፡ በዚህ አይነት ከተለያዩ ጥናቶች የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው አብዛኞቹ አፍሪካዎች የአውሮፓዎችን ያህል አይጽፉም፡፡ ሕዝቦቻችንም ያልጻፍነውን ሊያነቡ አይችሉም፡፡

እንደ Smith (1997) ገለጻ የንባብ ባህል ወይም ልምድ የንባብን ትምህርት አላማ በማዳበርና በማበልጸግ ላይ ይመሠረታሉ፡፡ ይህ አይነቱ ልምድ እንዲዳብርና እንዲበለጽግ ከተፈለገ ሰዎች ከንባብ ጋር ያላቸውን ቀረቤታ የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡ ወደንባብ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ወደንባብ እየቀረቡ ሲመጡ ለንባብ የሚጠቀሙበት ጊዜ እየሰፋ ይመጣል፤ ለንባብ የሚመድቡት ጊዜ ሲሰፋና የሚያነቡት መፅሐፍ፣ መጽሔት፣ ጋዜጣ ወዘተ በአይነትና በቁጥር እየጨመረ ሲመጣ ደግሞ የንባብ ልምድ አዳብረዋል ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

የንባብ ባህል ወይም ልምድ የሚመሰረተው የንባብን ተግባራት በተደጋጋሚ በማከናወን ነው፡፡ ይህ ማለት ተግባራቱ በተደጋጋሚ ሲፈጸም የንባብ ባህል በአዕምሮ ውስጥ ሰርፀው የመግባት እድል ያገኛል፡፡ በአእምሮ ውስጥ ሰርፆ የገባ ነገር ደግሞ በቀላሉ የማይላቀቁት ይሆናል፡፡ንባብን በተደጋጋሚ ማንበብ የጀመረ አንባቢ የተዋጣለት አንባቢ ይሆናል፡፡ ከዚህ አኳያ የተዋጣለት አንባቢ የሚከተሉት

ሁኔታዎች ይንጸባረቁበታል፡፡ የንባብ ፍላጎት፣ የንባብ ፍጥነት፣ የንባብ ስልትን መቀያየር፣ ድምጽን ከፍ አድርጎ በእርጋታ ማንበብ እና ዘና ያለ ንባብ ናቸው (Charles 1985:207፣ አለም፤2001፡65)፡፡

የንባብ ባህል ከትምህርት መስፋፋትና ማደግ ጋር የማይነጣጠል ትስስር አለው፡፡ በሀገራችን በአንደኛ ደረጃም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ማዳበር ነው፡፡የማንበብ ክሂል መዳበር ለማዳመጥ፣ለመናገር ና ለመጻፍ ክሂሎች መዳበር አስተዋፅኦ እንዳለው Sheng (2000:12) ያብራራሉ፡፡

የተለያዩ ተመራማሪዎች ንባብ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ውስጥ ዋነኛ መሳሪያ እንደመሆኑ መምህሩም ለማስተማር ያነባል፤ ተማሪዎችም ለመማር ብሎም ውጤት ለማግኘት ያነባሉ፡፡ ይህ የማንበብ ሂደት የፊደልን ቅርፅ ለይቶ ከማንበብ እስከ ከፍተኛው ደረጃ ድረስ ያለውን አእምሯዊ ክንውን ያጠቃልላል፡፡ ማንበብ በአንባቢው ፍላጎት የሚመራ ተግባር ሲሆን አንባቢው በተቻለው መጠን የፀሐፊውን ሀሳብ ለመገንዘብ ሲል የሚያነበውን ጉዳይ መገምገምን የሚጠይቅ አዕምሯዊ ተግባር መሆኑን (ተስፋዬ፣1981) ይገልፃሉ፡፡

ንባብ እንደተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ በይዘት አቀራረቡ ተመጥኖና በመምህራኑ የማስተማሪያ ዘዴ እንደሚሰጥ ግልፅ ነው፡፡ በመሆኑም በሁለተኛ ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች የንባብ ክሂላቸውን ለማዳበር የአንብቦ መረዳት ትምህርት ይሰጣል፡፡ የአንብቦ መረዳት ትምህርትን በክፍል ውስጥ ለማስተማር መጀመሪያ መምህሩ ቀድሞ ምንባቡን አንብቦ እና የትኛውን ዘዴ ተጠቅሞ እንዴት ማስተማር እንዳለበት እቅድ ነድፎ ወደ መማሪያ ክፍል መሄድ አለበት (Nuttall 1982፡1)፡፡

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እነዚህን ተግባራት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በክፍል ውስጥ በተገቢው መንገድ ማከናወናቸው ብዙ ጊዜ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሻሻል የተመረጡ ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍት መቅረባቸው ብቻ የታለመውን የመማር ውጤት እውን ሊያደርግ አይችልም፡፡

ምንም እንኳን ንባብ በግል የሚከናወን ተግባር ቢሆንም ተማሪዎች አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡ እነዚህም ቅድመ ሁኔታዎች ተማሪዎች የሚያገኙትን ፅሑፍ እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ዘዴውን ማሳየት ፣ለተማሪዎች የንባብ ዘዴዎችን በተግባር ማስተማር እና የንባብ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው ፡፡

በንባብ ልምድ ላይና በንባብ ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ጥናቶች የተካሄዱ ቢሆንም፤ አብዛኛዎቹ በተማሪዎች ላይ የተሰሩ ናቸው፡፡ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛነት በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ የሚከሰት ሊሆን ይችላል፡፡ከማስተማሪያ መጻሕፍት በዘመናዊ ሁኔታ አለመዘጋጀት፣ ትምህርቱ ከሚሰጥበት ዘዴና ከተማሪዎች ቁጥር መጨመር ጋር አያይዘው የተመለከቱ ጥናቶች አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ማስተዋል (1989)፣ ወንድአጥር (1993)፣ የኔ ሰው (1990)፣ በኅሰው (2003) ፤አለም (2001)፣ ደረጀ (2009)፣ ብርሃኑ (1999) ምህረቱ (1999) ይገኙበታል፡፡

ይሁን እንጂ በሀገራችን የመምህራን የንባብ ባህል ከማንበብ ማስተማሪያ ዘዴ ክሂል ጋር ያለው ዝምድና ከግምት የሚገባ ትኩረት ተሰጥቶት ምርምር የተደረገበት ስለመሆኑ አላጋጠመም፡፡ ከዚህ አንጻር የመምህራን የንባብ ልምድ ለክፍል ውስጥ ማስተማሪያ ዘዴያቸው የሚያመጣው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖች መመልከቱ የተማሪዎቹ አንብቦ መረዳትና የንባብ ልምድ መዳበር መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት መሰረትም የመምህሩ የንባብ ባህል ከማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ ጉዳይ ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ችግር

ንባብ፣አንባቢ ከአንድ ከተወሰነ ጽሑፍ ጋር መስተጋብር በመፍጠር ለራሱ ትርጉም የሚወስድበት የቋንቋ አገላለጽ ሲሆን፣ አንባቢም ከቀረበው ምንባብ ትርጉም እንዲያገኝም የአንባቢና የጸሐፊ አስተዋጽዖ ያስፈልጋል (Nattall, 1982:10) ፡፡

ተማሪው የቀረበለትን ጽሑፍ በአግባቡ የራሱን የአነባበብ ስልት ተጠቀሞ ክሂሉን ያዳብር ዘንድ ቋንቋቸው አፍ መፍቻ ሆነም አልሆነ ትምህርቱ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን

የተማሪዎች የንባብ ልምድ ችግር እስካሁን ድረስ እንዳልተቃለለ ከላይ የተገለጹት ጥናታዊ ፅሑፎች ይጠቁማሉ፡፡

በሌላ መልኩ የንባብ ባህል አለመዳበር በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ የሚከሰት ነው፡፡ይህን አስመልክተው የንባብ ባህል ያለመዳበር ችግር ሰዎች ስለራሳቸው ህይወት እያነበቡ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ የሚያግዙ ጽሑፎች እምብዛም ያለመኖር፣ ከመጻሕፍት ጋር ያላቸው ግንኙነት አናሳ መሆን፣ የጊዜ አጠቃቀማቸውን በአግባቡ አለመተግበር እንዲሁም መምህራን ለተማሪዎቻቸው የንባብ ልምድን ለማስገኘት የሚያስፈልጉ ተቀዳሚ ተግባራትን በወጉ አለማከናወናቸውን አያይዘው የተመለከቱ አጥኚዎች (ምህረቱ፤1999፣ Birhanu,1999፣ አለም፤2001፣ ደረጀ፤2009) የንባብ ልምዳቸው ከላይ በተገለጸው መንገድ ዝቅተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በዚህ መሠረት የዚህ ጥናት መነሻ አለም (2001)፣ " የንባብ ልምድ ፍተሻ በአዲስ አበባ ወጣቶች መነሻነት" እና ደረጀ (2009) ፣"የንባብ ልምድ ቅኝት በአዲስ አበባ" የሚል ርዕስ ነው፡፡ በጥናታቸው እንደጠቆሙት የንባብ ልምድ ሊያድግና ሊዳብር እንደሚገባው ቢያምኑም የብዙዎቹ የንባብ ልምድ አጥጋቢ አለመሆኑን፣ ትምህርት ቤቶች ለንባብ ልምድና ፍላጎት መሰረት አለማስያዛቸው፤ ለዚህ መሰረት ጣዮቹ መምህራን፣ በመማር ማስተማሪያ ቁሳቁስ ጥራትና ሌሎችንም ተጠያቂዎች እንደሆኑ አመልክተዋል፡፡ ይሁንና አጥኚዋ እነዚህን ችግሮች በምታስተምርበት ትምህርት ቤት ስለተመለከተች የመምህራኑን የንባብ ልምድ ከክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ዘዴው ጋር ያለውን ተዛምዶ እንድታጠና አነሳስቷታል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ጥናቱ በደቡብ ክልል በሚገኘው በከምባታ ጠምባሮ ዞን የመሰናዶ ትምህርት ቤት መምህራን ላይ ያተኩራል፡፡ የተተኳሪ መምህራን የንባብ ባህል ከማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ተዛምዶ አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ይመረምራል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል፡፡

1. በመምህሩ የንባብ ባህልና የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴያቸው መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?

2. መምህሩ በክፍል ውስጥ የሚጠቀመው የማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴው ምን ይመስላል?

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በከምባታ ጠምባሮ ዞን የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንባብ ባህል ከክፍል ውስጥ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው:: በዚህ ዓላማ ስርም የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች ይገኛሉ::

1. በመምህራኑ የንባብ ልምድና የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴያቸው መካከል ያለውን ግንኙነት መፈተሽ፣
2. የማንበብ ክሂልን ለማስተማር መምህራኑ በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበትን ዘዴ መመርመር፣

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ፣ በተለይም የማንበብን ክሂል በይበልጥ ለማዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ ከማስገኘት አንጻር አስፈላጊነት ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል:: በዚህ መሰረትም ጥናቱ:-

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንባብ ባህል መኖር ወይም ያለመኖር ለተማሪው የንባብ ልምድ አዎንታዊ እና አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያመጡ ተረድተው የንባብ ልምዳቸው ይጨምራል::
2. መምህራን በክፍል ውስጥ የንባብ ክሂል ትምህርት ሲሰጡ፣ ለማስተማሪያነት የሚጠቀሙበትን ዘዴ ለማሻሻል የሚሰጡት ትኩረት ምን መሆን እንዳለበት ጥቆማ ይሰጣል::
3. መምህራኑ የንባብን ባህል ለማሳደግ የራሳቸውን ጥረት እንዲያደርጉ መንገድ ይከፍታል::

4. ለትምህርት ባለሞያዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት አስተዋጽዖ ያርጋል፡፡
5. ይህ ጥናት ወደፊት ተመሳሳይ ጥናት ለማካሄድ ለሚፈልጉ ጥናት አቅራቢዎች መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን በመጠቆም ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ታስቦዋል፡፡

## 1.5 **የጥናቱ ወሰን** (Scope)

ይህ ጥናት በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በከምባታ ጠምባሮ ዞን በሚገኙ ስድስት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ላይ የተካሄደ ነው፡፡ ትኩረቱም በከምባታ ጠምባሮ ዞን በሚገኙ ዱራሜ፣ ሺንሺቾ፣ ሀደሮ፣ አንጋጫ፣ ዳምቦያ፣ ዶዮገና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንባብ ባህላቸው የማንባብን ክሂል ማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለው ዝምድና ምን ይመስላል? የሚለውን መፈተሽ ብቻ ይሆናል፡፡

ጥናቱ በመምህራኑ የንባብ ባህል የማንባብን ክሂል ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለውን ግንኙነት ከመፈተሽ ሌላ ሌሎች ክሂሎችን (የመጻፍ፣ የማዳመጥ እና የመናገር)፣ ማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ እና የመምህሩን የክፍል ውስጥ አቀራረብ አይመለከትም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ንባብና የንባብ ባህል

### 2.1.1 የንባብ ምንነት

ስለ ንባብ ምንነት የመስኩ ተመራማሪዎችና አጥኚዎች ተቀራራቢነት ያለው ብያኔና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ እነዚህ ብያኔዎች የዓላማ ልዩነት ይኑራቸው እንጂ ተቀራራቢ ናቸው፡፡ የአብዛኛዎቹን ብያኔ ሰጪዎች የሚወክለው ንባብ ግላዊ ነው፡፡ ንባብ አዕምሯዊ ወይም የግንዛቤ ሂደት ሲሆን አንባቢውንም ከቦታና ጊዜ ርቆ የሚገኝ ፀሐፊ ያስተላለፈውን መልእክት እንዲከታተልና አጸፋዊ መልስ እንዲሰጥ የሚያደርግ ነው በማለት Davis (1995:1) እና Nuttall (2000፡4) ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም አንባቢው በንባብ ሂደት የጽሑፍን መልእክት ለመገንዘብና ከውስጡ አስፈላጊ መረጃ ለይቶ ለማውጣት ከጸሐፊው ሐሳብ ጋር መስተጋብር ይፈጥራል፡፡ ስለዚህም ንባብ የሌሎች ሰዎችን ሀሳብ ለማወቅና ለመረዳት የምንጠቀምበት ተግባር ነው፡፡

ንባብ አንዱ የመረጃ መቀበያ ክሂል በመባል ይታወቃል ፡፡ ማንበብ ሲባል የተጻፈን ሁሉ ከዳር እስከዳር ከመወጣት ጀምሮ መምረጥ፣ መመርመርን የሚጠይቅ ነው፡፡ ማንበብ ማለት መረዳት፣ ማመዛዘንን፣ መገመትን፣ ማመሳከርን፣ መጠየቅን፣ ማወቅንና መርካትን እንደሚያጠቃልል ተስፋዬ (1981፡51-61) ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ በመነሳት ማንኛውንም ንባብ ስናነብ ሳንረዳ መጨረስ ሳይሆን ስለምናነበው ንባብ ማወቅና መረዳት አለብን፡፡

እንዲሁም Grellet (1981:3) ንባብ በውስጡ በርካታ ንኡሣን ክሂሎችን የያዘ፣ከአንድ ጽሑፍ ውስጥ የተፈለገውን መልእክት ወይም መረጃ በተቻለ መጠን በብቃት ማውጣትን የሚመለከት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ Cooper (1997)፣ McDonough & Shaw (2003)፣ Wallac(1992)፣ Williams (1984)፣ Zint (1976:8-9)፣ Ur (1996) እና ሌሎቹም ምሁራን ንባብን በየራሳቸው አገላለጽ በይነውታል፡፡ ሁሉም ግን

ማንበብ ከመገንዘብና ከመረዳት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ ስለሆነም ንባብ አንድን ጽሑፍ አንብቦ በተቻለ መጠን የመገንዘብ፣ የመረዳ ሂደትን የሚመለከት ነው፡፡

ንባብ በሰዎች መካከል መረጃ የመለዋወጥ ሂደት ነው፡፡ አንባቢ ከሆንን ፊዛዛ አንሆንም፣ ንቁ እንሆናለን፡፡ ይህ ማለት በምንባቡ ውስጥ ያለውን መልእክት ከህይወታችን ጋር ማቀናጀት እንችላለን፡፡ የአንባቢው ትርጉምና እውቀት ከዓለም ጋር በማዋሃድና ሁኔታውን በመዳሰስ ይገምታል፣ በተጨማሪም የምናነበውን ነገር ለመረዳት መልእክት እንደሚያስፈልግ Mac Lahlan እና Reid (1994, 3-4) ገልጸዋል፡፡

ተክላይ (2000፣38) Nuttall (1996)ን በመጥቀስ ንባብ በሶስት የተለያዩ ደረጃዎች እንደሚከፈልና የንባብ ትምህርት እነዚህን ደረጃዎች ደረጃ በደረጃ እንደሚያልፉቸው ያስረዳሉ፡፡

በዚህም መሰረት፡-

- መነጠል፣ መለየት፣መቁጠር (ለፊደል ወይም ለምልክት)
- ከአንደበት ማፍለቅ፣ንበት፣የድምጽ አፈላለቅ፣መናገር ወዘተ.
- መረዳት፣መገንዘብ፣ትርጉም መጨበጥ፣ ስሜት መከተል ወዘተ.

ባጠቃላይ ንባብ አንድ ሰው የቀረበውን ርዕሰ ጉዳይ ተረድቶ ዋና መልዕክት ላይ አስተያየት ለመስጠት፣ ሀሳብን ውድቅ ለማድረግ ወይም በሀሳቡ ተስቦ የራሱን አስተያየት ለማቅረብ፣ ከራስ አስተሳሰብ ጋር አዋህዶ በተግባር ለማሳየትና ለመግለጽ ከሚያስችል ግንዛቤ ላይ እንዲደርስ የሚያደርግ መሆኑን እንረዳለን፡፡

### 2.1.2 **የንባብ ዓላማ**

ንባብ አላማ አለው፣ የምናነበው ነገር አላማችንን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ በሕይወታችን ውስጥ በየቀኑ የተለያዩ መጻሕፍትን በተለያየ መንገድ ልናነብ እንችላለን፣ ለምን እንደምናነብ ጥያቄ መጠየቅና መልሱን መመለስ ስንችል ነው፡፡ ሰዎች ንባብን ለምን እንደሚያነቡ በመጠየቅ Grellt (1981)፣ Wallace (1992:6-7)፣ Davies (1995፡133)፣ አለም (2001) በሚከተሉት ሦስት መሰረታዊ የንባብ

አላማዎች በቅደም ተከተል ይዘረዝሯቸዋል፡፡ እነዚህም ንባብ ለጥንቃቄ ዓላማ፣ንባብ ለመማርና ለማወቅ ዓላማ፣ንባብ ለመዝናናት አላማ የሚሉ ናቸው፡፡

### ሀ. ንባብ ለጥንቃቄ

ንባብ ለጥንቃቄ የምናነብበት ጊዜ መኖሩን አለም (2001) እና Wallace (1992) ይገልጻሉ፡፡ በምሳሌ የሚያስረዱት "ቁም" የሚለው የትራፊክ ምልክት ለአንድ የመኪና አሽከርካሪ ምን ማለት እንደሆነ በመግለጽ ነው፡፡ ይህም የመኪና አሽከርካሪው የጽሁፉን መልእክት ተግባራዊ በማድረጉ ህይወቱን ሊያተርፍ ይችላል፡፡ የጽሑፉን መልእክት ተግባራዊ ባለማድረጉ ደግሞ ህይወቱን ሊያጣ ይችላል፡፡ በዚህም መሰረት በንባብ አማካኝነት የሚተላለፉ መልእክቶች በመገንዘብ ራሳችንን ከአደጋ ለመታደግ እንችላለን፡፡

### ለ. ንባብ ለመማርና ለማወቅ

እንደ አለም (2001) ገለጻ "ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚያነቡት አዲስ ነገር ለመማር፣ ለማወቅና ለመገንዘብ ሲሉ ነው"፡፡ የንባብ አላማ በአንባቢ አእምሮ የተያዘን ግልጽ የሆነ አላማ ከግብ ለማድረስ ነው Harmer (2001:200)፡፡ ይህም ስለ አለም ያለን እውቀት እንዲዳብር እገዛ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪ በንባብ አማካኝነት አደዲስ የትምህርት ይዘቶችን ለመረዳት፣ መረጃን ፈልጎ ለማግኘት፣ አካባቢን ይበልጥ ለመገንዘብና እውቀትን ለማስፋት በማንበብ አብዛኛውን ጊዜ እንድንወስድ ያደርገናል፡፡

### ሐ. ንባብ ለመዝናናት

እንደ Wallace (1992:7) ገለጻ ንባብ ለመዝናናት አላማ ሲባል "ንባብን ለንባብነቱ ማንበብ" ነው፡፡ ሰዎች ለመደሰትና ለመዝናናት ሲሉ ያነባሉ፡፡ ለዚህ አላማ የሚውሉ ልቦለድ፣ ግጥም፣ ተውኔት ወዘተ ሰዎች ራሳቸውን የሚያስደስቱበትና የሚያዝናኑበት ነው፡፡ ከዚህም በላይ አንባቢ የሆኑ ሰዎች ለማፍራት በዚህ መልኩ ማንበብን እንዲለማመዱ ማድረግ ይቻላል፡፡

ንባብን ለምን እንደምናነብ ካላወቅን ማንበብ ምንም ፋይዳ የለውም ማለት ይቻላል፡፡ ሁል ጊዜ ንቁ ለመሆን የሚጠቅሙንና መረጃ ይሰጡናል የምንላቸውን መጻህፍት ማንበብ አንዱ አላማን ከማሳካት አንጻር የሚመደብ ነው፡፡ መጻሕፍትን ከማንበብ በፊት መስተዋል ያለበት ነገር ቢኖርለምን አላማ ማንበብ እንዳለብን፣ ስለሚነበበው ነገር ካሉት መረጃ በመነሳት እንድንተገብር ይረዳናል፡፡

የንባብ ትምህርት ዓላማ በጣም ተፈላጊ ከሚባሉት የልምድ አይነቶች አንዱና ዋነኛው ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ይህ ተፈላጊው ልምድ በትምህርት ቤቶች ምን ያህል ተግባራዊ ሆኖዋል? ብለን ስንጠይቅ በዋናነት በአእምሯችን የሚመጡት መምህራን ናቸው፡፡ ለዚህም ተማሪዎች ንባብን ለምደው እንዲያድጉ ከሚያደርጓቸው ስፍራዎች አንዱ ትምህርት ቤት ነው፡፡

### 2.1.3 ማንበብ ለምን ይጠቅማል?

ንባብ ከሰው ልጅ ህይወት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ ይህም ሲባል አንድ ሰው አዲስ እውቀት ለማግኘት ወይም የነበረውን ዕውቀት የበለጠ ለማዳበር፣ ለመደሰት እና ለተለያዩ ጉዳዮች ንባብን ይጠቀምበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአካባቢው ያለውን ነገርና የሚኖርባትን አለም ጠልቆ ለመረዳት ንባብ አይነተኛ መሳሪያ በመሆን ያገለግላል (Davies 1995:5)፡፡

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ንባብ ከሰው ልጅ የእለት ተእለት ተግባራት ጋር ያለው ተዛምዶ እጅጉን የተቀራረበ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ መልኩ ለመምህራኑ እውቀትን ማበልጸጊያና ለሚሰሩበት ሙያ ጥሩ ሞዴል ሲያደርጋቸው፣ ሁለተኛ ቋንቋቸውን ለሚማሩ ተማሪዎች ደግሞ የተለያዩ የባህል ልዩነቶችን ለመገንዘብ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ከራሳቸው ውጭ ያለውን ባህል ለመረዳት ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

ከድረ ገጽ Kozol (no date) የተገኘው መረጃ እንደሚገልጸው፣ ሰዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የንባብን ጥቅም እየተረዱ መጥተዋል፡፡ የሚያነብ ሰው በአንድ ጊዜ ብዙ ነገሮችን ሲያከናውን ይታያል፡፡ ምክንያቱም ይላሉ Kozol ማንበብ ለተለያየ ነገር ጠቃሚ ነው፡፡ ነገር ግን ማንበብ ብቻ የእውቀት ምንጭ ነው ማለት አንችልም፡፡ ለምሳሌ በConcordia University ከተደረገው ጥናት የተገኘው ውጤት

እንደሚያመለክተው ከጥሩ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስቲ የተመረቁ ያለምንም ተጨማሪ ንባብ ጥሩ መምህር ወይም የገንዘብ ሰው ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን አብዛኞዎቹ ታዋቂ ሰዎች ዘውትር ያነባሉ በማለት በምሳሌ አስደግፊው ገልጸዋል፡፡ Kozol (no date) አክለውም የንባብን ጥቅም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን 8 ነጥቦችን አስፍረዋል፡፡

## 1.ንባብ በመሰረቱ አሁን ላለው ህብረተሰብ ጠቃሚ ነው

ከንባብ አላማዎች አንዱ ሰዎች ለጥንቃቄ ወይም ራስን ከአደጋ ለመከላከል በሚል ያነባሉ፡፡ በዚህም የተነሳ አብዛኞዎቹ አዋቂ ሰዎች በመድሀኒት ብልቃጥ ላይ የተጻፈውን ጽሑፍ እንኳን ማንበብ እስኪያቅታቸው የሚደርሱ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ለልጆቻቸውና ለተጠቃሚው ሰው በጣም አስፈሪና አደጋ የሚያደርስ ነው፡፡ ያለእርዳታም የፍላጎትን መተግበር አስቸጋሪ ነው፡፡ የመንገድ ትራፊክ ህጎችን እንዲሁም የማስጠንቀቂያ ጽሑፎችን ያለንባብ መረዳት አስቸጋሪ ነው፡፡

## 2.ስራን ለመፍጠር

አዳዲስ ነገር ለመፍጠር ብዙ ዘገባዎችና አጫጭር ጽሑፎች የግድ ይነበባሉ፡፡ መጥፎ የሆነ የንባብ ልምድ ሌላ ስራ የምንሰራበትን ጊዜ በጣም ያባክናል፡፡ ሰዎች ያለምንም ጥሩ የንባብ ልምድ ምን መስራት እንዳለባቸው የመረዳት አቅም የላቸውም፡፡ ስለዚህ አላማን መሰረት ያደረገ ንባብ የምንፈልገውን ያሳካልናል፡፡

## 3.ንባብ አዕምሮን ለማሳደግ

የተጻፉ ነገሮችን ማንበብ አንዱ አእምሮን ማሳደጊያ ዘዴ ነው፡፡ መምህራን ህጻናትን ለማስተማር ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲሁም የማዳመጥ፣ የመናገርና እና የመጻፍ ችሎታቸውን በተጨማሪ  ለማሳደግ ይችላሉ፡፡ አብዛኞቹ መናገርን ሲወዱ ጥቂቶቹ ግን ማዳመጥን ይመርጣሉ፡፡ ባጠቃላይ ንባብ ለሕጻናትም ሆነ ለአዋቂዎች አንድ ነገር ምን ማለት እንደሆነ ለማወቅ ይረዳቸዋል፡፡

## 4.አዳዲስ እውቀቶችን እንዴት ማግኘት እንዳለብን ለመገንዘብ

መጸሕፍት፣ መጽሄትና ድረ-ገጽ ዋና ዋና የመማሪያ መንገዶች በመሆን የማንበብ ልምድንና ያነበብነውን ለመረዳት ይጠቅማሉ፡፡ እንዴት ማንበብ እንዳለበት

የሚያውቅ ሰው ሕይወቱን በብዙ አቅጣጫ ማሰማራት ይችላል፡፡ በሕይወት ዘመናችን ስንኖር ብዙ መረጃ ልናገኝ እንችላለን፣ ከነዚህም ውስጥ ንባብ ዋነኛው መረጃ ማግኛ ዘዴ ነው፡፡

## 5.ማስተዋልን ያሳድጋል

የኮምፒውተር እና የቴሌቭዥን ጌሞችን መጫወት በጣም ደስተኛ ሊያደርገን ይችላል፡፡ የዚህ ደስታ የመጣው ማሰብ በማያስፈልገው እንቅስቃሴ ነው፡፡ ንባብ ግን ከዚህ በተለየ መልኩ እናየዋለን፡፡ ሰዎች በንባብ ስለብዙ አለም ወይም ከዚያ በላይ አልፈው ሊያውቁ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡-በንባብ ጀብደኛ፣ ጥሩ ንጉስ ወይም ብልህተኛ…ወዘተ መሆን ይቻላል፡፡ የማያነቡ ግን እነዚህን ነገሮች የማግኘት እድላቸው አናሳ ነው፡፡

## 6. ንባብ ለሰዎች የፈጠራን ችሎታ ይጨምራል

መምህራን ለተማሪዎች ንባብን ስናነብላቸው በየመሀሉ ለጥቂት ጊዜ ንባቡን በማቋረጥ በቀጣይነት ምን እንደሚከሰት ታሪኩን እንዲገምቱ መጠየቅ ነው፡፡ ጨርሰን አንብበንላቸውም ከሆነ ስለታሪኩ አጨራረስ እንጠይቃቸው፣መሻሻል ያለበት ነገሮች እንዳሉና እንዲናገሩ እድል በመስጠት ታሪኩን ወደፊት ከሆነ ደግሞ ሌላ የታሪክ መጻህፍትን በማምጣት እንዲያነቡ ካበረታታናቸው ወደ ጥሩ አንባቢነት ይለወጣሉ፡፡

## 7.የግል እቅድን ለማሳካት ንባብ መሰረታዊ ነገር ነው

የማያነቡና ደካማ አንባቢያን አልፎ አልፎ ለራሳቸው ደካማ የሆነ ምርጫና ችሎታ ነው ያላቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ ከሰዎች ገለልተኛ ይሆናሉ፡፡ ለራሱ በሚሰጠው የተሳሳተ ግምት ከአዋቂ ሰዎች ጋር እንዳይቀላቀል ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ እነኚህ የማያነቡ ሰዎች ውጫዊ የባህርይ ችግር ስለሚታይባቸው በተለያየ የትምህርት ዘርፎች መሳተፍ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ስለማያነቡ አያስተውሉም፡፡

## 8.ጥሩ የንባብ ልምድ መኖር የፊደል እና የቃላት ችሎታን ያሳድጋል

ተማሪዎችን በምናስተምርበት ጊዜ በድምጽ ብቻ ያለን ፊደል የማናስተምር ከሆነ ፊደላቱን ማስተማር ቀላል ይሆናል፡፡ በተጨማሪ ንባብ የቃላት ችሎታን ያሳድጋል፡፡ አዳዲስ ቃላትን በምናገኝበት ጊዜ በአእምሯችን እንመዘግባቸውና እንጠቀምባቸዋለን፡፡ እዚህ ላይ ቃላት በተለያየ ምንባብ ውስጥ በመግባት የተለያየ ግንዛቤ ስለሚፈጥሩልን በመዝገበ ቃላት ከምናውቃቸው ተጨማሪ ትርጉም እንዳላቸው ማወቅ እንችላለን፡፡

የንባብ ጥቅም ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች እና ከቃላት እስከ ንግግር እንዲሁም ጽሑፍ ድረስ መሰረት የሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም ንባብ በትምህርት ዘርፍ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይታመናል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዋናው በማዳመጥና በንግግር የማይገኙትን የህይወት ገጠመኞች እንድናገኝ ማስቻሉ ነው፡፡ ባጠቃላይ ግን ንባብ አዲስ መረጃን ለማግኘትም ሆነ ክሂሎቹን ለማዳበር መሰረት ሊሆን እንደሚችል Williams (1984:46) የሚከተሉትን ነጥቦች በመዘርዘር ይገልፃሉ፡፡ Nuttall (1982:3) እና Grellet (1981:46) እነዚህን ነጥቦች ይጋራሉ፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ተማሪዎች በማዳመጥና በመናገር ያላገኙትን ነገር በንባብ አግኝተው ቋንቋውን ይበልጥ እንዲለማመዱ እድል ይሰጣቸዋል፤
- አንድን ምንባብ አንብበው ምን ማስተላለፍ እንደፈለገ በቀላሉ መግለጽ ያስችላቸዋል፤
- ከቋንቋ ትምህርት በተጨማሪ ተማሪዎች አካባቢያቸውን፣ሀገራቸውን እንዲሁም በአለም ዙሪያ ያሉ ነገሮችን እንዲያውቁ ያስችላቸዋል፤
- ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ አንብበው በሚያደርጉት ውይይት በተጓዳኝ የንግግር ክሂልን ለመማር ያስችላል፤
- ተማሪዎች የምንባቡን ሀሳብ ተረድተው የሚፈልጉትን መረጃ ከምንባቡ ውስጥ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ለመማር ይረዳቸዋል፤
- ከንባብ ክሂል ባሻገር የጽሕፈት፣ የቃላት፣ የሰዋስው፣ ወዘተ.እውቀታቸውን ለማሳደግ ይረዳል፤

- ተማሪዎች ከተለያዩ ገጠመኞች ጋር እንዲተዋወቁ እና እንዲዝናኑ ያስችላቸዋል፤
- ተማሪዎች መሰረታዊ የሆነ የአንብቦ መረዳት ክህሎት እንዲኖራቸው ያስችላል፤

በመሆኑም ተማሪው ጥሩ የንባብ ክህሎትና ፍላጎት እንዲኖረው ከማስቻል ባለፈ፣ ካለው አዕምሯዊና ስነ-ልቦናዊ ጠቀሜታ አኳያ የንባብ ትምህርት በመምህሩም ሆነ በተማሪዎች ተገቢ ትኩረት አግኝቶ በመማሪያ ክፍል ውስጥ መከናወን አለበት፡፡ መምህሩ ለተማሪው ተፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ ከተማሪው በላቀ ሁኔታ የንባብ ልምድ ያካበተ ሊሆን ይገባል፡፡ የማንበብ ልምድ የሌለው መምህር ተማሪዎችን በተፈለገው መንገድ የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው አያደርግም (አለም 2001)፡፡

ይህን አስመልክቶ የመምህራኑን የንባብ ልምድ ማዳበር የሚችልበትን አቅጣጫ ከማስቀደማችን በፊት ስለ ንባብ ባህል ወይም ልምድ ምንነት እንመልከት፡፡

## 2.1.5 የንባብ ባህል ምንድነው?

ማንባብ መረጃ የመቀበያ ክሂል ነው፡፡ ቢሆንም የተለያዩ ፅሑፎችን በምናነብበት ወቅት መረጃን የመቀበል አቅማችን ሊለያይ ይችላል፡፡ ምክንያቱም አንድን ፅሁፍ አንብቦ ለመረዳት የንባብ ልምድ ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ይህንን አስመልክቶ የሚከተለው ጥቀስ ይገልጻል፤

> *ስለ ንባብ ልምድ ከማንሳታችን በፊት በቅድሚያ ልምድ ምንድነው?*[1] *የሚለውን ጥያቄ ብንመልስ ተገቢ ይሆናል፡፡ ልምድ ወደዚህ ዓለም ስንመጣ ይዘን የምንመጣውን ተፈጥሮ የምናሻሽልበት፣የምናሳድግበት፣ የምናዳብርበት፣ አብሮን የነበረ አሁንም ያለ ወደፊትም አብሮን የሚኖር፤ ከተግባርና ከተሳትፎ የሚመነጭ ነው* (አለም፣ 2001፡65) ፡፡

የንባብ ባህል ሲባል ደግሞ ጠቅለል ባለ መልኩ አብዛኛውን የሕብረተሰብ ክፍል የሚሸፍነው ጊዜውን በሚታይ መንገድ ለንባብ መስጠቱና የዘውትር ልምዱ ሲሆን

---

1 የንባብ ልምድ ማለት በተደጋጋሚ የሚከናወን፣በሆነ አጋጣሚ የሆነ ደረጃ ላይ ደርሶ ሊቀር የሚችል ነው፡፡

[2](ምህረቱ፤1999፡154) ነው፡፡ በሀገራችን ብዙ ሰዎች የሚታዩት ሲያነቡ ሳይሆን ሌሎች ነገሮችን ሲያከናውኑ ነው፡፡ ሰው በተለያየ ቦታ በእጁ የሚነበቡ ነገሮች ይዞ ሲያነብ ቢታይ በተወሰነና በሚያሳምን መልኩ የንባብ ሕይወት ወደ የሰው ሕይወት ሰርጾ እየገባ እንደሆነ ለመደምደም የሚያስችለን ይሆናል፡፡

ይህ ከላይ የተገለጸው ሀሳብ አንድ ሰው አንድን ነገር ደጋግሞ ሲያደርግ ካየን ለዚያ ነገር ምን ያህል ትኩረት እንደሚሰጠው እንረዳለን፡፡ በዚህ አይነት ንባብ አንድ ሰው ፍላጎት እስካለው ድረስ ሁልጊዜ ሊያደርግ የሚችልና ማቆሚያ የሌለው ነው፡፡ ንባብ ባህላችን ሆነ ማለት ግን ለትምህርት የምናደርገው ንባብ ወይም በአንድ ለተወሰነ ጊዜ ለሆነ ዓላማ ብቻ ለማስፈጸም የሚደረግን የንባብ ርብርቦሽን ከግምት ውሰጥ ማስገባት አይደለም፡፡

ባጠቃላይ የንባብ ባህል ወይም ልምድ ማለት የሰዋስው ችሎታን፣ የቃላትን ፍቺ ማወቅ፣ የዓረፍተ ነገሮች የቃላትንና ድምጾችን በትክክል ማንበብ መቻል እንደሆነ Omaggio (1983) ገልጸዋል፡፡

## 2.1.6 የንባብ ባህል መገለጫዎች

አንድ ሰው የሚያነበውን መጽሐፍ መርጦ ያለምንም ቀስቃሽ በራሱ ፍላጎትና በፈለገው ጊዜ ማንበብ ሲጀምር የማንበብ ልምድ አለው ማለት እንችላለን፡፡ በዚህ አይነት ማንበብ የለመደ አንባቢ ጥሩና የተዋጣለት አንባቢ፤ንባቡም የፍላጎቱን ሊያደርስለት የሚችል እንደሚሆን እሙን ነው (አለም፣ 2001፡65፤ Charles 1985:207) ፡፡ አለም (2001፡66) አክለውም እንዲህ ያለውን ንባብ ደግሞ ከዚህ እንደሚከተለው ባለው ሁኔታ ገልጸውታል፡-

[2] የንባብ ባህል ማለት ደግሞ አብዛኛው ማህበረሰብ ሲተገብረው የሚታይና ሊቀር የማይችል፣ ለምሳሌ አንድ ሰው በቀን የተወሰነ ሰአት ካላነበበ አእምሮው እረፍት የማያገኝ ከሆነ ማንበብ ባህል ደረጃ ደርሷል እንላለን፡፡ በርግጥ ልምድ እየዳበረ ሲሄድ ባህል ወደ መሆን ሊሸጋገር ይችላል፡፡ ጥናቱም ትኩረት የሚያደርገው የመምህራኑን የንባብ ባህል ነው፡፡ (ከተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች ተጨምቀው የተወሰዱ)

## ሀ. ከፍተኛ የንባብ ፍላጎት

የንባብ ልምድ ያዳበረ ሰው በእጆቹ የሚገቡትን ለደረጃውና ለእድሜው የሚመጥኑትን መጽሐፎች ፣ጋዜጦች ፣መጽሔቶች፣ ወዘተ ገዝቶም ሆነ ተውሶ ሲያነብ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ካነበቡም በኋላ ያነበቡትን ቁም ነገር ለጓደኞቻቸው ወይም ለወላጆቻቸው ለማጋራት ፍላጎቱ ይኖራቸዋል፡፡

## ለ. የንባብ ፍጥነት

የማንበብ ልምድ ያዳበረ የሚባለው ሰው በፍጥነት ማንበብ ይችላል፡፡ በፍጥነት ማንበብ ይችላል ለሚለው እንደተደረሰበት ፈጣን አንባቢ በአፍ መፍቻ ቋንቋው 600 ቃላትን በደቂቃ ያነባል፡፡

## ሐ.የንባብ ስልትን መቀያየር ስለመቻል

የንባብ ልምድ ያዳበረ ሰው በሚያነብበት ጊዜ እንደንባቡ ዓላማና እንደሚያነበው ቁም ነገር የአነባብ ስልቱን መቀያየር የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም በቀላሉ ከግርፍ ወደ አሰሳ ንባብ፣ ከሰፊ ወደ ጥልቅ ንባብ ወይም በተቃራኒው እንዳስፈላጊነቱ እያለዋወጠ ማንበብ ይችላል፡፡ በዚህ አይነት የሚያነብ ሰው የማንበብ ችሎታው የላቀ ነው፡፡

## መ. ድምፅን ከፍ አድርጎ በእርጋታ ማንበብ መቻል

የማንበብ ልምድ ያዳበረ ሰው በለሆሳስ ከሚደረገው ንባብ በተጨማሪም በጮክታ ንባብም ጥሩ አቀራረብ ያሳያል፡፡ እንዲህ አይነቱ አንባቢ ድምጹን መጥኖና ወደ አድማጮችም አልፎ አልፎ እየተመለከተ በእርጋታ ማንበብ ይችላል፡፡

## ሠ. አስደሳች ንባብ

የማንበብ ልምድ ያዳበረ አንባቢ በሚያነብበት ጊዜ ፊቱ ላይ የመጨነቅ ስሜት አይታይም፡፡ እንዲህ አይነቱ አንባቢ በለሆሳስ የንባብ ወቅት ስሜቱ ዘና ብሎ ይታያል፡፡

ከፍ ሲል የዘረዘሩት የማንበብ ልምድ ያዳበረ ሰው ወይም የተዋጣለት አንባቢ የሚያሳያቸውን ባህሪያት ያመላክታሉ፡፡ታድያ እንዲህ አይነቱ አንባቢ ለመፍጠር ምን መደረግ አለበት?

### 2.1.7 በንባብ ባህል ላይ ያሉ ተፅዕኖዎች

የንባብ ባህል ወይም ልምድ ከሰው ወደ ሰው ይለያያል፡፡ ለልዩነት መፈጠር መነሻ የሚሆኑና አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነሱም የሚኖሩበት አካባቢ፣ ውስጣዊ የስሜት ሁኔታ፣ማህበራዊ ፍላጎት እና ስነ-ልቦናዊ ዝንባሌ ናቸው (Carbo 1991:2)፡፡

እንደ ምህረቱ (1999) ገለጻ ሀገራችን ለንባብ ባህል መዳበር የሚሰጠው ግምት የተሳሳተ በመሆኑ የጊዜ አጠቃቀማችን በጣም የተመናመነ ነው፡፡ ሌላው የንባብ ባህል እንዳይዳብር ምክንያት የሆነው ባህሉ እራሱ ማህበራዊ ህይወትን የሚያጠናክር በመሆኑ ግለኝነትን ወይም መለየትን አያበረታታም፡፡ ንባብ ደግሞ በግል የሚሠራ ሥራ ነው፡፡ በዚህ አይነት መጽሐፍን ለማንበብ ፍላጎት እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ ሰዎች ለንባብ ያላቸው አመለካከትም የወረደ ያደርገዋል፡፡

ሌላው የንባብ ባህል እንዳይዳብር ከሚያደርጉ ችግሮች መካከል የንባብ ፍላጎት አለመኖር አንዱና ትልቁ መሰረት ነው፡፡ ስለዚህ የንባብ ፍላጎት ያለመኖር፣ የብዙ ኢትዮጵያውያን አስተዳደግ፣ የቤተ መፃሕፍት አለመኖርና አለመስፋፋት፣ የማህበረሰቡ አመለካከት ዝቅተኛ መሆን ወዘተ. የንባብ ባህል እንዳይዳብር ከሚያደርጉ ነጥቦች መካከል እንደሚጠቀሱ አለም (2001፡67) ገልጸዋል፡፡

ከላይ የተገለጹትና ሌሎችም ለንባብ ባህል አለመጎልበት የየራሳቸው ተጽእኖ አላቸው፡፡ ይህም ተጽእኖ በመምህራን የንባብ ባህል ላይ የራሱን አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ታዲያ የመምህራኑን የንባብ ባህል ለማሻሻል ምን መደረግ አለበት? ለሚለው ጥያቄ ከዚህ ቀጥሎ ምሁራኑ መልስ ይሰጣሉ፡፡

### 2.1.8 የንባብ ባህል ለማጎልበት የሚያግዙ ነጥቦች

የተለያዩ ምሁራን ስለንባብ ባህል የሚዳብርበትን መንገድ ገልጸዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ከድረ-ገጽ Maugham (no date) እንደተገኘው የንበብ ልምድን እንዲህ ብለዋል፤ "የግል የንባብ ባህልን ማዳበር በጥቅሉ ወደ ሕይወት መልካም ነገር መጠጋት ነው፡፡" ትክክለኛ መጽሐፍ እርካታን ይሰጣል፡፡ ምክንያቱም ከህይወታችን ጎን ለጎን የተለያዩ ገጸ-ባህሪያትን ግልጽ በማድረግ ያስደስተናል፡፡

በመጀመሪያ ልናነብ የምንመርጠው መጻሕፍት ዓላማችንን ለማሳካት እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፤ በሌላ መልኩ በጣም የሚያስጠላና የሚሰለች መጻሕፍትን ልናነብ እንችላለን እነኚህ ሁኔታዎች ብዙ ጊዜ ሊያጋጥሙን ይችላሉ፡፡ መረዳት ያለብን ነገር ፍላጎታችንን ሊያሟሉ የሚችሉ መጻሕፍት ማንበብ እንዳለብን ነው፡፡ ለንባብ ባህል ማደግ ትልቁ ነገር ንባብን የእለት ተዕለት ወይም የዘውትር ልምድ ማድረግ ነው፡፡ ራስን ለንባብ ሕይወት መስጠት ወይም ባህል ማድረግ ቀላል ነገር አይደለም፡፡ የንባብ ሕይወት የሚጠይቀን በርካታ ነገር አለና፡፡ ከጊዜ አጠቃቀም አንስቶ እስከ የሚነበቡ ጽሑፎች ግገር ድረስ የሚያስከፍለን ዋጋ ቀላል አይሆንም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሚከተሉት ነጥቦች የማንበብ ባህል ወይም ልምድ እንዲኖረን ያደርገናል፡፡

- **ለማንበብ ማቀድ**

በአንድ አመት ውስጥ ቢያንስ 50 መጻህፍትን ወይም ከዚያ በላይ እናነባለን ብለን ማቀድ አለብን:: ያቀድነውን ለመፈጸም መጣርና በእቅዳችን መሰረት አንብበን ከሆነ ደስታን ይሰጠናል፤ይህን ካላደረግንና ካላሳካን ግን በፍጥነት ለማሳካት መጣር አለብን (Maugham no date)፡፡

ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ተግባራዊ ለማድረግም በየቀኑ ከ5-10 ደቂቃ ያህል የንባብ ጊዜ መወሰን አለብን፡፡ ይህ ሰአት በየቀኑ ለማንበብ ያለንን ፍላጎት እንዲቀሰቅስ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ በቁርስና በምሳ ሰአት እንዲሁም ከተቻለ በእራት ሰአት እየበላን ማንበብ እና ሁልጊዜ ሰአታችንን በመወሰን በቀን 4 ጊዜ ቢያንስ ለ10 ደቂቃ ብናነብ በቀን 40 ደቂቃ ማንበብ እንችላለን፡፡ ይህ ማለት ትልቅ የንባብ

ጅማሬ ሊሆነን ይችላል (Maugham no date) ፡፡ በመሆኑም ለንባብ ባህል ማከናወን ቁልፍ የሆነ ነገር ቢኖር ጊዜን በአግባቡ መጠቀም መቻል ነው፡፡ ለሌሎች ነገሮች ጊዜ እንደሚኖረን ሁሉ፣ ለንባብም ጊዜ መመደብ ይኖርብናል፡፡ በአብዛኛው ማህበረሰብ ውስጥ ለንባብ ጊዜ ሰጥተው ማንበብ እንደኪሳራ ያዩታል፡፡ የጊዜ አጠቃቀማችንን ማወቅ ፕሮግራማችንን በአግባቡ ለማከናወን ወሳኝ ሚና ያለው ክህሎት ነው፡፡ በዚህ መንገድ ተጠቅመን የንባብ ባህላችንን እንዲያድግ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ተገቢ ብቻም ሳይሆን ወሳኝ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ንባብ የሚጎለብትበት ነጥብ እንደ አለም (2001) እና ምህረቱ (1999) ገለጻ የንባብ ባህል ሊዳብር የሚችለው ብቸኛው መንገድ የትምህርት መስፋፋት መሆኑ ሐቅ እንኳ ቢሆን፣ የንባብ ልምድ ያለው ለመፍጠር፣ ትምህርት ቤት፣ መምህራን፣ ወላጆች፣ ማህበረሰቡ፣ ለንባብ ያለውን አመለካከት መቀየር ሲቻል ነው፡፡ ይህ መሆን የሚችለው "መምህሩም የራሱን የንባብ ባህል አዳብሮ የማንበብ ልምድ ያለው አንባቢ መፍጠር እንዲቻል ጥረት ማድረግ ያለበት ከዝቅተኛ ክፍል ተማሪዎች ጀምሮ ነው" (አለም ፣2001፡67)፡፡ ከዚህ ጋር አያይዘውም የንባብ ባህል አዳብሮ፣ የማንበብ ልምድ ያለው አንባቢ ለመፍጠር የሚከተለውን ነጥብ አስፍረዋል፡፡

- **ሁልጊዜ መጽሐፍ መያዝ**

አንድ ሾፌር ከቤት ሲወጣ የመንጃ ፈቃድ እንደማይለየው ሁሉ በምንሄድበት ቦታ ሁሉ ከእጃችን መጻሕፍት መለየት የለበትም፡፡ ለምሳሌ፡-ወደስራ ስንሄድ፣ ወደቀጠሮ ቦታ ወደፓርቲ የትም ቢሆን መጻሕፍት ከእኛ መለየት የለባቸውም፡፡ ከተቻለና ጊዜ ካለን ሀኪም ቤት ተራ እየጠበቅን እንኳን ብናነብ ጊዜውን በአግባቡ ልንጠቀም እንችላለን፡፡

- **ማስታወሻ ማዘጋጀት**

ማንበብ የምንፈልጋቸውን መጻህፍት መመዝገብ የእለት ተእለት ስራችን በማድረግ፣ በግል ማስታወሻ መያዝ ነው፡፡ ጥሩ መጻህፍት ናቸው ተብለው ሲነገሩ በማናቸውም ቦታ የሰማናቸውን ሁሉ በማስታወሻችን መመዝገብ ይኖርብናል፡፡ መጻሕፍትን

በምናነብበት ጊዜ ያነበብነውን ነገር በፋይል አደራጅተን መያዝ፣ መልእክታቸውን በምንፈልግበት ጊዜ ከያዝነው በቂ መረጃ ወይም መልስ ስለሚሆነን ይረዳናል፡፡ በተጨማሪም ስናነብ ቀልባችንን የሳቡ አባባሎች፣ ጸሐፊው የተጠቀመባቸውን ምርጥ ቃላት /ቋንቋ/ በማስታወሻ መያዝ አለብን፡፡ ይህንን በማስመልከት Harmer (1991፡17) እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ፤ "ሲያነቡ በዚያው ቅጽበት ማስታወሻ ወይም በሚያነቡት ጽሑፍ ላይ የተመሰረተ ሀሳብ ቢጽፉ ጥሩ የማንበብ ችሎታ ይኖርዎታል፡፡" ከዚህ ጽሑፍ እንደምንረዳው በምናነበው ጽሑፍ ላይ የተመሰረተ ሀሳብ የጸሀፊውን የአጻጻፍ ስልት ለማወቅ ይረዳናል፡፡

- **ፀጥ ያለ ቦታ መፈለግ**

የማንበቢያ ቦታ እንደየፍላጎቱ ከሰው ወደሰው ይለያያል፡፡ ነገር ግን በቤት ውስጥ ምቹ በሆነ ቦታ በመቀመጥ ማንበብ ይኖርብናል፡፡ ምንአልባት ለመተኛት ፈልገን ካልሆነ በስተቀር ለምንም የሚረብሸን ነገር ለምሳሌ፡-ቴሌቭዥን፣የሙዚቃ ድምጽና ቤተሰብ ያለበት እንዳይሆን በማድረግ ሀሳባችንን በመሰብሰብ የመጽሀፉን ሀሳብ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ብዙ መጻሕፍትን የምናነብ ከሆነ የቴሌቭዥንና ድረ-ገጽ አጠቃቀም መቀነስ አለብን፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው የምንጠቀም ከሆነ የማንበብ ጊዜን መፍጠር ስለሚስቸግረን፣ አጠቃቀማችንን መቀነስ ይኖርብናል፡፡ እነዚህን በአግባቡ ከፈጸምን ጥሩ የንባብ ጊዜንና ስፍራ እንፈጥራለን፡፡

- **የቀልድ መጻሕፍትን አንብቦ መጨረስ**

ሊማርኩ የሚችሉ መጻሕፍት ፈልጎ በማንበብ ጭብጡን መያዝ ነው፡፡ የምናነባቸው ነገሮች የስነ-ጽሑፍ ወይም የፈጠራ ጽሑፍ ላይሆኑ ይችላሉ፣ የቀልድ ጽሑፎችን ማንበብ የተለያዩ ዕሑፎችን እንድናነብ ያደርጉናል፡፡ ይህንንም በማድረግ ችሎታችንን ካዳበርን በኋላ ከበድ ያሉ መጻሕፍትን ወደማንበብ ደረጃ ቀስ በቀስ መሸጋገር ይቻላል፡፡ እንደ Maugham, (no date) ገለጻ የቀልድ መጻህፍት እንደጻፉት stephen king,John Grisham,Tom Clancy,Robert Ludlum እና ሌሎችም ጸሐፍቶች ታዋቂ የሆኑበት የራሳቸውን ምክንያት ብንጠይቃቸው ይነግሩናል፡፡ ስለዚህ ይህንን መሠረት አድርገን የንባብ ባህል የማዳበር ደረጃ በሂደት እንደሚመጣ በማወቅ ደረጃውን ጠብቆ ማንበብና ተግባራዊ ማድረግ አለብን፡፡

- **የቡድን ንባብ ማደፋፈር**

የንባብ ፍላጎት ማሳደጊያ መንገዶች መካከል የቡድን ንባብ ማጠናከር ነው፡፡ መምህራን ለማስተማር የሚያነቡት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ መጻሕፍትን ማንበብ እንዳለባቸው ሁሉ ተማሪዎቹንም ክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ በቡድን የሚያነቡበትን በቀላሉ ማመቻቸት ይችላሉ (ዓለም 2001፡68)፡፡

በእንዲህ አይነቱ የቡድን ንባብ አንድን ጽሑፍ በጋራ አንብበው በመወያየት ያነበቡትን በሚገባ እንዲረዱና የንባብ ዘዴ ወይም ብልሀት እንዲለዋወጡም ማድረግ ይቻላል፤የቡድን ንባብ በተጨማሪ ብዙ ተማሪዎችን በቡድን ከፋፍሎ እያንዳንዱን ቡድን በቀላሉ ለመከታተል ያስችላል፡፡

- **በመጻሕፍት ምርጫ ላይ እገዛና ጥቆማ በማድረግ**

አንድ መምህር የንባብ ልምድ ካለው በክፍል ውስጥ ለማስተማሪያነት የሚጠቀምበት ዘዴ ለተማሪዎቹ እገዛ ያደርጋል፡፡ ይህንን አስመልክተው መምህራን የተማሪዎቹ የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ብሎም የማንበብ ልምድ ማዳበር እንዲችሉ ከፍላጎታቸውና ከደረጃቸው ጋር አብረው የሚሄዱትን ለይተው መምረጥና መጠቆም ይገባል፡፡ ይህም ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ እንደ መፅሔት፣ጋዜጣ ፣መጽሐፍ እና ያዘጋጁትን ጽሑፍ ለንባብ ማስተማሪያነት እንደ ምንጭነት ቢጠቀሙ የንባብ ትምህርቱ የተሻለ ሊሆን እንደሚችል Celce-murcia (1991:20) እና አለም (2001፡67) ይገልጻሉ፡፡ አለም (2001፡67) አክለውም ተማሪዎቹ በሚያደርጉት የመጽሐፍ ምርጫ ከዚህ የሚከተሉትን ነጥቦች መሰረት አድርገው ተማሪዎቹን መርዳት ይገባል፡፡

- የትኛው መጽሐፍ ከተማሪው እድሜና ችሎታ ጋር የተመጣጠነ ነው?
- የትኛው መጽሐፍ ከተማሪው ባህልና አካባቢ ጋር አብሮ ሊሄድ ይችላል?
- ተማሪው በጉጉት ሊያነበው የሚችለውና ከፍላጎቱ ጋር አብሮ የሚሄድ መጽሐፍ የትኛው ነው?
- በቅርቡ ታትሞ የወጣውና ያልተሰለቸ ይዘት ያዘለው የትኛው መጽሐፍ ነው?

የማንበብ ልምድ ያለው መምህር እነዚህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በአእምሮው በመያዝ ተማሪውን በመጽሐፍ ምርጫ ሊያግዘው ይገባል፡፡ መምህሩ ለተማሪው የማንበብ ፍላጎት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጣሪ ናቸው፡፡ ተፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ እንዲችል ከተማሪው የላቀ የንባብ ልምድ ያካበተ ሊሆን ይገባል፡፡ የማንበብ ልማድ ያለው መምህር ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ነጥቦች መሰረት አድርጎ ተማሪዎቹን በሚፈልገው መንገድ ማገዝ ይችላል፡፡

የንባብ ባህል ማዳበር ከንባብ ትምህርት ዓላማ ማሳደግ ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ ዓይነቱ ልማድ እንዲበለፅግ ከተፈለገ በመምህራንም ሆነ በሌሎች ከንባብ ጋር ያላቸው ቀረቤታ የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ እንደሚገባ Smith (1997:29) ገልጸዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ሰዎች ሁልጊዜ ወደንባብ መቅረብ እንዳለባቸው ነው፡፡ ወደ ንባብ በቀረቡ ቁጥር ለንባብ የሚጠቀሙበት ጊዜ እየሰፋ ይመጣል፡፡ የሚመድቡት ጊዜ ሲሰፋና የሚያነቡትም መፅሐፍ፣መፅሔት፣ጋዜጣ ወዘተ.በአይነትና በቁጥር እየጨመረ ሲመጣ የንባብ ባህላቸውን አዳብረዋል ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

በተጨማሪም ደረጀ (2002፡76) Reutzel and Cooter (1999፡11)ን ጠቅሰው የንባብን ልምድ ማዳበር የሚያመጣውን ለውጥ እንዲህ በማለት ገልጸዋል፡-

> *የተካነ አንባቢ የቀረበለትን ጽሑፍ መረዳት ብቻ ሳይሆን አስተሳሰቡን ለማስፋፋት ይጠቀምበታል፤...በንባብ ክሂሎት የመበልጸግ ሂደት ሕይወትን ሙሉ አብሮ የሚጓዝ ነው፡፡ ወደ ተካነ አንባቢነት የሚደረገው ጉዞ ከተለመዱ የሕይወት ተሞክሮዎችና ከተካበተ እውቀት ይበልጥ እየረቀቀና እየጠለቀ የሚመራ ሂደት ነው፡፡*

ባጠቃላይ የመምህራን የንባብ ልምድ ተጽእኖ ተማሪዎቻቸውን ለንባብ የሚቀሰቅስበት ዘዴ ጋር ይያያዛል፡፡ የMcKool & Gespass (2009) ጥናት እንደሚጠቁመው ንባብን ለመዝናናት የሚያነቡ መምህራንና ተማሪዎቻቸውን እንዲያነቡ የሚያነቃቁ መምህራን መካከል ልዩነት የለም፡፡ እንደሁም ለመደሰትና ለእውነት የሚያነቡ መምህራን ሁልጊዜ ተማሪዎቻቸውን ያነቃቃሉ፡፡

Kozol (no date) ጠቅለል ባለ መንገድ ሲገልጹ የማያነቡ መምህራንን 3 ዋና ዋና መንገዶችን በመጠቀም የንባብ ፍላጎት እንዲኖራቸው ማድረግ ይቻላል፡፡

1.መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ

2.መጻሕፍትና ጋዜጦችን በማንበብ

3.ተማሪዎችን በንባብ መርዳት ናቸው፡፡

## 2.1.9 የአንባብያን አይነቶችና ባህሪያት

Conley (1992፣69) ጠቅለል ያለ ባህሪያትን በማየት አንባቢያን ብቁና ብቁ ያልሆኑ በሚሉ ሁለት ክፍሎች ይመድባሉ፡፡ እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር ቢኖር ብቁ የሆኑ ወይም ያልሆኑ ተብለው በአንድ ወይም በሌላ ክፍል የሚመደቡት አንባቢያን በመካከላቸው በጋራ የሚያሳዩዋቸው ጉልህ ባህሪያት ውጭ የተወሰነ ልዩነት አይታይም ማለት አይደለም፡፡ ከዚህ በታች ብቁ የሆኑና ብቁ ያልሆኑ አንባብያን አይነቶችና አበይት ባህሪያት በተናጥል በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 2.1.9.1 ብቁ የሆኑ አንባብያን

የጽሑፉን መሰረታዊ ሀሳብ ይበልጥ ለመረዳት ጽሑፉን የመገምገምና በዚያው ዙሪያ የራሳቸውን ጥያቄ እያነሱ ምላሽ የመስጠት ልምድ አላቸው፡፡ Millan (1991፣35) ሲያስረዱ "ብቁ አንባብያን ሀሳባቸውን በራሳቸው አባባል ለመግለጽ ይሞክራሉ፣ ከጽሁፉም ውጭ የሆኑ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ"ይላሉ፡፡ ይህም ማለት አንባብያኑ ከጽሑፉ አውዳዊ ፍቺ ውስጥ ያለውን ትርጉምን ያስተውላሉ፡፡

ብቁ የሆኑ አንባብያን አውዳዊ ጥቆማቸውንና የግል የህይወት ልምዳቸውን እንዲሁም እውቀታቸውን መሰረት በማድረግ አንድን ጽሑፍ ሙሉ በሙሉ ከማንበባቸው በፊት ርእሶቹን በመቃኘት ስለአጠቃላይ መልእክቱ የመተንበይ ልምድ አላቸው፣ ትንበያቸውም ትክክል መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ስለሚገፋፉ ጽሑፉን ፈጥነው ማንበብ ይያያዙታል (Silberstein 1994)፡፡

ከዚህም ሌላ ብቁ አንባብያን የዳበረ ልምዳቸውን መሰረት በማድረግ የሚያነቡት ጽሑፍ አንዳንድ ጉድለቶችና ስህተቶች ካሉት አሟልተውና አርመው የማንበብ ባህሪ አላቸው (May 1990:12)፡፡

በአጠቃላይ ብቁ አንባብያን ቀደም ሲል ካነበቡት ወይም ካለፉ ልምድ፣ ትምህርትና የሕይወት ገጠመኝ በመነሳት ከቀረበው ጽሑፍ ባሻገር ጉዳዩን በጥልቀት መመልከት፣ትንታኔ መስጠት የሚችሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም አንባቢው ከተጻፈው ጉዳይ ተነስቶ የራሱን ፍቺ፣ ሐሳብና አስተያየት የመስጠት ችሎታውን ማዳበር የሚችል መሆኑን Niles (1972) ይገልጻሉ፡፡

## 2.1.9.2 ብቁ ያልሆኑ አንባብያን

ብቁ ያልሆኑ አንባቢያን በግል ንባብ ወቅት በጸጥታ ከማንበብ ይልቅ በጮክታ ሲያነቡ ይታያል፡፡ ሌላው የሚታይባቸው ባህሪያት ብቁ ያልሆኑ አንባብያን ካላቸው አነስተኛ የንባብ ልምድ የተነሳ ትክክለኛ የአነባበብ ስልትን ተከትለው ስለማያነቡ ጊዜያቸውን በከንቱ ከማጥፋታቸው በተጨማሪ የማንበብ ልምዳቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ እነዚህ አንባብያን አንድን ጽሁፍ በሚያነቡበት ጊዜ በጋራ የሚንጸባረቁባቸው በርካታ ባህሪያት አሏቸው (May 1990፣14) ፡፡ ከነዚህ ባህሪያት መካከል ዋና ዋናዎቹ ንባብን የሚገነዘቡት በጽሁፉ ውስጥ የሰፈሩትን ቃላት እንደማነብነብ ወይም እንደመጥራት ነው፡፡

ብቁ ያልሆኑ አንባብያን ስለንባብ ምንነት ካላቸው የተሳሳተ ግንዛቤ የተነሳ አንዱን ጽሑፍ ሲያነቡ ሀሳቡ የማይገባቸው ከሆነ ጽሑፍን ቃል በቃል ለመሸምደድ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም ጽሑፉን ካነበቡ በኋላ ስለ ጽሑፍ የጽንሰ ሀሳብ ጥያቄ ሲጠየቁ አገናዝበው ከመመለስ ይልቅ የሸመደዱትን እንዳለ ቃል በቃል የመመለስ ባህሪ ይታይባቸዋል (Conley 1992:72)፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የብቁ አንባቢያንና ብቁ ያልሆኑ አንባብያን ባህሪያትና ምንነት መሰረት በማድረግ የመምህራን የንባብ ልምድ ወይም ባህል ምን ይመስላል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንደመስፈርትነት ሊያገለግለን ይችላል፡፡ ምክንያቱም መምህሩ ለተማሪው ተፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ ከተማሪው በበለጠ ሁኔታ የንባብ ልምድ ያካበተ መሆን አለበት፡፡ የንባብ ልምድ የሌለው መምህር ተማሪዎቹን በተፈለገው መንገድ የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው አያደርግም፡፡

በአጠቃላይ መምህራን የንባብ ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ጊዜ የሚከተሉትን ወሳኝ ሀላፊነቶች እንዳለባቸው Nuttal (1982:148) ፣ Celce- Marcia (1991:20) Dubin and David (1991:196) May (1990:11) ይገልፃሉ፡፡

- ❖ ተስማሚ የሆነ የማስተማሪያ ሞዴሎችን መጠቀም፤
- ❖ ከተማሪዎች የትምህርት ደረጃ ጋር የሚመጣጠን ምንባብ ወይም ቅንጫቢ ማዘጋጀት፤
- ❖ ተማሪዎች ምን ሊተገብሩና ላይተገብሩ እንደሚችሉ በቅድሚያ በመገምገም ለተማሪዎች የክህሎት ደረጃ የሚመጥን ትምህርት ማዘጋጀት፤
- ❖ ተማሪዎች የተዘጋጀውን ምንባብ በሙሉ ፍላጎት እንዲያነቡ ማነቃቃት፤
- ❖ ሁሉም በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በእኩል ደረጃ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ናቸው፡፡ በማለት ከላይ የተገለጹት ምሁራን ያብራራሉ፡፡

በተጨማሪም Williams (1986:42) "የንባብ ትምህርት በተማሪዎች እንጂ በመምህሩ ፈጽሞ መከናወን የለበትም፡፡" በማለት በአጽንኦት ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም የንባብ ትምህርት በመስማት የሚዳብር ሳይሆን ተማሪዎች እለት በእለት በሚያደርጉ ተከታታይ ልምምድ የሚዳብር በመሆኑ የንባብ ልምድ ያካበተ መምህር በንባብ ትምህርቱ ወቅት ምንባቡ በተማሪዎች ቢያስነብብ የተሻለ እንደሆነ አበክረው ይናገራሉ፡፡

## 2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በሀገራችን የማንበብ ባህል እንዲዳብር ለማድረግ ማንኛውም ዜጋ ሀላፊነት አለበት፡፡ በተለይ ደግሞ የቋንቋ መምህራን በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት በአሁኑ ጊዜ የንባብን ባህል እንዳናዳብር ከሚያደርጉ ነገሮች በመነሳት የተጠኑ ስራዎች ከዚህ ስራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ባይኖረውም በተዘዋዋሪ ይመለከተዋል፡፡

አለም (2001)፣ "የወጣቶች የንባብ ልምድ ፍተሻ፣ በአዲስ አበባ ወጣቶች መነሻነት" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ትኩረትም ወጣቶች ለንባብ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? የሚል ነው፡፡

የጥናቱም ግኝት ወጣቶቹ የንባብን አስፈላጊነት የሚያምኑ ቢሆንም ያላቸው ልምድ ግን ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመጨረሻም የንባብ ልምድን በአንድ ጀምበር የምናካብተው አለመሆኑን ተናግረው፤ የንባብ ልምድ ይዳብር ዘንድ ተማሪዎችን ከህጻንነት ጊዜያቸው ጀምሮ ከመጻህፍት ጋር በማገናኘት መሰረት መጣል እንደሚያስፈልግ በመፍትሄ ሀሳባቸው ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ደረጀ (2009)፣ "የንባብ ልምድ ቅኝት በአዲስ አበባ" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ትኩረትም የንባብ ልምድ ይዞታ የሚገለጽበት ሁኔታ ምን ይመስላል? በሚል ቅኝት አድርገዋል፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤትም የንባብ ልምድ ያልዳበረ መሆኑ፤ ትምህርት ቤቶች ተፈላጊውን መሰረት አለማስያዛቸው፣ ወላጆች፣ እንዲሁም መምህራንና የመማሪያ መፃሕፍት ጥራትና አቅርቦት በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህም የማንበብ ልምድ እንዲዳብር መሰረት በማስያዝ ረገድ ብዙም ተጽእኖ እንዳላሳደሩ አበክረው ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ ትምህርት ቤቶች፣ መምህራንና ወላጆች ለንባብ ልምድ ትኩረት እንዲሰጡ በመፍትሄነት ገልጸዋል፡፡ በመጨረሻም በዚህ ጥናት መነሻነት ሰፊና ጥልቅ ጥናት ማካሄድ እንደሚገባ በመግለጽ ፅሁፋቸውን አጠቃለዋል፡፡

በመጨረሻም Birhanu (1999)፣ "የሚያዝናና ንባብና አንባብያን ከመጻሕፍት ጋር ያላቸው ግንኙነት" በሚል ርእስ በባህር ዳር ከተማ የሚገኙ ደረጃቸው ከኮሌጅ እስከ ሁለተኛ ድግሪ ባለቸው ግለሰቦች ላይ ባደረጉት ጥናት የተገኘው ግኝት ከ215 ተጠኚዎች ውስጥ 97% ያህል በትርፍ ጊዜያቸው መጽሐፍ የሚያነቡ ሲሆን 3% እንደማያነቡ ውጤቱ ያመለክታል፡፡ በመጨረሻም በመፍትሄ ሀሳቡ መጻሕፍትን መግዛት ልምድ ማድረግ፣ የማንበብ ተነሳሽነት መኖርና ማራኪ መጻሕፍት ማግኘት እንደሚያስፈልጉ ጥናቱ ያመለክታል፡፡

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች በመምህራን የንባብ ባህል እና ንባብን የማስተማሪያ ዘዴያቸው ላይ በቀጥታ የተሰሩ ባይሆኑም በተዘዋዋሪ መልኩ ለንባብ ልምድ ልዩ ትኩረት እንደሚያስፈልግ ያሰምሩበታል፡፡ ለንባብ ልምድ መዳበር ዋነኛ ያደረጉት የጥናታቸው ተተኳሪ የሆኑት መምህራን እና በአንዳድ የከተማ ወጣቶች የንባብን ባህል በተለያዩ መንገዶች ማዳበር እንዳለባቸው ተገቢ

መሆኑን ሲገልጹ የመምህራኑን የንባብ ልምድ ከማስተማሪያ ዘዴው ጋር ያለው ተዛምዶ በቀጥታ አልቃኙትም፡፡

ይህ ጥናት ከላይ ከቀረቡ ጥናቶች የሚመሳሰለው በንባብ ልምድ ዙሪያ መፈተሹ ሲሆን፣ የሚለይበት ደግሞ የመምህራን የንባብ ባህል ከንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ የሚፈትሽ መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም በአካባቢ፣ በተጠኚዎች አይነት፣ በአላማና በጥናቱ ጊዜ ከላይ ከቀረቡ ጥናቶች ይለያል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የተነሳበትን አላማ ከግብ ለማድረስ ከዓይነታዊ የምርምር ዘዴ አንዱ የሆነው በገላጭ ቅኝታዊ (Descriptive survey Research) እንዲሁም መጠናዊ የምርምር ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህ ምእራፍ ስርም የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ ለጥናቱ ያገለገሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ዓይነትና አዘገጃጀት፣ እንዲሁም የተሰበሰቡ መረጃዎች የተተነተኑባቸው ስልቶች ቀርበዋል፡፡

### 3.1.1 የጥናቱ አካባቢ ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የሚካሄደው በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ስር ከሚገኙ 14 ዞኖችና 4 ልዩ ወረዳዎች መካከል በከምባታ-ጠምባሮ ዞን ነው፡፡ ይህ ዞን የተመረጠው በይሁነኝ ንሞና ዘዴ ነው፡፡ አካባቢው የተመረጠበት ምክንያት ከዚህ በፊት ጥናታዊ ስራዎች የተሰሩት በአዲስ አበባ፣ በባህር ዳር እንዲሁም ከሀገር ውጪ ሲሆን፣ ከዚህ ቦታ ርቆ መገኘቱ፣ የመምህራኑ የንባብ ባህል ከማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር እንዴት አዛምደው እንደሚጠቀሙ በመመርመር መረጃዎችን ማግኘት ስለምትችል ነው፡፡

### 3.1.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የሚካሄደው በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን ነው፡፡ በዚህ ዞን 15 የሁለተኛና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ 8ቱ መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ሲሆን፣7ቱ ደግሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ የሚሆኑ ከ8ቱ መሰናዶ ትምህርት ቤቶች 6 ትምህርት ቤቶች (ዱራሜ፣ ሺንሺቾ፣ ሀደሮ፣ አንጋጫ፣ ዳንቦያ፣ ዶዮገና መሰናዶ ትምህርት ቤት) በቀላል የእጣ ናሙና ዘዴ (Simple Random sampling method) ተመርጠዋል፡፡

በመሆኑም ከላይ በተመረጡት ስድስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ደረጃ በዓላማ ተኮር ንሞና (puroposive sampling method) ተመርጧል፡፡

ምክንያቱም በነዚህ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን የጥናቱ ተተኳሪዎች እንዲሆኑ ስለተደረገ ለጥናቱ በቂ መረጃ ለመሰብሰብ ከሚል አንፃር ሲሆን፣ ሁለተኛው ምክንያት በዚህ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች ከአንድ እና ከሁለት ዓመት በኋላ ወደ ዩኒቨርስቲዎች የሚገቡና ከፍተኛ የንባብ ስራ ስለሚጠብቃቸው ተገቢው ክሂል ይዘው ለመግባት መምህራኑ ምንያህል የንባብ ክሂሎት እንደሚሰጧቸው ለማወቅ አስፈላጊ ስለሆነ ነው፡፡

### 3.1.3 የተጠኚ መምህራን ናሙና አመራረጥ

ከላይ እንደተገለጸው ጥናቱ ያተኮረው በመሰናዶ ትምህርት ቤት በሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ብቻ ነው፡፡ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ አስራ ስምንት መምህራን በጠቅላይ ንሞና (comprehensive sampling) ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

### 3.1.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በስድስቱ መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመማር ላይ ከሚገኙት የ11ኛና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ተጠኚ መምህራን በሚያስተምሩባቸው በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ውስጥ በአማካይ 45-50 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል በእያንዳንዱ ምልከታ በተካሄደባቸው ክፍሎች ወካይ የሚሆኑ ተማሪዎችን ከተጠኚ መምህራን ጋር በመነጋገር ከተለያዩ የተማሪ አይነቶች በአንደኛ ወሰነ ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታቸው ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች እኩል ቁጥር በመምረጥ በአጠቃላይ ከሁሉም ተማሪዎች አንድ ሦስተኛ በመውሰድ ነው፡፡ የተፈለገውን ያህል ለመውሰድ የእጣ ናሙና ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በተለያየ የችሎታ ደረጃ ላይ ሚገኙ ተማሪዎችን በጽሑፍ መጠይቁ ለማካተት ሲባል ነው፡፡ በዚሁ መሰረት መጠይቁን የሞሉ 50 ሴት ተማሪዎችንና 70 ወንድ ተማሪዎች በአጠቃላይ 120 ተማሪዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን የጽሑፍ መጠይቁን ከሞሉ ተማሪዎች መካከል ዘጠኙ በትክክል ስላልሞሉ 111ዱ ብቻ ለትንተና ውለዋል፡፡

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት በጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የጽሑፍ መጠይቅ (questionnaire)፣ ምልከታና (Obeservation) እና ቃለ መጠይቅ (interview) ናቸው፡፡ ቀጥሎም ዝርዝሩ ቀርቧል፡፡

### 3.2.1 የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ

የጥናቱ አላማ የመምህራኑን የንባብ ባህል ከማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ በመሆኑ፣ ጥናቱን ለማካሄድ በጥቅም ላይ ከዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንዱ ለመምህራን የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ ይህ የጽሑፍ መጠይቅ የተዘጋጀው በምእራፍ ሁለት ላይ ከተጠቀሱት ንድፈ ሀሳቦች ላይ በመመርኮዝ መረጃ ያስገኛሉ ተብለው በታሰቡ ነጥቦች ላይ ነው፡፡

የጽሑፍ መጠይቁ አራት ክፍሎች አሉት፣ በክፍል አንድ ስር የሚካተቱት የመምህሩን አጠቃላይ መረጃን የሚጠይቁ 7 ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በክፍል ሁለት 13 ዝግ ጥያቄዎችና 1 ክፍት ጥያቄ ቀርቧል፣ በክፍል ሶስት የቀረቡት 10 ዝግ ጥያቄዎች የመምህራኑን የንባብ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴ ሲመለከቱ ፣ በክፍል አራት ደግሞ 4 ክፍት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ባጠቃላይ የጥያቄዎቹ ይዘት የመምህራኑን የንባብ ባህልና የማስተማሪያ ዘዴያቸውን የሚጠይቁ 23 ዝግ እና 5 ክፍት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ዝግ ጥያቄዎቹ በሊከርት ልኬት መሰረት የተዘጋጁ ሲሆን፣ ክፍት ጥያቄዎቹ የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ይህ የጽሁፍ መጠይቅ ደረጀ (2009) የተጠቀሙበት መጠይቅ የተወሰኑትን እንደሞዴል ተወስደው ከጥናቱ ጋር እንዲስማሙ ሆነው ተዘጋጅተዋል፡፡

መጠይቆቹ ከተዘጋጁ በኋላ ለመምህራኑ ከመበተናቸው በፊት ጥያቄዎቹ አስተማማኝነት እንዲኖራቸው የመጀመሪያውን ረቂቅ በባለሞያዎች (በካሪክለም መምህራን) እና በአማካሪዬ ተገምግሞ የማሻሻያ ሀሳብ እንዲሰጡ የተደረገባቸው ሲሆን፣ ለዋናው ጥናት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ በተደረገው ቃኚ ጥናትም ብቃቱ በ15 መምህራን ተፈትሾ ጠቃሚና አስፈላጊ ማሻሻያዎች ከተደረጉበት በኋላ መምህራኑ እንዲሞሉ ተደርጓል (አባሪ 1

ይመልከቱ)፡፡ እነኚህ በተጠኚ የመሰናዶ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሙሉ ለሙሉ ተሟልተው ተመልሰዋል፡፡

### 3.2.1.1 የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ

ሌላው ለመረጃ መሰብሰቢያነት ከሚውሉት መካከል ተጠኚ መምህራን በሚያስተምሯቸው ተማሪዎች የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁም በአራት ክፍል የተከፈለ ነው፡፡ በውስጡም በክፍል አንድ የተማሪዎቹን አጠቃላይ መረጃ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በክፍል ሁለት የመምህራኑን የንባብ ትምህርት የሚያስተምሩበትን ዘዴ በሚመለከት 9 ዝግ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በክፍል ሶስት የቀረቡት ጥያቄዎች የንባብ ትምህርት በክፍል ውስጥ በመምህሩ እንዴት ተግባራዊ እንደሚደረግ ይመለከታሉ፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ የተዘጋጁት በመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ዝግጅት እንደተገለጸው በመስኩ ያሉ ምሁራን ስለንባብ ትምህርት የሰነዘሩትን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በውስጡም 9 ዝግ ጥያቄዎች ይዟል፡፡ በክፍል አራት ደግሞ 3 ክፍት ጥያቄዎች ይዟል፡፡ በአጠቃላይ ለተማሪዎች የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ 3 ክፍት ጥያቄዎችና 18 ዝግ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ መጠይቁም ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በአማካሪ ተገምግሞና ማሻሻያ የተደረገበት ሲሆን፣ ለዋናው ጥናት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ በተደረገው ቃኚ ጥናት በ50 ተማሪዎች ተፈትሾ ጠቃሚና አስፈላጊ ማሻሻያዎች ከተደረገበት በኋላ በናሙናነት በተመረጡ ተማሪዎች እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡(አባሪ ሁለትን ይመልከቱ)፡፡

የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ በስድስቱም ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ ተማሪዎች ተበትኗል፡፡ የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉት ተማሪዎች የተመረጡት ተጠኚ የ11ኛ እና 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከሚያስተምሩባቸውና ምልከታው ከተካሄደባቸው የመማሪያ ክፍሎች ከየትምህርት ቤቱ ማለትም ከ11ኛ ክፍል10 እና ከ12 ክፍል10 በአጠቃላይ በአማካይ 20 በናሙናነት በመውሰድ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የጽሑፍ መጠይቁ (6×20) በ120 ተማሪዎች ተሞልቶ ተመልሷል፡፡ ነገር ግን የጽሑፍ መጠይቁን ከሞሉ ተማሪዎች መካከል ዘጠኙ በትክክል ስላልሞሉ 111ዱ ብቻ ለትንተና ውለዋል፡፡

### 3.2.1.2 የክፍል ውስጥ ምልከታ

የክፍል ውስጥ ምልከታ የጥናቱ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ነው፡፡ የክፍል ምልከታው የተካሄደው በውስን (fixed) የምልከታ ስልት ነው፡፡

ውስን ምልከታ የሚባለው በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረገው በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከሚታዩት ክንውኖች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ቀደም ብሎ የመከታተያ ቅጽ (checklist) አዘጋጅቶ መከናወኑን ወይም አለመከናወኑን በማየት መመዝገብ ነው (weir and Robert 1994፣ Richards and Nunan 1990፣ Sheal፣ 1989:97 እና ያለው 1998) ፡፡

ውስን ምልከታ ለማከናወን የተለያዩ ሞዴሎች እንዳሉ ከዘረዘሯቸው መካከል የመከታተያ ቅጽ (checklist) አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ የመከታታያ ቅጹ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በአጥኚዋ ተዘጋጅቶ፤በአማካሪዋ ተገምግሞ እና አስተያየት ተሰጥቶበት አስፈላጊ ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)

በዚህ ምልከታ መከታተያ ቅጽ በመጠቀም በናሙናነት በተመረጡት ክፍሎች በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲያስተምሩ ለሶስት ተከታታይ ጊዜ ምልከታ ተካሂዷል፡፡ ምልከታው የተካሄደው በአጥኚውና በሁለት ረዳቶች አማካይነት ነው፡፡ ረዳት ተመልካቾቹ በማስተማር ላይ የሚገኙ የእንግሊዘኛ እና የአማርኛ መምህራን ናቸው፡፡ ለአጥኚው ረዳት ያስፈለገበት ምክንያት ጥናቱን አስተማማኝ ለማድረግ ያህል ነው፡፡ በአጥኚውና በረዳቶቹ መካከልም ከምልከታ በፊት አስፈላጊ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በዚህ አይነት መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ ሶስቱ የምልከታ ውጤቶች ተደምረው አማካይ ውጤታቸውን በመውሰድ ለትንተና በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በምልከታው ሁሉም ተጠኚ መምህራን ሦስት ሦስት ጊዜ (18×3=54) ክፍለ ጊዜያት ታይተዋል፡፡ ምልከታውን ለማጠናቀቅም ስምንት ሳምንት ፈጅቷል፡፡

### 3.2.1.3 ቃለ መጠይቅ

ከፅሑፍ መጠይቅና ምልከታ በተጨማሪ ቃለ መጠይቅ በጥናቱ አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ተተግብሯል፡፡ በቃለ መጠይቁ የቀረበው ለአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት ሀላፊዎች እና ለተጠኚ መምህራን ነው፡፡ ምንም እንኳን ለተጠኚ

መምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅ የተዘጋጀ ቢሆንም በጽሑፍ መጠይቁ ያልተገለጹ ሀሳቦች ካሉ በቃለ መጠይቁ ለማግኘት ሲሆን ሌላው ለአማርኛ ቋንቋ የክፍለ ትምህርት ሀላፊዎች የቀረበ ነው፡፡ የቃለ መጠይቁ ጥያቄዎች ለጥናቱ እንዲስማሙ ሆነው ከተዘጋጁ በኋላ በአማካሪ ተገምግመውና ማሻሻያ ተደርጎባቸው በተግባር ላይ ውለዋል፡፡

### 3.2.1.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በጽሑፍ መጠይቅ፣ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በየንዑስ ጉዳዮች ስር በመደራጀት ገላጭ ዘዴን በመጠቀም እና ተዛምዷቸውን ደግሞ በመቶኛ ስሌት በመጠቀም ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀመው ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መካከል አንዱ የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ በመጠይቁ በሶስት አይነት መንገድ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የመጀመሪያው ከአንድ በላይ አማራጭ መልሶች የያዙ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በአራት የስምምነት ስኬሎች (ዘውትር፣ አብዛኛውን ጊዜ፣ አልፎ አልፎ እና ፈጽሞ አያከናውኑም) በሚል የቀረቡ ሲሆን፣ በዚህ መንገድ የተገኙ መረጃዎች በማቀናጀት ተተንትነዋል፡፡ ሌላው ክፍት የጽሑፍ መጠይቅ በየርዕሰ ጉዳዮች ስር በማቀናጀት ተተንትነዋል፡፡

በመምህራን የንባብ ባህልና የንባብ ትምህርትን ማስተማሪያ ዘዴው መካከል ያለውን የግንኙነት ደረጃ ለማወቅ በመቶኛ ስሌት ተገልግሏል፡፡ በመረጃ አተናተን ሂደትም በመጀመሪያ ስለመምህራኑ የንባብ ባህል በመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በአራት ክፍሎች በመመደብ በየምድባቸው ከተደራጁ በኋላ ከተለያዩ አቅጣጫዎች እየታዩ በመቶኛ ተተንትነዋል፡፡ ከዚህም የተገኘው መረጃ ማብራሪያና ትርጉም ተሰጥቶባቸዋል፡፡

# ምእራፍ አራት

## የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

### 4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና

በዚህ ምእራፍ በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች በየመልካቸው ተጠናቅረው ተተንትነዋል፡፡ ትንተናው መሰረት የሚያደርገው በመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ፣ በተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ፣ በክፍል ምልከታ እንዲሁም ለመምህራንና ለአማርኛ ክፍለ ትምህርት ኃላፊዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ነው፡፡ ለጥናቱ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን ረገድ በቅድሚያ መምህራን ስላላቸው የንባብ ባህል፣ የመምህሩ ንባብን የማስተማሪያ ዘዴው በተግባር ማዋል ለመፈተሽ በተደረገው ምልከታ የተገኙ መረጃዎች በመቶኛ ተሰልተዋል፡፡ በመጨረሻም በመምህራኑ የንባብ ልምድና ንባብን ከማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለው ዝምድና ለማወቅ በመቶኛ ስሌት የተገኘው ውጤት ቀርቧል፡፡

የዋናው ጥናት ትንተና ከመቅረቡ በፊት ስለተጠኚ መምህራን እና የጽሑፍ መጠይቁን ስለሞሉት መምህራን ዳራ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 4.1.1 የተጠኚ መምህራን ዳራዊ መግለጫ

ሠንጠረዥ 1፦ የተጠኚ መምህራን ዳራ

| ትምህርት ቤት | ፆታ | እድሜ | የትምህርት ደረጃ | የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት | | የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዋና | ንኡስ | | |
| ዱራሜ | ወ | 54 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | --- | 11ኛ እና 12ኛ | 32 |
| | ወ | 45 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | ኢ.ዱኬሽን | 11ኛ | 30 |
| | ሴ | 48 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 11ኛ | 33 |
| | ሴ | 38 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 12ኛ እና 12ኛ | 20 |
| ሺንሺቾ | ወ | 40 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 11ኛ | 20 |
| | ወ | 35 | ቢ.ኤ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 12ኛ | 14 |
| | ወ | 24 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 11ኛ | 3 |
| ሀደሮ | ወ | 49 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 11ኛ | 29 |
| | ወ | 41 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 11ኛ | 23 |
| | ሴ | 26 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | እንጊሊዘና | 12ኛ | 9 |
| | ወ | 23 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | እንጊሊዘኛ | 12ኛ | 5 |
| አንጋጫ | ወ | 47 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | እንግሊዘኛ | 11ኛ | 25 |
| | ወ | 27 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | እንግሊዘኛ | 11ኛ | 9 |
| | ወ | 27 | ቢ.ኤ | አማርኛ | ትያትር | 11ኛ እና 12ኛ | 8 |
| ዳንቦያ | ወ | 40 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | እንግሊዘኛ | 11ኛ | 27 |
| | ሴ | 28 | ቢ.ኤ. | አማርኛ | እንግሊዘኛ | 12ኛ | 3 |
| ዶዮገና | ወ | 45 | ቢ.ኤ | አማርኛ | እንግሊዘኛ | 12ኛ | 32 |
| | ወ | 24 | ቢ.ኤ.+ፒ.ጂ.ዲ.ቲ | አማርኛ | ----- | 11ኛ | 2 |

ከሰንጠረዥ 1 መመልከት እንደሚቻለው ተጠኚ መምህራን አስራ ስምንት ናቸው፡፡ ጥናቱን በትክክል ለማከናወን ያመች ዘንድ የመምህራኑ ዳራ ፍተሻ ተደርጓል፡፡ በጾታ ረገድ ሲታይ 4 ሴት (22.2%) እና 14 ወንድ (77.8%) መምህራን ናቸው፡፡ የተጠኚ መምህራን ዕድሜ ደረጃ ከ23 እስከ 54 ዓመት ነው፡፡ በትምህርት ደረጃ አንፃር ሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ አላቸው፡፡ በስልጠና ደረጃም ሲታይ 14(77.8%)

መምህራን አማርኛን በዋናነት እና እንግሊዝኛን በንዑስ ትምህርትነት አጥንተዋል፡፡ 2(11.1%) መምህራን ደግሞ አማርኛን ብቻ በዋናነት ያጠኑ ሲሆኑ፣ 2(11.1%) መምህራን አማርኛን በዋናነት እና "ኢዱኬሽን" በንዑስ ትምህርትነት አጥንተዋል፡፡

### 4.1.2 የመምህራን የንባብ ባህል በተመለከተ ከቀረበው መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

*ሰንጠረዥ 2፡ የመምህሩ የንባብ ባህል ባህሪያት*

| ተ.ቁ | የጥያቄው ይዘት | የመላሽ ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 2.1 | እርስዎ አንባቢ የሚሉት እንዴት ያለ ሰው ነው?<br>- በእረፍት ጊዜው መጽሐፍ የሚያነበውን<br>- ለንባብ ጊዜ የማይወስነውን<br>- የሚነበቡ መጽሐፍቶች ከእጁ የማይለየውን<br>- በሚያነቡበት ጊዜ ፊታቸው ላይ የመጨነቅ ስሜት የማይታይባቸውን<br>- ሌሎች | 3<br>11<br>3<br>0<br>1 | 16.67<br>61.1<br>16.67<br>0<br>5.56 |
| 2.2 | የንባብ ባህልዎ ምን ይመስላል?<br>- ሁል ጊዜ አነባለሁ<br>- አብዛኛውን ጊዜ አነባለሁ<br>- አልፎ አልፎ አነባለሁ<br>- ፈጽሞ አላነብም | 3<br>9<br>6<br>0 | 16.67<br>50.00<br>33.33<br>0 |

በሰንጠረዥ 2 መመልከት እንደሚቻለው የአንድ አንባቢ ባህሪ ለመለየት ከቀረበው መጠይቅ የተገኘው ምላሽ 61.1% መምህራን ለንባብ ጊዜ የማይወስነውን አንባቢ ነው ሲሉ፣ 16.67% መምህራን በእረፍት ጊዜው የሚያነበውን፣16.67% መምህራን ደግሞ የሚነበቡ መጻሕፍት ከእጁ የማይለየውን ሰው አንባቢ ነው ይሉታል ፣ በመጨረሻም ሌሎች በሚለው ስር የተሰጡ ሀሳቦች 5.56% መምህራን አንባቢ የሚባለው ለንባብ ልዩ ፍቅር ያለው ሰው፣ መጽሐፍ የማይመርጠው ነው አንባቢ የሚባለው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በተራ ቁጥር 2.2 በቀረበው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ 50% አብዛኛውን ጊዜ እንደሚያነቡ፣ 33.33% የሆኑት አልፎ አልፎ እንደሚያነቡ፣ የተቀሩት 16.67% ደግሞ ሁል ጊዜ የሚያነቡ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

የሠንጠረዥ 2 ጥያቄ (2.1 እና 2.2) ምላሾች የምንረዳው አብዛኛው ተጠኚ መምህራን ለንባብ ጊዜ የማይወስነው የማንበብ ልምድ እንዳላቸው ያምናሉ፡፡

በምእራፍ ሁለት (2.1.6) በቀረበው ነጥብ በሰፊው እንደተገለጸው አንድ ሰው የሚያነበውን መጽሐፍ መርጦ ያለምንም ቀስቃሽ በራሱ ፍላጎት ማንበብ ሲችል ነው የማንበብ ልምድ አለው ማለት የሚያስችለን፡፡ በዚህ አይነት ማንበብ የለመደ አንባቢ ጥሩና የተዋጣለት አንባቢ፤ ንባቡም የፍላጎቱን ሊያደርስለት የሚችል እንደሚሆን እሙን ነው (አለም፣2001፡65፤charles, 1985:207)፡፡ ከዚህ መረጃ ጋር አብዛኛው ተጠኚዎች ከሰጡት ምላሽ ጋር አለመገናኘቱን ውጤቱ ያመለክታል፡፡ ይህም ሁል ጊዜ፣ አብዛኛውን ጊዜም ሆነ አልፎ አልፎ የማንበብ ልምድ በተግባር እንዴት ሊገለጥ እንደሚችል ለማወቅ፤ በቀን ለምን ያህል ሰአት እንደሚሰሩ፣ በእረፍት ጊዜያቸው ለምን ያህል ሰአት እንደሚያነቡ እና የንባብ ልምዳቸው በአማካይ እንዴት እንደሚገለጽ በሚጠቁም ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

*ሠንጠረዥ 3፡ የመምህሩን የንባብ ባህል የሚገልጹ ባህሪያት*

| ተ.ቁ | የጥያቄው ይዘት | የመላሾች ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 2.3 | በቀን ለምን ያህል ሰዓት የማስተማር ስራ ይሰራሉ<br>- ለስድስት ሰአት<br>- ለስምንት ሰአት<br>- ለአስር ሰአት<br>- ለአስራ ሁለት ሰአት<br>- ሌሎች | 8<br>1<br>8<br>0<br>1 | 44.44<br>5.56<br>44.44<br>0<br>5.56 |
| 2.4 | በእረፍት ጊዜዎ በቀን ለምን ያህል ሰዓት ያነባሉ<br>- ለአርባ ደቂቃ<br>- ለአንድ ሰአት<br>- ለሁለት ሰአት<br>- ለስድስት ሰአት<br>- ሌላ | 0<br>6<br>8<br>3<br>1 | 0<br>33.33<br>44.44<br>16.67<br>5.56 |
| 2.5 | የንባብ ልምድዎ በአማካይ እንዴት ይገለፃል<br>- በሳምንት አንድ መጽሐፍ<br>- በወር አንድ መጽሐፍ<br>- በወር ሁለት መፅሐፎች<br>- በአገኘሁት አጋጣሚ<br>- ሌሎች | 2<br>8<br>5<br>2<br>1 | 11.12<br>44.44<br>27.78<br>11.12<br>5.56 |

በሰንጠረዥ 3 እንደሚታየው በተራ ቁጥር 2.3 በቀረበው መጠይቅ የተጠኚዎችን የንባብ ባህላቸውን ለማወቅ በቀን ለምን ያህል ሰአት እንደሚሰሩ የሚመለከት ጥያቄ ከቀረበው 44.44% በቀን ለስድስት ሰአት፣ 44.44% በቀን ለአስር ሰአት፣ 5.56% ለስምንት ሰአት፣ 5.56% የሚሆኑት ደግሞ የምሰራበትን ሰአት መወሰን አልችልም ብለዋል፡፡ በእረፍት ጊዜዎ በቀን ለምን ያህል ሰአት ያነባሉ ለሚለው ጥያቄም 33.33% ለአንድ ሰአት፣ 44.44% ለሁለት ሰአት፣ 16.67% ለስድስት ሰአት፣ 5.56% ሰአት መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ለጥያቄ 2.56 ከተሰጠው ምላሽ እንደምናየው አብዛኛው 44.44% የሚሆኑት በወር አንድ መጽሐፍ፣ 27.78% በወር ሁለት መጽሐፍ፣ 11.12% ባገኘሁት አጋጣሚ የሚል ሲሆን ቀሪዎቹ 5.56% ጊዜ መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ተገኝቷል፡፡

በሠንጠረዥ 3 ጥያቄ (ቁጥር 2.3 ፣ 2.4 እና 2.5 ) ምላሾች እንደሚያሳዩት የመምህራኑን የንባብ ባህል ለማወቅ በቀን ለምን ያህል ጊዜ እንደሚሰሩና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚያነቡ ለመረዳት በጥያቄ ቁጥር 2.5 ከተገኘው ውጤት ጋር ማስተያየት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በተ.ቁ 2.4 ላይ በቀረበው መጠይቅ ከአንድ መምህር በስተቀር በቀን ለተወሰነ ሰአት እንደሚያነቡ ከገለፁ በኋላ አብዛኛው 44.4% በወር አንድ መጽሐፍ እንደሚያነቡ ገልጸዋል፡፡ በጥያቄ 2.5 ደግሞ 44.4% በቀን ለሁለት ሰአት እንደሚያነቡ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በሁለቱ መልሶች መካከል ልዩነት እንዳለ እናያለን፡፡ በቀን ሁለት ሰአት እያነበቡ በወር አንድ መጽሐፍ እንደሚፈጅባቸው መረጃው ያመለክታል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የንባብ ፍጥነታቸው ዘገምተኛ እንደሆነ እና ፍልጎትና ድርጊት የሚለያዩ መሆናቸው ውጤቱ ያመላክታል፡፡ ቀደም ሲል በተደረገ ጥናትም (አለም 2001፣ ደረጀ 2009) በንባብ ፍላጎትና በክንዋኔው መካከል ልዩነት መኖሩ ተጠቁሟል፡፡ ስለዚህ ይህ ሀሳብ ደግሞ ከሰንጠረዥ 3 ተ.ቁ 2.1 እና 2.2 በእጅጉ ይዛመዳል፡፡

ሰንጠረዥ 4፡- መምህራን በብዛት የሚያነቧቸው ጽሑፎች

| ተ.ቁ | የጥያቄው ይዘት | የመላሾች ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 2.6 | እርስዎ ምን አይነት ጽሑፍ ነው የሚያነቡት? | | |
| | - ልብ-ወለድ | 16 | 88.88 |
| | - የሀይማኖት መፃህፍት | 9 | 50.00 |
| | - ጋዜጣ | 6 | 33.33 |
| | - የፍልስፍና መፃሕፍት | 3 | 16.67 |
| | - መጽሔት | 7 | 38.88 |
| | - በራሪ ጽሑፎች | 3 | 16.67 |
| | - የታሪክ መጽሐፍ | 2 | 11.12 |
| | - ሁሉም | 3 | 16.67 |
| | - ሌሎች | 4 | 22.22 |
| 2.7 | መጽሐፍ የሚያነቡት ለምን አላማ ነው? | | |
| | - ለመዝናናት | 9 | 50.00 |
| | - የንባብ ልምድ ለማሻሻል | 8 | 44.44 |
| | - ለጠቅላላ እውቀት | 6 | 33.33 |
| | - ለማስተማር መጠቀሚያ | 8 | 44.44 |
| | - ለሁሉም | 10 | 55.56 |
| | - ሌሎች | 3 | 16.67 |

በሠንጠረዥ 4 እንደተገለጸው፣ ለጥያቄ 2.6 የሚያነቡት ጽሐፍ በተመለከተ ተጠኚዎቹ በተደጋጋሚ የጠቀሷቸው ቀርበዋል፡፡ በአብዛኛው ልብ ወለድ 88.88%፣ የኃይማኖት መጽሐፍ 50%፣ መጽሔት 38.88% ሲሆኑ፣ ዝቅተኛ አንባቢ ያለው የታሪክ መጽሐፍ 11.12% ሁሉንም የሚያነቡ ደግሞ 16.67% ነው፡፡ በመጨረሻም ሌሎች በሚለው 22.22% ተጠኚዎች የፖለቲካ መጻህፍት፣ ማጣቀሻዎች እና የተገኘውን ሁሉ እንደሚያነቡ ከምላሹ ተገኝቷል፡፡[3] ከላይ በቀረቡት ጥያቄዎች የተገኙት ምላሾች እንደሚጠቁሙን መጠይቁን የሞሉ ተጠኚዎች ልብ ወለዶችን፣ የሀይማኖት መጽሐፍ፣ መጽሔት እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱትን ጽሑፎች እንደሚያነቡ መረጃው ያመለክታል፡፡ እነዚህን ጽሑፎች የሚያነቡት ለምን አላማ እንደሆነ እንዲገልጹ ተጠይቀው ነበር፡፡ በዚሁ ሰንጠረዥ በጥያቄ ቁጥር 2.7 መጽሐፍት የሚያነቡት ለምን አላማ ነው? ለሚለው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ ለመዝናናት 50%፣ የንባብ ልምድ ለማሻሻል 44.44%፣ ለጠቅላላ እውቀት 33.33%፣ ለማስተማር መጠቀሚያ 44.44%፣ ለሁሉም 55.5% ሲሆን፣ ሌሎች በሚለው ላይ

---

[3] በዚህና በሌሎች ተከታታይ ሰንጠረዦች አልፎ አልፎ የመልሶችን ቁጥር ከጠቅላላ መላሾች አንጻር ስንመለከተው ልዩነት እንዳለ እንመለከታለን፣ ይህ የሆነው ተጠኚዎች የሚመርጡት ከአንድ በላይ መልስ የመስጠት እድል ስላላቸው ነው፡፡
ይህም ከደረጀ (2009) ጥናት ጋር ይስማማል፡፡

16.67% የሚሆኑ ተጠኚዎች ለመዝናናት ከሚለው ውጪ ስራ ለመፍጠር፣ ብቸኝነትን ለመርሳት የሚል ምላሽ ተገኝቷል፡፡

ከዚህ ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠኚዎች መጻሕፍት የሚያነቡበት አላማ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ለምን እንደምናነብ ካላወቅን ማንበብ ምንም ፋይዳ የለውም ማለት ይቻላል፡፡ ሁል ጊዜ ንቁ ለመሆን የሚጠቅሙንና መረጃ ይሰጡናል የምንላቸውን መጻህፍት ማንበብ አንዱ ነው፡፡ በክፍል ሁለት 2.1.2 እንደተገለጸው ንባብን ለምን እንደሚነበብ በተመለከተ Grellt (1981) Wallace (1992:6-7) በሚከተሉት ሦስት መሰረታዊ የንባብ አላማዎች ይዘረዝሯቸዋል፡፡ እነዚህም ንባብ ለጥንቃቄ ዓላማ፣ ንባብ ለመማርና ለማወቅ ዓላማ፣ ንባብ ለመዝናናት አላማ የሚሉ ናቸው፡፡ ይህም በሠንጠረዥ 4 ላይ እንደተጠቆመው ከመምህራኑ ምላሽ ጋር በአብዛኛው የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ መምህራኑ የንባብ ልምዳቸውን ተጠቅመው ለሌሎች የማጋራት ባህልስ አላቸው ለሚለው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ሠንጠረዥ 5፡ መምህራን የንባብ ልምዳቸውን ለሌሎች የማጋራት ሁኔታ*

| ተ.ቁ. | የጥያቄው ይዘት | የመላሽ ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % |
| 2.8 | መጽሐፍ ካነበቡ በኋላ ስላነበቡት ጉዳይ ከጓደኞችዎ ጋር ይወያያሉ<br>- ሁል ጊዜ<br>- አብዛኛውን ጊዜ<br>- አልፎ አልፎ<br>- አልወያይም | 1<br>3<br>12<br>2 | 5.56<br>16.67<br>66.67<br>11.12 |

በምእራፍ ሁለት 2.1.6 ላይ እንደተገለጸው የንባብ ልምድ ያዳበረ ሰው በእጆቹ የሚገቡትን ለደረጃውቸው እና ለእድሜያቸው የሚመጥኑትን መጽሐፎች፣ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ ወዘተ ገዝቶም ሆነ ተውሶ ሲያነብ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ካነበቡም በኋላ ያነበቡትን ቁም ነገር ለጓደኞቻቸው ወይም ለወላጆቻቸው ለማጋራት ፍላጎቱ ይኖራቸዋል (አለም፣2001፡65 ፤ Charles, 1985:207)፡፡ ይህንን ሁኔታ ተጠኚዎቹ ያከናውኑ ይሆን ተብሎ በጥያቄ ተራ ቁጥር 2.8 መጽሐፍ ካነበቡ በኋላ ስላነበቡት

ጉዳይ ከጓደኞችዎ ጋር ይወያያሉ? በሚል ለቀረበው መጠይቅ፣ 5.56% "ሁል ጊዜ" 16.67% "አብዛኛውን ጊዜ" 66.67% "አልፎ አልፎ" 11.12% "አልወያይም " በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን 66.67% አልፎ አልፎ እንደሚወያዩ ውጤቱ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለመምህራኑ በቀረበው ቃለ መጠይቅ፣ ከሌላ የስራ ባልደረባዎ ጋር ስለንባብ ባህል መዳበር ይወያያሉ? ውይይቱን የሚያደርጉት በምን መልኩ ነው? ከሚለው ምላሽ የተገኘው ውጤት አብዛኞቹ አንዳንድ ጊዜ ውይይት እንደሚያደርጉ ተረጋግጧል፡፡ ከውይይቱ በተጨማሪ የንባብ ባህላቸውን እንዴት እንደሚያዳብሩ ከላይ የተገኘውን መረጃ በማያያዝ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

*ሰንጠረዥ 6፡ የንባብ ባህል ሊዳብር የሚችለው እንዴት ነው?*

| ተ.ቁ. | የጥያቄው ይዘት | የመላሽ ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % |
| 2.9 | የንባብ ልምድን እንዴት ማዳበር የሚቻል ይመስልዎታል? | | |
| | - በየቀኑ በማንበብ | 11 | 61.1 |
| | - ለንባብ ያለንን የጊዜ አጠቃቀም በመወሰን | 5 | 27.7 |
| | - የሚያዩትን ለማንበብ የጊዜ አጠቃቀም በመወሰን | 0 | 0 |
| | - ሌሎች | 4 | 22.2 |

በሠንጠረዥ 6 ጥያቄ ቁ. 2.9 በቀረበው መጠይቅ የንባብ ባህል እንዴት ማዳበር እንደሚቻል የተሰጠው ምላሽ 61.1% የሚሆኑት መምህራን በየቀኑ በማንበብ፣ 27.7% ለንባብ ያለንን ጊዜ በመወሰን የንባብ ልምዳችን ማዳበር እንደሚችል ሲገልጹ፣ ሌሎች በሚለው ስር የተሰጠው 22.2% የሚሆኑት ደግሞ የተለያዩ መጻሕፍትን ከመማሪያ መፅሐፍ በተለየ ሁኔታ የሚያነብ ከሆነ፣ የማበብ ፍላጎትና ፍቅር ሲኖረው፣ በየቀኑ የሚያነበውን ጽሑፍ መልእክት ምን ያህል እንደተረዳና እንደተጠቀመ ማስታወስ ሲችል፣ ለማንበብ የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ የሚጠቀም ከሆነ የንባብ ባህልን ማዳበር ይችላል የሚል ምላሽ ተገኝቷል፡፡

በምእራፍ ሁለት 2.1.5 በተጠቀሰው ነጥብ የንባብ ባህል ማዳበር ከንባብ ትምህርት ዓላማ ማሳደግ ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ ዓይነቱ ልምድ እንዲበለፅግ ከተፈለገ በመምህራንም ሆነ ሌሎች ማህበረሰቦች ከንባብ ጋር ያላቸው ቀረቤታ የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ እንደሚገባ Smith (1997:29) ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለመምህራን በቀረበው የቃለ መጠይቅ የንባብ ባህልዎ ዳብሯል ብለው ያስባሉ? ከሚለው ጥያቄ የተገኘው መረጃ አብዛኞቹ የንባብ ባህላችን ሙሉ በሙሉ ዳብሮዋል ማለት አንችልም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ምክንያቱን ሲገልጹ ንባብ በአንድ ጊዜ የሚዳብር ሳይሆን በተደጋጋሚ የሚከናወንና ሂደታዊ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ይህም በሠጠረዥ 7 ላይ እንደተጠቆመው ከመምህራኑ ምላሽ ጋር በአብዛኛው የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝ ለክፍለ ትምህርቱ ሀላፊዎች በቀረበላቸው የቃለ መጠይቅ “መምህራን ንባብን ለማዳበር ምን ማድረግ አለባቸው? ” ከክፍለ ትምህርቱ ሀላፊዎች መካከል አንዱ በአመት ሁለት ቀን በወጣቶች አዳራሽ ንባብ ብቻ እንዲቀርብ እና አንባቢዎች እንዲጨምሩ በማድረግ የንባብ ባህል የሚዳብርበትን መንገድ የበኩላቸውን እንቅስቃሴ እያደረጉ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም የንባብ ልምዳቸውን ተጠቅመው በክፍል ውስጥ የሚተገበረው ጽሑፍ አስመልክቶ የተገኘ መረጃ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

*ሠንጠረዥ 7፡ መምህራን ንባብን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ዘዴ አስመልክቶ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ. | የጥያቄው ይዘት | ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % |
| 2.10 | የንባብ ትምህርት ሲያስተምሩ ከመማሪያ መጽሐፍ ውጪ የራስዎን ተጨማሪ ምንባብ ያዘጋጃሉ | | |
| | - ዘውትር | 0 | 0 |
| | - አብዛኛውን ጊዜ | 2 | 11.12 |
| | - አልፎ አልፎ | 14 | 77.7 |
| | - ፈጽሞ አላዘጋጅም | 2 | 11.12 |
| 2.11 | ንባብዎ ለማስተማር ዘዴዎ ያለው አስተዋፅዖ | | |
| | - በጣም ከፍተኛ | 6 | 33.33 |
| | - ከፍተኛ | 8 | 44.44 |
| | - መካከለኛ | 3 | 16.67 |
| | - ዝቅተኛ | 1 | 5.56 |

ከፍ ባለው ሰንጠረዥ 7 እንደሚታየው በተ.ቁ.2.10 ላይ የቀረበው መጠይቅ መምህራን የንባብ ልምዳቸውን ተጠቅመው በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች የንባብ ትምህርትን ሲሰጡ ከማስተማሪያ መጽሐፉ ውጭ የሚጠቀሙት ጽሑፍ እንዳለ የሚጠይቅ ነው፡፡ ተጠኚዎቹም 77.7% የሚሆኑት "አልፎ አልፎ"፣ 11.12% "አብዛኛውን ጊዜ"፣ 11.12% ደግሞ "ምንም አላዘጋጅም" በማለት መልሰዋል፡፡

በዚሁ ሠንጠረዥ በተራ ቁጥር 2.11 ንባብ ለዘዴ ስለሚኖረው አስተዋጽዖ ለቀረበው ጥያቄ 44.44% የሚሆኑ መምህራን "በከፍተኛ" ደረጃ እንደሚጠቀሙ፣ 33.33% የሚሆኑት "በጣም በከፍተኛ" ደረጃ አስተዋጽዖ እንዳለው ሲገልጹ፣ 16.67% "በመካከለኛ" ደረጃ 5.56% መምህር ደግሞ "ዝቅተኛ " እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በጥያቄ ቁጥር 2.10 ከተገኘው ውጤት ጋር ስናስተያየው ተቃራኒ ነው፡፡ ንባባቸው ለማስተማር ዘዴያቸው ያለውን አስተዋጽዖ በተመለከተ የተገኘው ምላሽ በአብዛኛው 44.44% "ከፍተኛ" በጥያቄ 2.10 የተገኘው ምላሽ ደግሞ በአብዛኛው 77.7 የሚሆኑ ከመማሪያ መጽሐፍ ውጪ ተጨማሪ ጽሑፍ የሚያዘጋጁት "አልፎ

አልፎ" እንደሆነ ከምላሹ ተገኝቷል፡ ይህንኑ በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ሠንጠረዥ 8፡ ንባብን ለመማር የሚጠቀሙት ጽሑፍ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ | የጥያቄው ይዘት | ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % |
| 2.3 | በንባብ ጊዜ መምህራችሁ ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ በግላቸው ጽሑፎችን በማቅረብ ያለማምዷችኋል | | |
| | - ሁል ጊዜ | 0 | 0 |
| | - አብዛኛውን ጊዜ | 10 | 9 |
| | - አልፎ አልፎ | 54 | 48.65 |
| | - ፈጽሞ አያለማምዱንም | 47 | 42.35 |
| | ድምር | 111 | 100 |
| 2.5 | መምህራችሁ ክፍል ውስጥ እንድታነቡ የሚያሳድሩት ተጽእኖ ምን ያህል ነው | | |
| | - በጣም ከፍተኛ | 27 | 24.32 |
| | - ከፍተኛ | 29 | 26.13 |
| | - መካከለኛ | 37 | 33.33 |
| | - ዝቅተኛ | 18 | 16.22 |
| | ድምር | 111 | 100 |

በሠንጠረዥ 8 በተራ ቁጥር 2.3 በቀረበው መጠይቅ መምህራችሁ ንባብን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ ከመማሪያ መጻሕፍት ውጭ በግላችው ጽሑፎችን በማቅረብ እንደሚያለማምዷቸው ለተጠየቀው የሰጡት ምላሽ አብዛኞቹ 48.65% "አልፎ አልፎ"፣ 9% "አብዛኛውን ጊዜ"፣ 42.35% የሚሆኑት ደግሞ ፈጽሞ እንደማያለማምዷቸው ምለሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ መረጃ እንደምንረዳው 42.3% የሚሆኑ ተማሪዎች መምህራት እንደማያለማምዷቸው ነው፡፡ ይህ ሀሳብ ደግሞ ከላይ በሰንጠረዥ 8 ላይ መምህራን ከሰጡት መረጃ ጋር አይመሳሰልም፡፡ በዚሁ ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር 2.5 ለቀረበው መጠይቅ፣ 26.1% "ከፍተኛ"፣ 24.3% "በጣም

ከፍተኛ"፣ 33.3% "መካከለኛ"፣16.2% ደግሞ ዝቅተኛ ነው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ውጤቱ እንደሚያሳየው መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው የሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ ጋር ተመሳሳይነት የለውም፡፡ ይህንንም ለመረዳት ለክፍል ትምህርቱ ሀላፊ በቀረበው የቃለ መጠይቅ ከተጠኚ መምህራኑ የተገኘው ምላሽ የተማሪዎቹ የንባብ ችሎታ በክፍል ውስጥ ለመተግበር የሚያነሳሳ ስላልሆነ፣ከአንድና ከሁለት መምህራን ውጪ ጥረት እንደማያደርጉ፣ያም ሆኖ ውስንነት እንደሚታይበት ተናግረዋል፡፡

ከዚህ መረጃ ማጠቃለል የሚቻለው ተጠኚዎቹ ከመማሪያ መጻሕፍት ውጭ የራሳቸውን ጽሑፍ በማዘጋጀት ረገድ አልፎ አልፎ እንደሆነ ውጤቱ ያሳያል፡፡ ነገር ግን ይህ ውጤት በተደጋጋሚ በተካሄደው ምልከታ ሲከናወን የታየው በሁለት መምህር ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም ተጠኚ መምህራን ከሚያስተምሩበትና ምልከታ ከተካሄደባቸው በናሙናነት ከተመረጡት ተማሪዎች የተገኘው መረጃ አብዛኞቹ መምህራን እንደማይተገብሩ ተረጋግጧል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ምን እንደሆነ በቃለ መጠይቅ ወቅት ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፣ ያነበብነው ሁሉ በማስተማር ላይ ተግባራዊ የምናደርግበት አጋጣሚ ስለሌለና የተማሪዎች ዝቅተኛ የንባብ ችሎታ ለመተግበር የሚያነሳሳ አይደለም በሚል ሀሳብ በምክንያትነት ገጸልዋል፡፡

በምእራፍ ሁለት 2.1.9.2 በተገለጸው ነጥብ መምህራኑ የንባብ ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ጊዜ ከተማሪዎች የትምህርት ደረጃ ጋር የሚመጣጠን ምንባብ ወይም ቅንጫቢ ማዘጋጀት ከወሳኝ ሀላፊነቶች መካከል አንዱ እንደሆነ Nuttal (1982:148) ፣ Celce- Marcia (1991:20) Dubin and David (1991:196) May (1990:11) ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ በተራ ቁጥር 2.10 እና 2.11 ለቀረቡ ጥያቄዎች ከተሰጡ መልሶች የተገኘው ውጤት ሙሉ በሙሉ አልተመሳሰለም፡፡ ይህም የሚያሳየው የመምህራኑ የንባብ ልምድ ለማስተማሪያ ዘዴያቸው የሚተገብሩበት መንገድ ዝቅተኛ እንደሆነ ከጽሑፍ መጠይቅ፣ ከተማሪዎች መጠይቅ እና ከክፍል ምልከታው የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ በክፍል ውስጥ ንባቡን እንዴትና በማን እንደሚካሄድ ከመምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ሰንጠረዥ 9፡ መምህራኑ ምንባቡን እንዴት እንደሚተገብሩ የሚያሳይ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ | የጥያቄው ይዘት | ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % |
| 2.12 | ተማሪዎች የተለያዩ ጽሑፎች አንብበው እንዲመጡ እና ስላነበቡት ጉዳይ እንዲወያዩ ያደርጋሉ | | |
| | - ሁል ጊዜ | 2 | 11.1 |
| | - አብዛኛውን | 5 | 27.8 |
| | - አልፎ አልፎ | 11 | 61.1 |
| | - ፈጽሞ አላደርግም | 0 | 0 |
| 2.13 | ክፍል ውስጥ ምንባቦች የሚነበቡት በእርስዎ ነው | | |
| | - ሁል ጊዜ | 0 | 0 |
| | - አብዛኛውን ጊዜ | 4 | 22.2 |
| | - አልፎ አልፎ | 11 | 61.1 |
| | - ፈጽሞ አላነብም | 3 | 16.7 |
| 2.14 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የማንበብ እድል የሚያገኙት | | |
| | - ሁል ጊዜ | 4 | 22.2 |
| | - አብዛኛውን ጊዜ | 10 | 55.6 |
| | - አልፎ አልፎ | 4 | 22.2 |
| | - አያነቡም | 0 | 0 |

ከሠንጠረዥ 9 መመልከት እንደሚቻለው በተራ ቁጥር 2.12 በቀረበው መጠይቅ ተማሪዎች ከክፍል ውጪ የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው እንዲመጡና ስላነበቡት ጉዳይ እንዲወያዩ ማድረጋቸውን በሚመለከት የቀረበ ሲሆን፣ 61.1% “አልፎ አልፎ”፣ 27.8% “አብዛኛውን ጊዜ”፣11.1% “ሁል ጊዜ” አደርጋለሁ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው መምህራን ተማሪዎቻቸውን ስላነበቡት ጉዳይ እንዲወያዩ የማድረጉ ጉዳይ ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህ ውጤት በምልከታ ወቅት ከተገኘው ውጤት ጋር በተወሰነ ደረጃ ይለያያል፡፡ ምክንያቱም ከምልከታ የተገኘው ውጤት ሲከናወን የታየው በተወሰኑ ማለትም በስድስት 33.3% ተጠኚዎች ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም አብዛኞዎቹ ተጠኚ መምህራን ተማሪዎቹን ስላነበቡት ጉደይ በክፍል

ውስጥ እንደማያወያዩ ታይቷል፡፡ ይህም በሠንጠረዥ 9 ላይ ከተገጸው የመምህራኑ ምላሽ በምልከታ ከተገኘው ውጤት ጋር የማይስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር (2.13) በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት ምንባቦች በማን እንደሚተገበሩ ለቀረበው መጠይቅ 61.1% "አልፎ አልፎ"፣22.2% "አብዛኛውን ጊዜ"፣ 16.7% "ፈጽሞ አላደርግም" የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህም ከጥያቄ ተራ ቁጥር 2.12 ተማሪዎችን አንብበው እንዲመጡ እና በክፍል ውስጥ እንዲወያዩ "አልፎ አልፎ" አደርጋለው በማለት ከሰጡት መልስ ጋር ማስተያየት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም 61.1% ከክፍል ውጪ እንዲያነቡና እንዲወያዩ አደርጋለው በማለት ከገለጹ በኋላ በክፍል ውስጥ ምንባቦችን የሚተገብሩት 61.1% በመምህራኑ መሆኑ በሁለቱ መልሶች መካከል መፋለስ አለ፡፡

በተራ ቁጥር 2.14 መምህራኑ ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ የማንበብ እድል የሚያገኙት እንዴት እንደሆነ በሚመለከት ለቀረበው መጠይቅ 55.6% "አብዛኛውን ጊዜ"፣ 22.2% "ሁል ጊዜ"፣ 22.2% "አንዳንድ ጊዜ" የሚል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ ከላይ የተገለጸውን ተግባራት በተመለከተ ከተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

*ሠንጠረዥ 10 ፡ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ | የጥያቄው ይዘት | ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % |
| 2.2 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የማንበብ እድል ይሰጣችኋል | | |
| | - ዘውትር | 13 | 11.7 |
| | - አብዛኛውን ጊዜ | 27 | 24.3 |
| | - አልፎ አልፎ | 62 | 55.8 |
| | - አይሰጥም | 9 | 8.1 |
| 2.6 | ባነበባችሁት ጽሑፍ ላይ ከጓደኞቻችሁ ጋር በቡድን እንድትወያዩ ያደርጓችኋል | | |
| | - ሁል ጊዜ | 38 | 34.2 |
| | - አብዛኛውን ጊዜ | 61 | 54.9 |
| | - አልፎ አልፎ | 12 | 10.8 |
| | - አያደርጉም | 0 | 0 |

ከሰንጠረዥ 11 መረዳት እንደሚቻለው መምህራኑ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች እንዲያነቡ እድል እንደሚሰጡ እና እንደሚያወያዩ በሚል ለቀረበው መጠይቅ

የተገኘው 11.7% "ዘውትር"፣ 24.3% "አብዛኛውን ጊዜ"፣ 55.8% "አልፎ አልፎ"፣ 8.1% ደግሞ " አይሰጥም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በሠንጠረዥ 10 በተራ ቁ 2.14 ከቀረበው መጠይቅ የተገኘው ምላሽ 55.6% የሚሆኑ መምህራን አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቹ የማንበብ እድል እንደሚያገኙ ሲመልሱ 55.8% የተማሪዎች ምላሽ "አልፎ አልፎ" ጋር እንደማይመሳሰል መረጃው ያመለክታል፡፡ Williams (1986:42) "የንባብ ትምህርት በተማሪዎች እንጂ በመምህሩ ፈጽሞ መከናወን የለበትም፡፡" ከሚለው ሀሳብ ጋር እንደማይስማማ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ውጤት በምልከታ እንደታየው ከሁለት መምህራን በስተቀር ሌሎች ተጠኚዎች ሲያከናውኑ አልተገኘም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ መምህሩ የሚያነበውን በማዳመጥ ብቻ ይወሰናሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ለንባብ ልምድ ትልቅ እንቅፋት ነው፡፡

መምህራን አብዘኛውን ጊዜ ከማህበረሰቡ ጋር ባላቸው ግንኙነት በሚኖሩበት አካባቢ ለንባባቸው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያደርሱ ነገሮች እንደሚኖሩ ይታወቃል፡፡ ይህን የአካባቢ ተጽእኖ በንባብ ልምድ ላይ ያለው ድርሻ ለመረዳት የሚያስችል ክፍት ጥያቄ ቀርቦ ተጠኚ መምህራን የሰጡት ዝርዝር ከዚህ በታች ባለው መሰረት ቀርቧል፡፡

*ሠንጠረዥ 11፣ በአካባቢያቸው ንባብን የሚያበረታታ/ የሚያደናቅፍ ምን ሁኔታ እንዳለ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ | የጥያቄው ይዘት | የጥያቄው ይዘት |
|---|---|---|
| 2.15 | የሚያበረታቱ ሁኔታዎች | የሚያደናቅፍ ሁኔታዎች |
| | - መንፈሳዊ ትምህርት ቤት መኖራቸው<br>- መጻሕፍት በመዋዋስ ማንበብ<br>- በትምህርት ቤቱ ቤተ-መጻሕፍት መኖር<br>- በመስሪያ ቤቶች የሚመጡ ጋዜጦች መኖራቸው<br>- የተለያዩ የመዝናኛ ቦታዎች አለመኖር<br>- ምንም የሚያበረታታ ነገር የለም | -አየርን ብረት(ሙቀት)<br>-የተለያዩ ሚዲያዎች መስፋፋት<br>-የአካባቢው ማህበረሰቡ ለንባብ ያለው አመለካከት ዝቅተኘነት<br>-የሚነበቡ መጻሕፍቶችን የማግኘት እድሉ ጠባብ መሆን<br>-የመብራት በተደጋጋሚ መጥፋት<br>-በሁለት ፈረቃ መስራትና ድካም<br>-የሕዝብ ቤተ-መጻሕፍት አለመኖር<br>-የተለያዩ ወቅታዊ መጽሔት፣ መጻሕፍት፣ጋዜጦች የሚገኙበት መደብር አለመኖር<br>-አካባቢው የንግድ ቦታ መሆኑና በትርፍ ጊዜ ስራ መጠመድ<br>-የንሮ ውኽርቀት<br>-የጓደኛ ንግግር(ጨዋታ) ወዘተ. |

ከሠንጠረዥ 11 መረዳት እንደሚቻለው፣ ተጠኚዎች ለንባባቸው ባህል መዳበር የአካባቢው ማህበረሰብ አበረታች ወይም ተጽእኖ ፈጣሪ መሆኑን የሚያመለክት

መረጃ የሚጠቁም ነው:: ከላይ በተገለጸው መረጃ መሰረት ንባብን ከሚያበረታቱ ይልቅ የሚያደናቅፉት የሚበልጡ ሆነው ተገኝተዋል:: ይህም አካባቢ በተጠኚዎቹ ላይ ምን ያህል አሉታዊ ተፅእኖ እንዳለው ያሳያል:: ይህንን አስመልክቶ ለትምህርት ክፍል ሀላፊዎች በቀረበው የቃለ መጠይቅ "በመምህራኑ የንባብ ልምድ ላይ ጎልቶ የሚታይ ችግር ካለ ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት የተደረገው ጥረት ምንድነው?" የተገኘው ምላሽ ጎልቶ የሚታይ ችግር አለ፣ ችግሩም መምህራኑ የማንበብ ፍላጎት ቢኖራቸውም መጻሕፍት በአካባቢው አለመገኘት በዋናነት ሲገልጹ፣ በስራው ደስተኛ አለመሆን፣ የኑሮ ሁኔታ፣ የአካባቢ ሁኔታ፣ የማህበረሰቡ ጫና ሌሎቹ ናቸው:: በሁለቱ የክፍለ ትምህርቱ ሀላፊዎች አማካይነት የተሰጠው መፍትሄም በቅርብ ቀን መጻሕፍትን በማሰባሰብ አነስ ያለች የህዝብ ቤተ መጻሕፍት ከፍተን እያንዳንዱ መምህር በውሰት ወስዶ እንዲያነብ ለማድረግ ተነጋግረን ጨርሰናል ሲሉ መልስ ሰጥተዋል::

በምእራፍ ሁለት 2.1.7 Carbo (1991:2) የንባብ ባህል ወይም ልምድ ከሰው ወደ ሰው ይለያያል:: ለልዩነት መፈጠር መነሻ የሚሆኑና አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች አሉ:: እነሱም የሚኖሩበት አካባቢ፣ውስጣዊ የስሜት ሁኔታ፣ ማህበራዊ ፍላጎት እና ስነ-ልቦናዊ ዝንባሌ ናቸው:: በሠንጠረዥ 12 የተገኘው ውጤትም ከዚህ ሀሳብ ጋር ሙሉ በሙሉ ይመሳሰላል::

ሠንጠረዥ 12፡ መምህራኑ የሚያከናውኗቸው ማስተማሪያ ዘዴያቸውን የተመለከመረጃዎች

| ተ.ቁ | የጥያቄው ይዘት | ዘውትር እጠቀማለሁ | | አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ | | አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ | | ፈጽሞ አልጠቀም ም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 3.1 | በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርቱ ሲጀመር ተማሪዎችን አነቃቃለሁ | 15 | 83.3 | 2 | 11.1 | 1 | 5.6 | -- | -- |
| 3.2 | ተማሪዎችን በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ በቡድን፣ በጥንድ የሚያነቡበትን መንገድ እጠቀማለሁ | 5 | 27.8 | 7 | 38.9 | 5 | 27.8 | 1 | 5.5 |
| 3.3 | ተማሪዎቹ ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ ባነበቡት ምንባብ ላይ ተመርኩዘው በቡድን እንዲወያዩ አደርጋለሁ | 3 | 16.7 | 8 | 44.4 | 7 | 38.9 | -- | -- |

በሠንጠረዥ 12 እንደተገለጸው ለጥያቄ 3.1 ለቀረበው ጥያቄ 83.3% "ዘውትር እጠቀማለሁ"፣ 11.1% "ዘውትር እጠቀማለሁ"፣ 5.6% "አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ" በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህ ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠኚ መምህራኑ ምንባቡን ከማስነበባቸው በፊት ተማሪዎችን የማነቃቃትና የማዘጋጀት ተግባራቸው ከፍተኛ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ ውጤት በምልከታ ወቅት ከተገኘው ውጤት ጋር የሚስማማ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ንባብን ለመዝናናት ከሚያነቡ መምህራንና ተማሪዎቻቸውን እንዲያነቡ ከሚያነቃቁ መምህራን መካከል ልዩነት የለም፡፡ ምክንያቱም ለመደሰትና ለእውቀት የሚያነቡ መምህራን ሁልጊዜ ተማሪዎቻቸውን ያነቃቃሉና (McKool &Gespass ፣2009)፡፡

በዚሁ ሠንጠረዥ በተራ ቁጥር 3.3 የቀረበው መጠይቅ 16.7% "ዘውትር እጠቀማለሁ"፣ 44.4% "አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ"፣ 38.9% "አልፎ አልፎ

እጠቀማለሁ" የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ተማሪዎቹ ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ በጉዳዩ ዙሪያ የማወያየት ተግባር የተሰጠውን መልስ ከሠንጠረዥ 9 ጥያቄ ተ.ቁ. 2.12 "አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ" ለሚለው ጥያቄ ከሰጡት መልስ ጋር ማስተያየት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም 61.1% ተጠኚዎች "አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ" ሲሉ የገለጹ ሲሆን፣ በዚህ ግን 38.9% የሚሆኑ ተጠኚዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ከሰጡት ምላሽ ማየት ተችሏል፡፡ ይህም ከሰንጠረዥ 9 ተ.ቁ 2.12 እና ሠንጠረዥ 10 ተ.ቁ 2.6 ከሰጡት ምላሽ ጋር ይዛመዳል፡፡ ነገር ግን ይህ ውጤት በምልከታ ከተገኘው ጋር የሚጋጭ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ መረጃ የተጠኚ መምህራን ተማሪዎች በቀረበ መጠይቅ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል፡፡

*ሠንጠረዥ 13፡ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች*

| ተ.ቁ | የጥያቄው ይዘት | ዘውትር እጠቀማለሁ | | አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ | | አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ | | ፈጽሞ አልጠቀምም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 3.4 | የንባብ ትምህርት ሳስተምር ከመማሪያ መጻሕፍት ውጪ ተጨማሪ መጻሕፍት እጠቀማለሁ | 3 | 16.7 | 2 | 11.1 | 13 | 72.2 | -- | -- |
| 3.5 | ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲያነቡ አበረታታለሁ | 10 | 55.5 | 6 | 33.3 | 2 | 11.1 | -- | -- |
| 3.6 | የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው አጓጊና ሳቢ ጽሑፎች በክፍል ውስጥ አቀርባለሁ | 3 | 16.7 | 6 | 33.3 | 9 | 50 | -- | -- |
| 3.7 | ተማሪዎቹን ከክፍል ውጪ ለሚያደርጉት ንባብ ደረጃቸውን የጠበቀ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ እሞክራለው | 3 | 16.7 | 3 | 16.7 | 9 | 50 | 3 | 16.7 |

የማንበብ ባህሉን ያዳበረ መምህር ለንባብ ትምህርት መስጫነት የሚውለው ጽሑፍ ከተማሪዎች ዳራ እና የክፍል ደረጃ ጋር መመጣጠኑ፣ የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎት ማነሳሳቱን፣ በቅድሚያ በመምህሩ መፈተሽ እና መገምገም እንዳለበት ምሁራን ይመክራሉ፡፡ ይህም ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ እንደ መፅሔት፣ ጋዜጣ፣ መጽሐፍ

እና ያዘጋጁትን ጽሑፍ ለንባብ ማስተማሪያነት እንደ ምንጭነት ቢጠቀሙ የንባብ ትምህርቱ የተሻለ ሊሆን እንደሚችል Celce-murcia (1991:20) ይገልጻሉ፡፡

ይህንን ሁኔታ ተጠኚዎቹ እንደሚያከናውኑት በሠንጠረዥ 14 ተራ ቁጥር 3.4 ለቀረበው መጠይቅ የተሰጠው ምላሽ 16.7% "ዘውትር እጠቀማለሁ"፣ 11.1% "አብዛኛውን ጊዜ"፣ 72.2% "አልፎ አልፎ" መረጃው ያሳያል፡፡ ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲያነቡ አበረታታለሁ ለሚለው መጠይቅ 55.5% "ዘውትር እጠቀማለሁ"፣ 33.3% "አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ"፣ 11.1% "አልፎ አልፎ እጠቀማለው" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው አጓጊና ሳቢ ጽሑፎች በክፍል ውስጥ አቀርባለሁ ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ 16.7% "ዘውትር እጠቀማለሁ"፣ 33.3% "አብዛኛውን ጊዜ"፣ 50% "አልፎ አልፎ" በማለት መልሰዋል፡፡ ተማሪዎቹን ከክፍል ውጪ ለሚያደርጉት ንባብ ደረጃቸውን የጠበቀ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ እሞክራለው፣ ለሚለው ጥያቄ ደግሞ የተሰጠው ምላሽ 16.7% "ዘውትር እጠቀማለሁ"፣ 16.7% "አብዛኛውን ጊዜ" ፣ 50% "አልፎ አልፎ"፣ 16.7% ፈጽሞ አልጠቀምም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ከላይ በጥያቄ ተራ ቁጥር 3.5 የተሰጠው ምላሽ 55.5% "ዘውትር እጠቀማለው" የሚል ምላሽ ሲገኝ በጥያቄ 3.6 ደግሞ 16.7% "ዘውትር እጠቀማለው" ከሚለው የመላሹ መጠን ጋር ይለያያል፡፡ ከዚህ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ በምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ሠንጠረዥ 14፡ከመማሪያ መጻሕፍት ውጪ ለሚቀርቡ ጽሑፎች ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ | የመምህሩ የንባብ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | | ምልከታው የተካሄደባቸው ክፍለ ጊዜያት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | 32 |
| 2 | የቀረበው ጽሐፍ ተማሪዎችን የሚያነሳሱና ደረጃቸውን የጠበቁ | 9 | 50 | 9 | 50 | 32 |
| 3 | የንባብ ትምህርት ሲያስተምሩ ከመማሪ መጻሕፍት ውጪ ተጨማሪ መጻህፍት መጠቀም | 1 | 5.6 | 17 | 94.4 | 32 |
| 4 | ተማሪዎቹን ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲያነቡ ማበረታታት | 1 | 5.5 | 17 | 94.4 | 32 |
| 7 | የንባብ ፍልጎት እንዲያድርባቸው አጓጊና ሳቢ ታሪኮችን ያዘሉ ጽሑፎች መጠቀም | 1 | 5.5 | 17 | 94.4 | 32 |
| 8 | ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ለሚያደርጉት ንባብ ከደረጃቸው ጋር አብሮ የሚሄድ መሆን አለመሆኑን የማረጋገጥ ተግባር | - | - | 18 | 100 | 32 |

በምልከታ ንድፉ በተራ ቁጥር ( 2፣ 3፣ 4፣ 7፣ 8 ) በቀረቡት ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ የሚቀርበው ጽሑፍ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎትና ተነሳሽነት እንዲያድርባቸው ማድረጋቸውን የሚገልጹ ናቸው፡፡ ምልከታው ከተካሄደባቸው ክፍለ ጊዜያት በ 50% መምህራን ለእለቱ የንባብ ትምህርት ባቀረቡት ጽሐፍ ተማሪዎችን የሚያነሳሱና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሌሎቹ 50% ክፍለ ጊዜያት ግን በቀረበው ጽሑፍ ተማሪዎችን የሚያነሳሱና ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ ነገር ግን በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተጠቀሰው፣ የንባብ ባህሉን ያዳበረ መምህር በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙት ፅሑፎች የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያነሳሳና ሳቢ ሊሆኑ

የሚችሉ መሆን እንዳለበት Nuttal (1982:148) ፣ Celce- Marcia (1991:20 ) Dubin and David (1991:196) May (1990:11) ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጂ በአንዳንድ የመማር ማስተማር ክፍሎች ይህ ሁኔታ አለመታየቱ በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በመጠይቁ ሠንጠረዥ 14 ጥያቄ (ቁጥር 3.4 ፤3.5፤ 3.6) እና በምልከታ ንድፉ በተራ ቁጥር 3 እና 4 ላይ የቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች እንደሚያሳዩት ተጠኚ መምህራኑ ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ ተጨማሪ ሳቢና አጓጊ መጻሕፍትን የሚጠቀሙ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ እንዲሁም ለተማሪዎች ከቀረበው መጠይቅ የተገኘው ውጤት 43% ያህሉ መምህራን ተጨማሪ ጽሑፎችን በክፍል ውስጥ እንደሚጠቀሙ አረጋግጠዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ውጤት በምልከታ ከተገኘው ውጤት ጋር ሲጋጭ ይታያል፡፡ ምክንያቱም ከምልከታ የተገኘው ውጤት ሲከናወን የታየው በአንድ መምህር 5.56% ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ከመማሪያ መጻሕፍት ውጭ ሌላ ተጨማሪ ጽሑፎች አለመጠቀማቸውን ውጤቱ ያረጋግጣል፡፡ በሰንጠረዥ 13 ጥያቄ ቁጥር 3.6 ከተሰጠው ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ለተማሪዎቹ ከክፍል ውጪ ለሚያደርጉት ንባብ ደረጃቸውን የጠበቀ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ የሚያደርጉት ጥረት ዝቅተኛ እንደሆነ ነው ፡፡ ይህ ውጤት በምልከታ ወቅት ከተገኘው ውጤት ጋር የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

*ሠንጠረዥ 15፡መምህራን ተማሪዎቹን እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው የሚያሳይ ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች*

| ተ.ቁ | የጥያቄው ይዘት | ዘውትር እጠቀማለሁ | | አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ | | አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ | | ፈጽሞ አልጠቀምም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 3.8 | የአንድን ጽሑፍ መልእክት ለመረዳት የሚያግዙ ጠቃሚ ዘዴዎችን ለተማሪዎች እነግራለሁ | 6 | 33.3 | 11 | 61.1 | 1 | 5.6 | -- | -- |
| 3.9 | ተማሪዎቹ ከምንባቡ ያገኙትን ሃሳብ /ጭብጥ/ እንዲናገሩ አደርጋለሁ | 7 | 38.9 | 8 | 44.4 | 3 | 16.7 | -- | -- |

በሠንጠረዥ 15 እንደተገለጸው በጥያቄ ቁጥር 3.8 ለቀረበው መጠይቅ፣ 33.3% "ዘውትር እጠቀማለሁ"፣ 61.1% "አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለው"፣ 5.6% "አልፎ አልፎ እጠቀማለው" የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ተማሪዎቹ ከምንባቡ ያገኙትን ሃሳብ /ጭብጥ እንዲናገሩ /እንዲጽፉ አደርጋለሁ ለሚለው መጠይቅ የተሰጠው 38.9% "ዘውትር እጠቀማለሁ"፣ 44.4% "አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለው"፣ 16.7% "አልፎ አልፎ እጠቀማለው" የሚል ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው የአንድን ጽሑፍ መልእክት ለመረዳት የሚያግዙ ጠቋሚ ዘዴዎችን ለተማሪዎች የሚያደርጉት በመካከለኛ ደረጃ እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ውጤት በምልከታ ወቅት ከሁለት መምህራን ውጪ ሌሎች ሲያከናውኑ አልታየም፡፡ በጥያቄ ቁጥር 3.9 የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው ተጠኚ መምህራን ተማሪዎቹን ከምንባቡ ያገኙትን መልእክት እንዲገልጹ ከማድረግ አንፃር ጥሩ እንደሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን በምልከታው ከተገኘው ውጤት ጋር እንደማይመሳሰል መረጃው ያሳያል፡፡ ይህንንም ለማረጋገጥ በምልከታ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ሠንጠረዥ 16 መምህራኑ የምንባቡን መልእክት እንዲረዱ የተጠቀሙበት ዘዴ ከምልከታ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ | የመምህሩ የንባብ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | | ምልከታው የተካሄደባቸው ክፍለ ጊዜያት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | 32 |
| 5 | የአንድን ጽሑፍ መልእክት ለመረዳት የሚያግዙ ጠቋሚ ዘዴዎችን መጠቀም | 2 | 11.1 | 16 | 88.9 | 32 |
| 10 | መረጃዎችን ለይቶ ለማውጣት የገረፍታ ንባብ የማድረግ ስራ | 6 | 33.3 | 12 | 66.7 | 32 |
| 15 | ተማሪዎች የጽሑፉን መልእክት መረዳታቸውን ለማወቅ ጥያቄ የመጠየቅ | 16 | 88.9 | 2 | 11.1 | 32 |

በሰንጠረዥ 16 እንደተመለከተው የአንድን ጽሁፍ መልእክት ለመረዳት የሚያግዙ ጠቋሚ ዘዴዎችን መጠቀም በሚመለከት ምልከታ ከተካሄደባቸው ክፍለ ጊዜያት 11.1% መምህራን እንደተከናወነ ታይቷል፡፡ በተቀሩት 88.9% ክፍለ ጊዜያት ደግሞ እነዚህን ዘዴዎች አለመጠቀማቸው ታይቷል፡፡ ነገር ግን May (1990:40)

እና Millan (1991:48) የማንበብ ልምድ ያለው መምህር ለተማሪዎቹ የምንባቡን መልእክት ለመረዳት የሚያግዙ ጠቋሚ ዘዴዎች ስነ አገባባዊ ጥቆማ፣ ስነ መዋቅራዊ ጥቆማ፣ ስነ-ድምጻዊ ጥቆማ፣ ባህላዊ ጥቆማና ዳራዊ ጥቆማ ተማሪዎች ምንቡን ከማስነበባቸው በፊት መጠቆም እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጂ በአብዛኞቹ ክፍለጊዜያቶች በመምህራኑ ይህ ተግባር እንዳልተከናወነ በምልከታው ከተገኘው ውጤት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዚሁ ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር 1.10 እና 1.15 የቀረበው ጥያቄ መረጃዎችን ከምንባቡ ለይቶ ለማውጣት የገረፍታ ንባብ የማድረግ ተግባር በተመለከተ በ 33.3% ክፍለ ጊዜያቶች እንደሚከናወኑ ታይቷል፡፡ በ66.7% ክፍለ ጊዜያት ግን እንዳልተከናወኑ በምልከታው ተረጋግጧል፡፡ ተማሪዎች የጽሑፉን መልእክት መረዳታቸውን ጥያቄ የመጠየቅ ተግባርን በሚመለከት በ88.9% ክፍለ ጊዜያት መምህራኑ ተማሪዎቻቸው ያነበቡትን ጹሑፍ መልእክት መረዳት አለመረዳታቸውን ለመፈተሽ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደሚጠቀሙ የምልከታው ውጤት ያመለክታል፡፡ ይህ ውጤት በሰንጠረዥ 15 ተራ ቁጥር 3.9 ከተገኘው ውጤት ጋር በአብዛኛው የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

*ሰንጠረዥ 17፡ የንባብ አይነቶችን በተመለከተ ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

| ተ.ቁ | የጥያቄው ይዘት | ዘውትር እጠቀማለሁ | | አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ | | አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ | | ፈጽሞ አልጠቀምም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 3.10 | በክፍል ውስጥ ምንባብ የማስነብበው በለሆሳስ ነው | 5 | 27.8 | 5 | 27.8 | 7 | 38.9 | 1 | 5.5 |

ከሠንጠረዥ 17 ተራ ቁጥር 3.10 እንደምንረዳው በክፍል ውስጥ ምንባብ የማስነብበው በለሆሳስ ነው፣ለሚለው ጥያቄ 27.8% "ዘውትር እጠቀማለሁ"፣ 27.8% "አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ"፣ 38.9% "አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ" የሚል ምላሽ

ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ውጤት መረዳት የሚቻለው ንባብን በለሆሳስ ማስነበብን በአብዛኞቹ በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚተገብሩ ውጤቱ ያሳየናል፡፡ በተጨማሪም ለተማሪዎች ከቀረበው መጠይቅ የተገኘው ውጤትም ከዚህ ውጤት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

*ሠንጠረዥ 19 ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ | የጥያቄው ይዘት | ዘውትር ይጠቀማሉ | | አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ | | አልፎ አልፎ ይጠቀማሉ | | ፈጽሞ አይጠቀሙም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 3.3 | መምህሩ ንባብን በግል በለሆሳስ እንድታነቡ ያደርጓችኋል | 8 | 7.2 | 31 | 27.9 | 48 | 43.2 | 17 | 15.3 |

በሰንጠረዥ 18 እንደተመለከተው ተጠኚ መምህራኑ ንባብን በግል በለሆሳስ እንዲያነቡ ስለማድረጋቸው 7.2% ተማሪዎች "ዘውትር"፣ 27.9% ተማሪዎች "አብዘኛውን ጊዜ"፣ 43.2% ተማሪዎች "አልፎ አልፎ"፣ 15.3% ተማሪዎች "ፈጽሞ አይጠቀሙም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በዚህ መረጃ አብዛኞቹ መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ንባብን በግል በለሆሳስ እንዲያነቡ ማድረጋቸውን ያመለክታል፡፡ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃም ሆነ ከመምህራን የተገኘው ውጤት ተመሳሳይነት አለው፡፡ ነገር ግን ከምልከታ ክንውኑ ከሁለት 11.1% መምህራን ውጪ ሌሎች ሲያከናውኑ አልታየም፡፡ ይህም በሰንጠረዥ 10 ተ.ቁ 2.13 እና 2.14 ከሰጡት ምልሽ ጋር ይዛመዳል፡፡ ይህን አስመልክቶም ከምልከታ የተገኘው መረጃም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

*ሠንጠረዥ 19 ንባብን ደቂቃ በመወሰን የማንበብ ተግባር በክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ | የመምህሩ የንባብ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | | ምልከታው የተካሄደባቸው ክፍለ ጊዜያት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | 32 |
| 9 | በክፍል ውስጥ ፅሑፎች የሚነበቡት በሰአት በተመጠነ ፍጥነት | 2 | 11.1 | 16 | 88.9 | 32 |
| 11 | ለንባቡ ጊዜ ወስነው (ደቂቃ ወስነው) የማንበብ ተግባር | 2 | 11.1 | 16 | 88.9 | 32 |

በምልከታ ተራ ቁጥር 9፣11 የተጠቀሱ ተግባራት መምህራን የንባብ ልምዳቸውን ተጠቅመው የተማሪዎቹን የንባብ ፍጥነት ለመረዳት ለምንባቡ ጊዜ (ደቂቃ) ወስነው እንደማያለማምዱ በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የክንውኖቹን አተገባበር ለማየት በተካሄደ ምልከታም በአብዛኛው 88.9% ክፍለ ጊዜያት ለምንባቡ ጊዜ (ደቂቃ) ወስነው እንደማያስነብቡ ለማየት ተችሏል፡፡

ቀደም ሲል በክፍል 2 እንደተጠቀሰው የንባብ ልምድ ያለው መምህር የተማሪዎቹን የንባብ ፍጥነት ለማሻሻል ጥረት ያርጋል፡፡ ይህን በማድረግ የተማሪዎቹን የንባብ ክሂል ማሳደግ ይችላል፡፡ ነገር ግን በምልከታው ሂደት በመማር ማስተማር ክፍሎቹ የታዩት ድክመቶች አብዛኛው መምህራን ይህንን አለማድረጋቸው በተማሪዎች የንባብ ፍጥነት መዳበር ላይ ተፅዕኖ ማሳደራቸውን ሊታወቅ ይገባል፡፡

*ሠንጠረዥ 20 ፡ ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር በማገናኘት የማንበብ ተግባርከምልከታ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ | የመምህሩ የንባብ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | | ምልከታው የተካሄደባቸው ክፍለ ጊዜያት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | 32 |
| 13 | ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያያይዙት ማድረግ | 6 | 33.3 | 12 | 66.7 | 32 |

በሰንጠረዥ 20 በተራ ቁጥር 13 በቀረበው መምህራኑ ተማሪዎችን ምንባቡን ተመርኩዘው ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር በማዋሃድ በቡድን ማወያየት በሚመለከት የቀረቡ ተግባራት ናቸው፡፡ ነገር ግን የክንውኖቹን አተገባበር ለማወቅ በተካሄደው ምልከታ በ 33.3% ክፍለ ጊዜት የቡድን ውይይት እንደሚያደርጉ ለማየት ተችሏል፡፡ በተቀሩት 66.7% ክፍለ ጊዜያት ግን ተማሪዎቹ ያነበቡትን ጹሑፍ አስመልክተው ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር በማገናኘት በጥንድም ሆነ በቡድን ውይይት እንደማያደርጉ ታውቋል፡፡ በአንጻሩ ግን በክፍል 2 ላይ እንደተገለጸው፣ ዓለም (2001፡68) መምህራን ለማስተማር የሚያነቡት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ መጻሕፍትን ማንበብ እንዳለባቸው ሁሉ፣ ተማሪዎቹንም ክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ በቡድን የሚያነብቡትን በቀላሉ ማመቻቸት ይችላሉ በማለት ነበር የገለጹት፡፡ የጥናቱ ተተኳሪዎች ግን በተወሰነ ደረጃ ብቻ ይህንን ትግበራ እንደሚያከናውኑ በምልከታው እንደታየው ሁሉ የጽሑፍ መጠይቁ ውጤትም ያረጋግጣል፡፡

ባጠቃለይ በመምህራኑ የንባብ ባህልና ንባብ ትምህርትን የማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዳለ በዚህ ጥናት ተፈትሿል፡፡ ይህም ግንኙነት እንዳላቸው በመቶኛ ስሌት በመጠቀም አዎንታዊ ግንኙነት መኖሩን አመልክቷል፡፡ ይህም ውጤት የመምህሩ የንባብ ባህል ንባብን ለማስተማር በሚጠቀሙበት ዘዴያቸው ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ፈጣሪ እንደሆነ አድምታ ያለው ይመስላል፡፡ ውጤቱም በምዕራፍ ሁለት በተ.ቁ 2.1.8 እና በተ.ቁ 2.1.3 እንደተብራራው አንድ መምህር የንባብ ልምድ ካለው በክፍል ውስጥ ለማስተማሪያነት የሚጠቀምበት ዘዴ ለተማረዎቹ እገዛ ያደርጋል፡፡ መምህራን የተማሪዎቹ የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ብሎም የማንበብ ልምድ ማዳበር እንዲችሉ ከፍላጎታቸውና ከደረጃቸው ጋር አብረው የሚሄዱትን ለይተው መምረጥና መጠቆም ይገባል፡፡ ይህም ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ እንደ መፅሔት፣ጋዜጣ ፣መጽሐፍ እና ያዘጋጁትን ጽሑፍ ለንባብ ማስተማሪያነት እንደ ምንጭነት ቢጠቀሙ የንባብ ትምህርቱ የተሻለ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም መምህሩ ለተማሪው ተፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ ከተማሪው በላቀ ሁኔታ የንባብ ልምድ ያካበተ ሊሆን ይገባል፡፡ የማንበብ ልምድ የሌለው መምህር ተማሪዎችን በተፈለገው መንገድ የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው አያደርግም (Celce-murcia 1991:20፣ አለም 2001፡67) በማለት የመምህሩ የንባብ

ንባብን ማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ዝምድና ለማስገንዘብ ከተሰጠው ሀሳብ
ተመዳል።

ም በተ.ቁ 2.1.9.1 ብቁ አንባብያን ቀደም ሲል ካነበቡት ወይም ካለፈ
፣ ትምህርትና የሕይወት ገጠመኝ በመነሳት ከቀረበው ጽሑፍ ባሻገር ጉዳዩን
ት መመልከት፣ትንታኔ መስጠት የሚችሉ ናቸው። በመሆኑም አንባቢው
ው ጉዳይ ተነስቶ የራሱን ፍቺ፣ ሐሳብና አስተያየት የመስጠት ችሎታውን
፤ የሚችል መሆኑን Niles (1972) ይገልጻሉ።

# ምእራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በከምባታ ጠምበሮ ዞን በ6 መሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የንባብ ባህል ከማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡

ጥናቱ የተካሄደው በ2005 ዓ.ም በዱራሜ፣ በሺንሺቾ፣ በሀደሮ፣ በአንጋጫ፣ በዳንቦያ፣ በዶዮገና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ 18 መምህራን በጠቅላይ ናሙና ስልት ነው፡፡ አብይ አላማውን ከግብ ለማድረስ አራት ንኡሳን አላማዎች ተነድፈዋል፡፡ ከተነደፉት ዓላማዎች ጋር ዝምድና ያላቸው ንድፈ ሀሳቦች በምእራፍ ሁለት ቀርበዋል፡፡ በምእራፍ ሶስትም የአጠናኑ ሂደት ተገልጿል፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች (የጽሑፍ መጠይቅ፣የክፍል ምልከታ፣ቃለ መጠይቅ) የተዘጋጁበት ስልት እና የአተናተን ዘዴው ተብራርቷል፡፡ በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደየዝምድናቸው ተቀናጅተው በምእራፍ አራት ስር ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ አካል በሆነው የገላጭ ስልት ተተንትነዋል፡፡ በትንተናው የተገኙ ውጤቶችም እንደሚከተለው ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

## 5.1 ማጠቃለያ

- ❖ ንባብ ባህል የሚሆነው፣ ለንባብ ፍላጎት ሲኖርና እሱም ተግባራዊ ስናደርግ ነው፡፡ ይህም መሰረት የሚጣለው በወላጆች፣ በትምህርት ቤቶች እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ግኝት ፍላጎትና ተግባር እንደማይገናኙ ከጽሁፍ መጠይቁ ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ምንም እንኳን 66.6% የሚሆኑ መምህራን ከስራ ውጪ በየቀኑ እንደሚያነቡ መግለጻቸው ጥሩ ቢሆንም አብዛኞቹ ግን የማንበብ ፍላጎታቸውና የንባብ ልምዳቸውን ለማዳበር የሚጠቀሙበት ጊዜ አለመጣጣሙ ከጥናቱ ግኝት መገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የብዙዎች መምህራን የንባብ ባህል አመርቂ አይደለም፡፡

❖ በሌላ በኩል ደግሞ ለመምህራኑ የንባባቸው ባህል መዳበር አካባቢው አዎንታዊ/አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡ ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው የአካባቢው ማህበረሰብ ለንባብ ያለው አመለካከት ዝቅተኝነት፣ የሚነበቡ መጻሕፍትን የማግኘት እድሉ ጠባብ መሆን፣የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት አለመኖር፣ የንግድ ቦታ መሆኑና በትርፍ ጊዜ ስራ መጠመድ ወዘተ አካባቢው ንባብን ከሚያበረታቱ ይልቅ የሚያደናቅፉት የሚበልጡ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም አካባቢው በንባብ ባህል መዳበር ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳላቸው ያሳያል፡፡

❖ በክፍል ውስጥ ንባብ ከማስተማራቸው በፊት በምን መልኩ እየተገበሩት እንደሆነ በጥናቱ ተዳሶ፣ መምህራኑ ምንባቡን ከማስነበባቸው በፊት ተማሪዎችን የማነቃቃትና የማዘጋጀት ተግባራቸው ከጽሑፍ መጠይቅ እና ከምልከታ የተገኘው መረጃ ደካማ እንደሆነ ያመላክታል፡፡

❖ መምህራኑ ንባብን ለማስተማር ከመማሪያ መጻሕፍት ውጭ የራሳቸውን ጽሑፍ በማዘጋጀት ረገድ ደካማ እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡ ይህም መረጃ በተደጋጋሚ በተካሄደው ምልከታ የተገኘው ውጤት ሲከናወን የታየው በአንድ መምህር ብቻ እንደሆነ ነው፡፡

❖ አብዛኛዎቹ መምህራን የንባብ ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴያቸው ደካማ አተገባበር እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ነገር ግን የተወሰኑ መምህራን የንባብ ልምዳቸውን ተጠቅመው እንደሚያስተምሩ ከጽሑፍ መጠይቁ እና በምልከታ የተገኘው መረጃ አመልክቷል፡፡ በመምህራን የንባብ ባህልና ንባብን የማስተማረያ ዘዴያቸው ጋር ያለው ግንኙነት ትልቅ አዎንታዊ ተዛምዶ አለው፡፡ ይህም አዎንታዊ የንባብ ባህል ያላቸው መምህራን የተሻለ ንባብን የማስተማሪያ ዘዴ ይተገብራሉ የሚል አድምታ ያለው ቢመስልም የንባብ ባህላቸው ዝቅተኛ የሆኑ መምህራን ንባብን የማስተማሪያ ዘዴያቸው ዝቅተኛ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል፡፡

❖ የንባብ ባህል እንዲዳብር ለማድግ መጀመሪያ የንባብ ፍላጎት መኖር አለበት ፡፡ ፍላጎት ካለ ንባብ ቀስ በቀስ ሂደታዊ በሆነ መልኩ እየተደጋገመ ሲመጣ ባህል ይሆናል፡፡ ይህን አስመልክቶ ንባብን ለማዳበር መምህራን ምን ማድረግ እንለባቸው ከጽሐፍ መጠይቁ የተገኘው አብዘኞቹ በየቀኑ

ነው፡፡ ይህንንም በጎ ስራ የንባብን ባህል ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት በሁሉም መምህራኖች ዘንድ እንዲሰርጽ ሌሎች መረሃ ግብሮች ቢዘረጉና ውይይትና ቅስቀሳ የሚያደርጉበት መንገድ ቢመቻችላቸው፤

- ✓ ጊዜን በአግባቡ በመጠቀም ለንባብ ባህል የጀርባ አጥንት ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን ለሌሎች ጉዳዮች ጊዜ ሲኖራቸው ለንባብ ግን ጊዜ እንደማይበቃቸው ይናገራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ለማንብብ ፍላጎቱ ካለን በቀን ጊዜ ወስነን ብናነብ ለወደፊቱ ጥሩ አንባቢ ስለሚወጣን ለጊዜ አጠቃቀማችን ገደብ ብናበጅለት፤
- ✓ የመምህራን የንባብ ባህል ለክፍል ውስጥ ንባብን የማስተማሪያ ዘዴያቸው ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽእኖ፣ ለተማሪዎቹ የንባብ ትምህርት አቀባበል ላይ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡ ይህንንም ለመቅረፍ መምህራን ከተማሪዎች በማንኛውም ነገር ቀድሞ መገኘት አለባቸው፡፡ ከዚህ አኳያ መምርራት ከመማሪያ መጽሐፉ ውጪ ንባብን የሚያስተምሩበት ጽሐፍ የሚያዘጋጁበትን የተለያዩ መጻህፍት፣ጋዜጣ፣ መጽሔት ወዘተ በየትምህርት ቤቶቹ ቤተ መጻሕፍት እንዲገኙ፤ የሚመለከታቸው ወገኖች ትምህርት ሚኒስተር፣ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ይህንን መረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከነሱ የሚጠቀሙበትን ድርሻ በመወጣት ጥረት ቢያደርጉ፤
- ✓ አንድ መምህር የንባብ ልምድ ካለው በክፍል ውስጥ ለማስተማሪያነት የሚጠቀምበት ዘዴ ለተማሪዎቹ የንባብ ባህል መዳበር እገዛ ስለሚያደርግ መምህራን የንባብ ባህላቸው እንዲዳብር የሚያነቡበት ጊዜና ቦታ በየትምህርት ቤቱ አስተዳደር ትኩረት እንዲጡ ቢደረግ፤
- ✓ የንባብ ባህል እንዲያድግ መምህራን ብቻ ሳይሆን እንዳንዱ ግለሰብ ዋጋ ሊከፍል የግድ ነው፡፡ መፃሕፍት የሚገዙ ነገሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም ጥሩ አንባቢ ብቻም ሳይሆን፣ የንባብ ባህሉን ለማዳበር የአንባቢዎች አስተዋጽኦ እጅጉን ወሳኝ በመሆኑ መምህራን በክፍል ውስጥ ንባብን ሲያስተምሩ መማሪያ መፃህፍትን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ጽሑፎች፣ አጋዥ መጻሕፍቶች፣ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች ወዘተ እንዲጠቀሙበት በበቂ ሁኔታ በየትምህረት ቤቶች እንዲኖሩ ቢደረግ፤

- ✓ በመጨረሻም በዚህ ጥናት የመምህራን የንባብ ፍላጎት በአብዘኛው ጥሩ መሆኑ ቢረጋገጥም የዳበረ የንባብ ባህል ስለሌላቸው የንባብ ባህላቸውና የንባብ ክሂልን ማስተማሪያ ዘዴያቸው ሲፈተሽ ዝቅተኛ መሆኑ ታይቷል፡፡ ስለዚህ የንባብ ባህል በድግግሞሽ የሚመጣ ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ ጊዜ የምናካብተው የንባብ ባህል ተደርጎ ሊታይ አይገባም፡፡ የንባብ ባህል ይዳብር ዘንድ መምህራኑ ሁልጊዜ ከመጽሐፍት ጋር የሚገናኙበትን መንገድ መሠረት መጣል ያስፈልጋል፡፡ ይህንን መሠረት የመጣል ኃላፊነት ደግሞ ትምህርት ቤቶች ብቻ የሚሸከሙት አይደሉም፡፡ እራሱ መምህሩ ወላጆችም፣ ሌሎች ሀላፊነት ያለባቸው ወገኖች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ፍላጎትን ወደ ተግባር ለመለወጥ እና የንባብ ባህላቸው ንባብን ለማስተማሪያ ዘዴያቸው ከፍተኛ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዲፈጥር በማድረግ ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ከመጻህፍት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በጠነከረ ሁኔታ በቂ ልምምድ ቢያደርጉ መልካም ነው፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


ማስተዋል ውበቱ፤(1989)፡፡ "የከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ፡-በአዲስ አበባ የሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ናሙናነት"፡፡ ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)፡፡

ምሕረቱ ጴ.ጉታ፤(1999)፡፡ *የንባብ ባህልና ቤተ ክርስቲያን*፡፡አዲስ አበባ፤ፊንፊኔ ማተሚያና ፐብልሽንግ ፡፡

በጎሰው የሸዋስ፤(2003)፡፡ "በአዲስ አበባ በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ ነባርና ጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ክሂል አተገባበር ንጽጽር፡፡" ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ፤ (1981)፡፡ *"ሥነ- ልሳን እና ቋንቋ ማስተማር"* ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ (ያልታተመ)፡፡-

ተክላይ ትእዛዙ፤(2000)፡፡ "በትግርኛ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የንባብ ብልሃት አጠቃቀም እና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥሞ ፍተሻ- በአክሱም ከተማ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መነሻነት" ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)፡፡

አለም እሸቱ፤ (2001)፡፡ "የወጣቶች የንባብ ልምድ ፍተሻ በአዲስ አበባ ወጣቶች መነሻነት፡፡" *መድብለ ጉባኤ* ፡አዲስ አበባ፤የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ኅትመት (ገጽ 60-79)፡፡

የኔሰው ደሴ፤ (1990)፡፡ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክረቧዊ በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽዖ፡፡" ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ፤ (1998)። *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር።*አዲስ አበባ፡ አልፋ አታሚዎች።

ደረጀ ገብሬ፤ (2009) ። "የንባብ ልምድ ቅኝት - በአዲስ አበባ።" *The Ethiopian Journal of Education*. Institute of Educational Research, Addis Ababa University, vol. xxix, no.2 pp.69-98.

ወንድ አጥር ደነቀ፤ (1993)። "በማስተማሪያ ቋንቋነት በኦሮምያ ክልል ለአራተኛ ክፍል የተዘጋጀ የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ተገቢነት።" ኤም.ኤ.ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)።

Birhanu Tefera.(1999)."Leisure Reading and Readership of Books: with Reference to some Literate Group in Bahir Dar." *Ethiopian Journal of Language and Literature*; No.9,Institute of Language Studies, AAU printing Press.

Carbo, M. (1991). *Teaching students to read through their individual learning style*. Boston Allyn and Bacon.

Celce- Murica, M.(1991). *Teaching English as a second language* . Boston: Heinle and Heinle publishers.

Conley M. w.(1992). *Contents Reading Instruction*: A communication Approach. New York: CUP.

Cooper, J.D.(1997). Literacy: Helping Children Construct Meaning.(3rd ed). Boston & New York: Houghton Mifflin Company.

Charles A.P(1985). *Reading Ability*. New York: Oxford University press.

Davies, F. (1995). *Introducing Reading*. England: clays Ltd.

Dawson, A.M (1963).*Fundamentals of basic reading* . David mky Company, Inc.

Dubin, F. & David, B.( 1991). “Academic Reading and the ESL/ EFL Teacher” in Celce Murcia (ed.) (1991) *Teaching English as second or Foreign language.* Heinle and Hainle Publishers.

Gerla, Jacqueline P. (2009).Case study: Jill, a pre-service teacher becomes a reader. *Southeastern Teacher Education Journal,* 2 (2), pp:145-152.

Grellet, F.(1981). *Developing Reading skills* .Cambridge: Cambridge University Press.

Harmer, J.(1991). *The practice of English Language Teaching.* Hong Kong: Heinemann Educational.

----------------. (2001). *The practice of English Language Teaching.* Oxford: Pearson educational limited.

Kozol, J. (no date). *Why Is Reading Important?* Retrieved October 19, 2013, from http://www.learn-to-read-prince-george.com/why-is-reading important.html

May, BF.(1990). *Reading as Communication an interactive approach.* (3rd ed) New York: Macmillan publisher Company

Millan, D. (1991). *Developing Reading Skills.* New York: CUP.

McKool, S. S. & Gespass, S. (2009). “Does Johnny's reading Teacher love to read? How teachers' personal reading habits affect instructional practices.” *Literacy Research and Instruction,* 48, 264-276.

McDonough, Jo. & Shaw, C.(2003). *Materials & Methods in ELT.* Oxford: Oxford University Parses.

Morrison, T.G. et.al.(1999). "Do teachers who read personally use recommended literacy practices in their classrooms?" *Reading Research and Instruction,* 38(2), 81-100.

Niles, Olives.(1972). "Reading skills common to the content Arius" In Melnik Amelia and John inerritt. (ed). *The reading curriculum.* Eynesbury: the Open University press, pp: 27-40.

Nuttall, C. (1982). *Teaching Reading skill in a foreign language.* London: Heinemann educational Books.

----------------. (2000). *Teaching Reading skill in a foreign language.* London: Heinemann educational Books.

Omaggio, Alice (1983) "Methodology in Transition: The new focus on proficiency." *The modern Language Journal.* 67/4 pp.330-341.

Richards, J. & Nunan, D.(1990). *Second Language Teaching Education.* Cambridge: Cambridge University Press.

Scott, J. E.(1996).Self-efficacy: A key to literacy learning. *Reading Horizons,*36, 195-213.

Sheng, H. J. (2000). *A Cognitive model for teaching reading compression.* forum, 38(4), pp.12-15.

Sheal, P. (1989). "Classroom Observation Training the observers." *ELT Journal.* 43(2).92-103.

Smith, E. (1997).*How Children Learn to Read.* London: Addison Wesley Longman New Zealand Limited.

Silberstein, S. (1994).*Techniques and resources in teaching Reading*: Oxford: Oxford University Press.

Sulentic- Dowell, et.al.(2006).How do Literacy experiences affect the teaching propensities of elementary per-service teachers? *Reading psychology*, 27,235-255.

Somerset Maugham, W. (no deat). *Efficient reading skills.* Retrieved October 23, 2013, from http://www.stenhouse.com/shop/pc/viewprd.asp?idProduct=9182

Ur, P. (1996). *A Course in Language: Practice and Theory.* Cambridge: Cambridge University Press.

Wallace, C. (1992). *Reading*. Oxford: Oxford University Press Wallace, C. (1992). *Reading*. Oxford: Oxford University Press.

Watson, P. & Elliot, S. (2007). “School” reading and multiple texts: Examining the meta cognitive development of secondary-level preserve teachers. *Journal of Adolescent & Adult literacy*, 51(2), 150-162.

Weir, C. & Robert, J.(1994). *Evaluation in ELT*. Oxford: Black well Publishers.

Williams, E. (1984). *Reading in the language classroom*. London: Macmillan publishers.

Williams, R. (1986). Reading in a Foreign Language. *English language Teaching Journal,* XXIX(1),46-52.

Zint, V.M.(1976).The Reading Process: the Teacher & the Learner.(2nd ed.). Lowa: W.M.C. Brown Company Publishers.

# አባሪዎች

አባሪ አንድ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲ፣የቋንቋዎች ጥናት ፣የጆርናሊዝም የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በ12ኛ እና 11ኛ ክፍል ተጠኚ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

በዚህ ጥናት ዓላማ የመምህራኑ የንባብ ባህል ከክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ዘዴው ጋር ያለውን ግንኙነት ለማወቅ የሚረዳ የመረጃ መሰብሰቢያ ነው፡፡

ውድ መምህር!ጥናቱ የታለመለትን ግብ በትክክል ሊመታ የሚችለው ትክክለኛውን መረጃ ከእርስዎ ማግኘት ሲቻል በመሆኑ ለእያንዳንዱ መጠይቅ ትክክለኛውን መረጃ እንዲሰጡኝ እጠይቃለሁ፡፡ ይህን መጠይቅ ለመሙላት ውድ ጊዜዎን ሰውተው ለሚያደርጉልኝ ትብብር ሁሉ በቅድሚያ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ለመጠይቁ የመሰጡት መልስ ምስጢራዊነት እንደተጠበቀ ሆኖ በመጠየቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

ክፍል አንድ

1.አጠቃላይ መረጃ

1.1 የትምህርት ቤት ስም_______________________

1.2 የክፍል ደረጃ______________________

1.3 ጾታ___________ 1.4 ዕድሜ_____________ 1.5 የትምህርት ደረጃ___________ 1.6 የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት ሀ.ዋና______________________ ለ. ንኡስ__________________

1.7. የአገልግሎት ዘመን_______________________

ክፍል ሁለት

2.የመምህራኑን የንባብ ባህል አጠቃላይ መረጃን በሚመለከት የቀረበ ጥያቄ፡፡

መመሪያ፡-ከዚህ ቀጥሎ ለተሰጡት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች ምላሽ ነው ብለውየሚስማሙበትን ሀሳብ የያዘውን ፊደል በማክበብ ያመልክቱ፡፡

2.1 እርስዎ አንባቢ የሚሉት እንዴት ያለ ሰው ነው?

ሀ.በእረፍት ጊዜው መጽሐፍ የሚያነበውን

ለ. ለማንበብ ጊዜ የማይወስነውን

ሐ.የሚነበቡ መፃህፍቶች ከእጁ የማይለየውን

መበሚያነቡበት ጊዜ ፊታቸው ላይ የመጨነቅ ስሜት የማይታይባቸውን

ሠ.ሌላ ካለ______________________________

2.2 .ያንባብ ባህልዎ ምን ይመስላል?

ሀ. ሁል ጊዜ አነባለሁ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ አነባለሁ

ሐ. አልፎ አልፎ አነባለሁ

መ.ፈጽሞ አላነብም

2.3 በቀን ለምን ያህል ሰዓት የማስተማር ስራ ይሰራሉ?

ሀ.ለስድስት ሰአት

ለ.ለሰባት ሰአት

ሐ.ለአራት ሰአት

መ.ለአምስት ሰአት

ሠ.ሌላ ካለ______________________________

2.4 በእረፍት ጊዜዎ በቀን ለምን ያህል ሰአት ያነባሉ?

ሀ.ለአርባ ደቂቃ

ለ.ለአንድ ሰአት

ሐ.ለሁለት ሰአት

መ.ለስድስት ሰአት

ሠ ሌላ______________________________

2.5 የንባብ ልምድዎ በአማካይ እንዴት ይገለፃል

ሀ.በሳምንት አንድ መጽሐፍ

ለ.በወር አንድ መጽሐፍ

ሐ.በወር ሁለት መፅሐፎች

መ.በአገኘሁት አጋጣሚ

ሠ.ሌሎች ____________________

2.6 እርስዎ ምን አይነት ፅሑፍ ነው የሚያነቡት ?(ከአንድ በላይ መምረጥ ይቻላል)

ሀ. ልብ- ወለድ

ለ. የሀይማኖት መፃሕፍት

ሐ. ጋዜጣ

መ. የፍልስፍና መጻሕፍት

ሠ. መጽሔት

ረ. በራሪ ፅሑፎች

ሰ. የታሪክ መጽሐፍ

ሸ. ሌላ ካለ ____________________

2.7 መጽሐፍ የሚያነቡት ለምን አላማ ነው? (ከአንድ በላይ መምረጥ ይችላሉ)

ሀ.ለመዝናናት

ለ.የንባብ ልምድ ለማሻሻል

ሐ.ለጠቅላላ እውቀት

መ.ለማስተማር ለመጠቀሚያ

ሠ.ለሁሉም

ረ.ሌላ ካለ ____________________

2.8 መጽሐፍ ካነበቡ በኋላ ስላነበቡት ጉዳይ ከጓደኞችዎ ጋር ይወያያሉ?

ሀ.ሁል ጊዜ

ለ.አብዛኛውን ጊዜ

ሐ.አልፎ አልፎ

መ.አልወያይም

2.9 የንባብ ልምድን እንዴት ማዳበር የሚቻል ይመስልዎታል?

ሀ.በየቀኑ በማንበብ

ለ.ለንባብ ያለንን የጊዜ አጠቃቀም በመወሰን

ሐ.የሚያዩትን ለማንበብ የጊዜ አጠቃቀም በመወሰ

መ.ሌሎች ______________________________

2.10 የንባብ ትምህርት ሲያስተምሩ ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ የራስዎን ተጨማሪ ምንባብ ያዘጋጃሉ?

ሀ.ዘውትር አዘጋጃለሁ

ለ.አብዛኛውን ጊዜ አዘጋጃለው

ሐ.አልፎ አልፎ አዘጋጃለሁ

መ.ፈጽሞ አላዘጋጅም

2.11 ንባብዎ ለማስተማር ዘዴዎ ያለው አስተዋጽዖ

ሀ.በጣም ከፍተኛ

ለ.ከፍተኛ

ሐ.መካከለኛ

መ.ዝቅተኛ

2.12 ተማሪዎች የተለያዩ ጽሑፎች አንብበው እንዲመጡ እና ስላነበቡት ጉዳይ እንዲወያዩ ያደርጋሉ?

ሀ.ዘውትር አደርጋለው

ለ.አብዛኛውን ጊዜ አደርጋለው

ሐ.አልፎ አልፎ አደርጋለው

መ.ፈጽሞ አላደርግም

2.13 ክፍል ውስጥ ምንባቦች የሚነበቡት በእርስዎ ነው?

ሀ.ሁል ጊዜ

ለ.አብዛኛውን ጊዜ

ሐ. አልፎ አልፎ

መ. አላነብም

2.14 ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የማንበብ እድል የሚያገኙት

ሀ ሁል ጊዜ

ለ.አብዛኛውን ጊዜ

ሐ.አልፎ አልፎ

መ.አያነቡም

2.15 በአካባቢዎ ንባብን የሚያበረታታ/የሚያደናቅፍ ምን ሁኔታ አለ?

ሀ. የሚያበረታታ

............................

............................

............................

............................

ለ. የሚያደናቅፍ

...................................

...................................

...................................

...................................

2 ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ጥያቄዎች የመምህሩን የንባብ ባህል በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ሲሰጥ የሚያከናውኗቸውን የግል ማስተማሪያ ዘዴ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ከተሰጡት አራት አማራጮች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ሲሰጡ የሚጠቀሙበት ዘዴ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ይህን ምልክት /✓/ በመጠቀም አመልክቱ፡፡

| ተ.ቁ. | የመምህሩ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ | ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዘውትር እጠቀማለሁ | አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ | አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ | ፈጽሞ አልጠቀምም |
| 1 | በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርቱ ሲጀምር ተማሪዎችን አነቃቃለሁ፡፡ | | | | |
| 2 | ተማሪዎቹን በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ በቡድን እና በጥንድ የሚያነቡበትን መንገድ እጠቀማለሁ፡፡ | | | | |
| 3 | ተማሪዎቹ ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ ባነበቡት ምንባብ ላይ ተመርኩዘው በቡድን እንዲወያዩ ✓ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 4 | የንባብ ትምህርት ሳስተምር ከመማሪያ መጻሕፍት ውጪ ተጨማሪ መጻህፍት እጠቀማለሁ፡፡ | | | | |
| 5 | ተማሪዎቹን ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲያነቡ አበረታታለሁ፡፡ | | | | |
| 6 | የንባብ ፍልጎት እንዲያድርባቸው ✓ አጓጊና ሳቢ ጽሑፎች በክፍል ውስጥ አቀርባለሁ፡፡ | | | | |
| 7 | ተማሪዎችን ከክፍል ውጪ ለሚያደርጉት ንባብ ደረጃቸውን የጠበቁ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ እሞክራለሁ፡፡ | | | | |
| 8 | የአንድን ጽሑፍ መልእክት ለመረዳት የሚያግዙ ጠቋሚ ዘዴዎችን ለተማሪዎችዎ እነግራለሁ፡፡ | | | | |
| 9 | ተማሪዎቹ ከምንባቡ ያገኙትን ✓ ሃሳብ /ጭብጥ እንዲናገሩ /እንዲጽፉ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 10 | በክፍል ውስጥ ምንባብ የማስነብበው በለሆሳስ ነው፡፡ | | | | |

ክፍል አራት፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።

4.1የንባብ ባህል እንዲዳብር በግልዎ ምን መደረግ አለበት ይላሉ ?

..........................................................................................................

..........................................................................................................

..................................................................።

4.2የንባብ ልምድዎና የማስተማር ዘዴዎ የተጣጣመ ነው?

..........................................................................................................

..........................................................................................................

..................................................................።

4.3በክፍል ውስጥ በንባብብ ትምህርት ለተማሪዎች የሚያደርጉት እገዛ ተገቢ ነው ይላሉ?

ተገቢ ነው ካሉ ማብራሪያ ይስጡ

..........................................................................................................

..........................................................................................................

..................................................................።

4.4የተለየ መይም ተጨማሪ ሀሳብ ካለዎት ይግለጹ፤

..........................................................................................................

..........................................................................................................

..................................................።

አዲስአበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

መጋቢት 2005 ዓ.ም

# አባሪ ሁለት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲ፣የቋንቋዎች ጥናት ፣የጆርናሊዝም የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በ12ኛ እና 11ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

ውድ ተማሪ፣የዚህ መጠይቅ ዓላማ የመምህራኑ የንባብ ባህል ከንባብ ማስተማሪያ ዘዴው ጋር ያለውን ግንኙነት ለማወቅ የሚረዳ ከተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ጥናቱም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የሚውል ሲሆን፣ከእናንተ የሚገኘው መረጃ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ስለሆነም የጽሑፍ መጠይቅን በትክክል እንድትሞሉ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡የሰጣችሁት መረጃም ለተጠቀሰው የጥናቱ አላማ ብቻ እንደሚውል ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡ውድ ጊዜያችሁን መስዋእት በማድረግ ላደረጋችሁልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

በመጠየቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

ክፍል አንድ

1 አጠቃላይ መረጃ

መመሪያ 1፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መረጃ ስጡ፡፡

1.1የክፍል ደረጃህ/ሽ................

1.2.ፆታ ወንድ.........ሴት.........1.3 እድሜ................

ክፍል ሁለት

መመሪያ 2፡-ከዚህ በታች የቀረቡትን ዝርዝር ጥያቄዎች አንብቡ ፡፡ከዚያም ከቀረቡት አማራጮች በግል ይበልጥ የምትስማሙበትን ሀሳብ የያዘውን ፊደል በማክበብ አመልክቱ፡፡

2.1በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለመከታተል ያላችሁ ፍላጎት ምን ያህል ነው?

ሀ.በጣም ከፍተኛ ለ.ከፍተኛ ሐ.መካከለኛ መ.ዝቅተኛ

2.2 በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የማንበብ እድል ይሰጣችኋል

ሀ.ዘውትር ለ.አብዛኛውን ጊዜ ሐ አልፎ አልፎ መ አይሰጥም

2.3 በንባብ ጊዜ መምህራችሁ ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ በግላቸው ጽሑፎቹን በማቅረብ ያለማምዷችኋል?

ሀ.ሁል ጊዜ ሐ.አልፎ አልፎ

ለ.አብዛኛውን ጊዜ መ.ፈጽሞ አያለማምዱንም

2.4 የአማርኛ ቋንቋ ንባብ ትምህርት ስትማሩ ከማስተማሪያ መጽሐፉ ውጪ ሌሎች ፅሑፎችን እንድታነቡ ያደርጋል?

ሀ.ዘውትር ሐ.አልፎ አልፎ

ለ.አብዛኛውን ጊዜ መ.ፈጽሞ አያደርጉም

2.5 መምህራችሁ ክፍል ውስጥ እንድታነቡ የሚያሳድሩት ተፅእኖ ምን ያህል ነው?

ሀ.በጣም ከፍተኛ ለ.ከፍተኛ ሐ.መካከለኛ መ.ዝቅተኛ

2.6 የአማርኛ ቋንቋ ንባብ ትምህርት ስትማሩ ከማስተማሪያ መጽሐፉ ውጪ ሌሎች ፅሑፎችን እንድታነቡ ያደርጋል?

ሀ.ዘውትር ሐ.አልፎ አልፎ

ለ.አብዛኛውን ጊዜ መ.ፈጽሞ አያደርጉም

2.7 ባነበባችሁት ጽሑፍ ላይ ከጓደኞቻችሁ ጋር በቡድን እንድትወያዩ ያደርጓችኋል?

ሀ.ሁል ጊዜ ያደርጋሉ ሐ. አልፎ አልፎ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ያደርጋሉ መ. አያደርጉም

2.8 ከክፍል ውጪ የተለያዩ ጽሑፎችን የማንበብ ልምድ ለማግኘት መምህሩ ያበረታታሉ?

ሀ.በጣም እስማምለሁ ሐ.አልስማማም

ለ.እስማማለሁ መ.በጣም አልስማማም

2.9 ለጥያቄ ቁጥር 2.7 መልሳችሁ"ሀ.በጣም እስማማለሁ "የሚል ከሆነ ልምዱን እንድታዳብሩ ያገዛችሁ ማን ይመስላችኋል ?

ሀ.የቋንቋ መምህራን ሐ. ጓደኞቼ

ለ. ወላጆቼ መ. የግል ተነሳሽነት

2.10 በዚህ የክፍል ደረጃ በመምህሩ አማካይነት የንባብ ችሎታዬ ተሻሽሏል ብላችሁ ታምናላችሁ?

ሀ በጣም እስማማለሁ

ለ. እስማማለሁ

ሐ.አልስማማም

መ.በጣም አልስማማም

ክፍል ሶስት

3 ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ሀሳቦች የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ንባብን ለማስተማር የሚጠቀሙበትን የማስተማሪያ ዘዴ ይመለከታል፡፡ከተሰጡት አራት አማራጮች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ስትማሩ መምህራችሁ የሚከተሉትን ተግባራት እንደሚያከናውኑ በዚህ ምልክት/✓/ በመጠቀም አመልክቱ፡፡

| ተራ ቁ. | የመምህሩ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ | ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዘውትር ይጠቀማል | አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማል | አልፎ አልፎ ይጠቀማል | ፈጽሞ አይጠቀምም |
| 1 | መምህራችሁ ትምህርቱን ሲጀምሩ ንባብን የምትማሩበትን አላማ ያሳውቋችኋል፡፡ | | | | |
| 2 | መምህሩ ከመማሪያ መጽሐፋችሁ ውጪ ሌሎች ጽሑፎችን አንብባችሁ ክፍል ውስጥ እንድትወያዩባቸው ያደርጋሉ፡፡ | | | | |
| 3 | መምህሩ ንባብን በግል በለሆሳስ እንድታነቡ ያደርጓችኋል፡፡ | | | | |
| 4 | መምህሩ ንባቡን ከጨረሳችሁ በኋላ ባነበባችሁት ምንባብ ላይ ተመርኩዛችሁ በቡድን እንድትወያዩ ያደርጋሉ፡፡ | | | | |
| 5 | መምህሩ ንባብን ለማስተማር የስነጽሑፍ ስራዎችን (ልቦለድ፣ሥነቃል፣ግጥም ወዘተ) በክፍል ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡ | | | | |
| 6 | መምህራችሁ ያነበባችሁትን ፅሑፍ ይዘት የተመለከተ ዘገባ እንድታቀርቡ ያደርጋሉ፡፡ | | | | |
| 7 | መምህሩ የተለያዩ የንባብ ስልቶችን ተጠቅማችሁእንድታነቡ ይነግሯችኋል፡፡ | | | | |
| 8 | መምህራችሁ ምንባብ ሲያስነብቧችሁ እንዴት ማንበብ እንዳለባችሁ ያስረዷችኋል፡፡ | | | | |
| 9 | መምህሩ ክፍል ውስጥ ለሚደረገው የንባብ ተግባር ግልጽ መመሪያ ይሰጣችኋል፡፡ | | | | |

ራት

ተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።

ሩ በክፍል ውስጥ ለንባብ ትምህርት የሚያደርጉላችሁ እገዛ ተገቢ ነው ሁ?አዎ ከሆነ መልሳችሁ እንዴት?

....................................................................................................

....................................................................................................

........................................።

ቧቸውን መጻሕፍት መምህራችሁ ይጠቁማችኋል? መልሳችሁ አዎ ከሆነ ፍቱን የምታገኙት በምን መንገድ ነው?

....................................................................................................

....................................................................................................

ልምድ እንዲዳብር በግልየአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ምን ማድረግ አለባቸው ታምናላችሁ?

....................................................................................................

....................................................................................................

........................................


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

መጋቢት 2005 ዓ.ም

# አባሪ ሶስት

## የምልከታ ቅፅ (checklist)

የንባብ ትምህርት ሲሰጥ መምህሩ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ለመከታተል የተዘጋጀ የምልከታ መከታተያ ቅጽ (checklist)

የመምህሩ መለያ ኮድ ........................... ት/ቤት.............

ክፍል ጊዜ...................... የትምህርቱ ርእስ...............

የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ ............... የግምገማ ጊዜ.................

መመሪያ፦በዝርዝር የቀረቡት ሀሳቦች የተከናወኑ ከሆነ ይህን ምልክት"✓" በመጠቀም አመልክት/ቺ፡፡

| ተራ ቁ. | የመምህሩ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
|---|---|---|---|
| 1 | የንባብ ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት ተማሪዎችን የማነቃቃት ስራ | | |
| 2 | የቀረበው ጽሑፍ ተማሪዎችን የሚያነሳሱና ደረጃቸውን የጠበቀ | | |
| 3 | የንባብ ትምህርት ሲያስተምሩ ከመማሪያ መጻሕፍት ውጪ ተጨማሪ መጻህፍት መጠቀም | | |
| 4 | ተማሪዎቹን ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲያነቡ ማበረታታት | | |
| 5 | የአንድን ጽሑፍ መልእክት ለመረዳት የሚያግዙ ጠቋሚ ዘዴዎችን መጠቀም | | |
| 6 | ተማሪዎቹ የንባብ ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ | | |
| 7 | የንባብ ፍልጎት እንዲያድርባቸው አጓጊና ሳቢ ታሪኮችን ያዘሉ ጽሑፎች መጠቀም | | |
| 8 | ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ለሚያደርጉት ንባብ ከደረጃቸው ጋር አብሮ የሚሄድ መሆን አለመሆኑን የማረጋገጥ ተግባር | | |
| 9 | በክፍል ውስጥ ፅሑፎች የሚነበቡት በሰአት በተመጠነ ፍጥነት | | |
| 10 | መረጃዎችን ለይቶ ለማውጣት የገረፍታ ንባብ የማድረግ ስራ | | |
| 11 | ለንባቡ ጊዜ ወስነው (ደቂቃ ወስነው) የማንበብ ተግባር | | |
| 12 | ተማሪዎቹ ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ ባነበቡት ምንባብ ላይ ተመርኩዘው በቡድን ማወያየት | | |
| 13 | ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያያይዙት ማድረግ | | |
| 14 | ተማሪዎችን ምንባብ ሲያስነብቡ እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው የማሳየት ተግባር | | |
| 15 | ተማሪዎች የጽሑፉን አደረጃጀት መረዳታቸውን ጥያቄ የመጠየቅ ተግባር | | |

## አባሪ አራት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲ፣የቋንቋዎች ጥናት ፣የጆርናሊዝም የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

**ለቃለ መጠይቅ (1) የተዘጋጁ ጥያቄዎች**

**ለመምህራን የሚቀርብ**

1. የማንበብ ልምድ የሌለው መምህር የንባብ ልምድ ካለው መምህር በምን ይለያሉ? በማስተማር ብቃታቸውስ ላይ ልዩነት ያመጣል ብለው ያስባሉ? ካሰቡ በምን መልኩ?
2. የማንባብልምድምና የማስተማር ዘዴም ተጣጣሚነት አለው ብለው ያስባሉ?
3. ከማስተማሪያ መጻሕፍት ውጪ ለተማሪዎችዎ የሚያቀርቧቸው ጽሑፎች ስፋት እንዴት ይገልጹታል?
4. ተማሪዎቹ ንባብን የመማር ፍላጎት በመምህሩ ጥረትና የማስተር ዘዴ ይወሰናል ብለው ያስባሉ?
5. ከሌላ የስራ ባልደረባዎ ጋር ስለንባብ ባህል መዳበር ይወያያሉ ?ውይይቱን የሚያደርጉት በምን መልኩ?
6. የንባብ ባህልዎ ዳብሮዋል ብለው ያስባሉ?እንዴት

**ለቃለ መጠይቅ (2) የተዘጋጁ ጥያቄዎች**

**ለአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት ሀላፊዎች**

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በንባብ ባህል መዳበርና በትምህርቱ አሰጣጥ ላይ የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ በክፍለ ትምህርቱ የሚደረገው አነሳሽነት ምን ያህል ነው?የመምህራኑስ ፍቃደኝነት አለ?
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎቹን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል የሚደረጉት ጥረት ካለ በክፍለ ትምህርቱ ምን ያህል ድጋፍ ያገኛል?
3. በመምህራኑ የንባብ ልምድ ላይ ጎልቶ የሚታይ ችግር ካለ ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት የተደረገው ጥረት ምንድነው? መምህራን ያላቸው ተነሳሽነት ምን ያህል ነው?

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለጸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ የአማርኛ ማስተማር መረሃ ግብር ተማሪ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የራስ ስራ ስለመሆኑንና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኳቸውን ተዛማጅ ጽሑፎች እና የመረጃ ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ሙሉ ሠለሞን

ፊርማ ________

አድራሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የማስረከቢያ ቀን ሰኔ 2005 ዓ.ም